



የአዋሣ፡ደብረምሕረት፡ቅዱስ፡ገብርኤል፡ቤተክርስቲያን
አዲሱ፡ሕንፃ

# ማዕዶት



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ግማደ መስቀሉ የሚኖርበት
የግሼን እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን

መስከረም ፲፱፻፹፭ ዓ.ም.
ቁጥር ፴፰
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

# ማዕዶት

መስከረም ፲፱፻፹፩ ዓ.ም.

ቁጥር ፴፰

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

« ማዕዶት »

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኖችዋን በቅዱስ ወንጌል መክራ፥ አስተምራ ፣ በአንብዓ ንስሐ አጥባ የተቀደሰ ትሩፋት አሠርታ በሥጋው ወደሙ አንጽታ፤ከዚህ ዓለም ወደ ገነት (ወደ መንግሥተ ሰማያት) መርታ የም ታሸጋግር ስለሆነች ይህ በየሦስት ወር የሚወጣው መጽሔት «ማዕዶት» ብላ ሰይመ ዋለች ። ማዕዶት ማለትም መሸጋገሪያ ድልድይ (መሰላል) ማለት ነው ።

ዋና አዘጋጅ

ሊቀ ትጉሃን ገ/ ክርስቶስ ኃ/ማርያም

ስልክ ቍ. 11 26 63 } አ/ አበባ

ፖ. ሣ. ቍ. 1283


| ተራ ቍ/ | ማ ው ጫ<br>አ ር እ ስ ት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርእሰ አንቀጽ . . . . . . . . | ፭ |
| ፪ | ቅዱስነታቸው በዘመን መለወጫ በዓል ቃለ ምዕዳን አስተላለፉ | ፰ |
| ፫ | የቅዱስ ፓትርያርኩ በዓለ ሢመት . . . . . | ፲ |
| ፬ | ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል . . . . . | ፲፱ |
| ፭ | ፓትርያርኩ በዘመን መለወጫ ዕለት በራጉኤል ቤተ ክርስቲያን | ፳፩ |
| ፮ | ቅዱስነታቸው በዘመን መለወጫ ቀን ለሠራተኛ ቡራኬ ሰጡ | ፳፪ |
| ፯ | ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ደብረ ጽጌንና ደብረ ሊባኖስን ጎበኙ | ፳፭ |
| ፰ | ቅዱስ ፓትርያርኩ በቍጥጥር ሥር ላሉት ቡራኬ ሰጡ | ፴፩ |
| ፱ | ቅ/ፓትርያርኩ በደ/ዘይት ቅ/ሩፋኤል በዓል . . . | ፴፬ |
| ፲ | ቅዱስነታቸው ለተፈናቃዮች ፰ ሺህ ብር ሰጡ . . | ፴፯ |
| ፲፩ | ፓትርያርኩ በዝዋይ ለሠለጠኑ የምስክር ወረቀት ሰጡ . | ፴፱ |
| ፲፪ | የቅ/ ሚካኤል ተአምር . . . . . . | ፵፪ |
| ፲፫ | ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በመድኃኔ ዓለምና በመጥ/ዮሐንስ | ፵፪ |
| ፲፬ | ቅዱስነታቸው አዋሳን ጎበኙ . . . . . | ፵፬ |
| ፲፭ | እውነቱ ሲገለጥ . . . . . . . | ፶ |
| ፲፮ | ያየነውን እንመሰክራለን . . . . . . | ፶፬ |
| ፲፯ | ንጽሕት በድንግልና . . . . . . . | ፶፭ |




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ... ደግ ቤተ መጻሕፍት

# «እ ን ቁ ጣ ጣ ሽ»

ይህ ቃል የተነገረውና ታሪኩም የተመሠረተው ከልደተ ክርስቶስ አንድ ሺህ ዘመናት በፊት ነው ቦታውም በኢየሩሳሌም ሰሎሞናዊ ቤተ መንግሥት ውስጥ ነበር የታሪኩ መንሥኤም በእስራኤላውያንና በኢትዮጵያውያን መካከል በነበረው ማኅበራዊና መንግሥታዊ ግንኙነት ምክንያት ነው ።

ወደኋላ መለስ ብለን ስለሁለቱ አገሮች ለብዙ ዘመናት የኖረው ግንኙነት በተመለከተ ከዚህ ላይ ለመጥቀስ እንሞክራለን ። አበው ኢትዮጵያውያን «እግዚአብሔር ከኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር ተለያይተው የኖሩበት ጊዜ የለም» ብለው እንዳስቀመጡት ሁሉ እስራኤላውያን በግብጻውያን ቀምበር ተይዘው በነበሩበት ዘመን ሀገራችን ኢትዮጵያ በነጻነትዋ ታፍራና ተከብራ ፣ በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንታ ትኖር እንደነበር ከታሪክ ማኅደር ለመረዳት እንችላለን ።

ለማስረጃም ያህል ሙሴ ከፈርኦን እጅ አምልጦ ከምድረ ግብጽ ወጥቶ የኮበለለው ስዊስካናል ተሻግሮ ወደ አማሌቃውያን አገር ሳይሆን በቦርት ሰዒድ ምድረ በዳ አድርጎ ወደ ከሰላ በመዝለቅ በተሰነይ ወደከረን ምድረ ኢትዮጵያ እንደገባ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ለመረዳት ይቻላል ። በሙሴ ዘመን ከረን ምድያም እየተባለች ትጠራ እንደነበርም ታውቆአል ።

ሙሴ ከረን ወይም ምድያም በደረሰ ጊዜ የምድያም ካህን የዮቶር ሴቶች ልጆች በጎቻቸውን ውኃ ለማጠጣት ከጉድጓዱ መክደኛ ጋር ሲታገሉ ስላገኛቸውና መክደኛውንም አንሥቶ በጎቹን ውኃ ስላጠጣላቸው ወስደው ከአባታቸው ከዮቶር ጋር አስተዋወቁት ። ዮቶርም ደስ ብሎት ሙሴን በክብር ተቀብሎ ከቤቱ አስገባው ፤ ከጊዜ በኋላም ከልጆቹ አንዲን አጋብቶ ከርሱ ጋር እንዲቀመጥና በጎቹንም እንዲጠብቅለት አደረገ ።

ሙሴም ሲፓራ ከምትባል ከካህኑ ከዮቶር ልጅ ሁለት ልጆች ወልዶአል ። ነገር ግን ሙሴ ከዮቶር ቤት ወጥቶ ወደ ግብጽ ከወረደ በኋላ ዮቶር ሙሴን ወደግብጽ ሸኝቶ ልጁንና ለሙሴ የወለደችለት ሁለቱ ልጆቹን ይዞ ወደ ምድያም ተመለሰ ። ሙሴ ሕዝቡን በአስደናቂ ተአምር ከፈርኦን ጽኑ አገዛዝ ፈልቅቆ ባሕረ ኤርትራን አሻግሮ ወደምድረ ርስት በሰላም እንደሚመራቸው ዮቶር ስለሰማ ሚሽቱንና ልጆቹንም ይዞለት ወደ ራፊድም ሄደ ።

በዚሁ ጊዜ ዮቶር የእስራኤል ሕዝብ ከሠፈሩበት ቦታ ከራፊድም ደረሰ ዮቶርም ሙሴ በሕዝቡ ፊት ሲፈርድ ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ እንደተቀመጠ ተመለከተ ። በዚሁ ጊዜ ዮቶር ሙሴን «ይህ የምታደርገው ነገር ሁሉ ልክ አይደለም። እንዲህም አይሁን የእስራኤል ልጆች በሙሉ ይሰብሰቡ ሕዝቡም ከመካከሉ አዋቂዎችን ይምረጥ ። አንተም አሥር አለቃ ሃምሳ አለቃ መቶ አለቃ ፣ ሻለቃ ብለህ ሹምላቸው ። ሥራውንም በየደረጃው አከፋፍለህ እንዲሠሩ አድርግ» ብሎ ዮቶር ለሙሴ መመሪያ ሰጠው ። በዚሁ መመሪያ መሠረትም ሙሴ የዮቶር ሐሳብ ተቀብሎ በሥራ ላይ አዋለው ። ሙሴም ድካሙን ሁሉ ተቀነሰለት ።

በዚህ መመሪያ መሠረት የእስራኤል ልጆች ብቻ ሳይሆኑ የዓለም ሕዝብ በሙሉ በዚህ መመሪያ ሲጠቀምበት ይኖራል ። የኢትዮጵያዊው ካህን የዮቶር አመራርና የአስተዳደር ስልት በመጽሐፍ ቅዱስ ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ ካየን(ካገኘን)ሀገራችን በሃይማኖት በታሪክ በሥነ ጽሑፍ በአስተዳደር፡ በሥነ ሥርዓትና እንግዳን በመቀበል ከዓለም ሁሉ በጣም የተለየ ታሪክ ያላትና የታወቀች አገር መሆንዋን እንረዳለን ።

በእስራኤላውያንና በኢትዮጵያውያን መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሠረተው ግንኙነት በዚህ መንገድ ሲሆን ከዚያን ጊዜ ወዲህ ግን ሁለቱ ሕዝቦች ተለያይተው አያውቁም ። ይኸውም ሙሴ ታቦተ ጽዮንን ከሲናይ ተራራ ከእግዚአብሔር እጅ ተቀብሎ ታቦቱ ወደ ኢየሩሳሌም ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ከክርስቶስ ልደት በፊት በዓላቱን ለማክበርና ለመስገድ ፤ ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ደግሞ ክርስቶስ ያስተማረባቸውን የተዘዋወረባቸውን ቦታዎችና የሞተበት የተቀበረበትና የተነሣበትን ያረገበትንም ሥፍራዎች ለመጎብኘትና ለመሳለም ክርስቲያኖች (ምእመናን) ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ ይኖራሉ ።

በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት የንግሥተ ሳባ መኳንንትና መሣፍንት ለስግደት ወደ ኢየሩሳሌም

www.ethiopianorthodox.org

ሂደው በተመለሱ ቍጥር የሰሎሞንን ታሪክና ዝና ጥበብና ብልጽግና የገንዘብ የሀገር ስፋትና የሠራዊት ብዛት ለንግሥቲቱ ሳይናገሩ የዋሉበትና ያደሩበት ጊዜ አልነበረም ።

ስለዚህ ንግሥቲቱም በጆሮ የሰማችውን በዓይን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እንዳለባት አምና ወሰነች ። ለጉዞዋም ብዙ ዝግጅት አደረገች ፤ የዝሆን ጥርስ ፣ የዝባድ ሽቶ ፤ ወርቅና ብር ልዩ ልዩ የከበሩ ዕቃዎች ሁሉ አዘጋጀች ። ጉዞው በተወሰነበት ጊዜ ንግሥቲቱ ከነመኳንንቶች ዋ ፤ ከነመሳፍንቶችዋ ከነሠራዊቶችዋና ከነደንገጡሮችዋ ጋር በአሥመራ ከዚያም በከሰላ ወደ ስዊስ ካናል ፣ ቀጥሎም በሲና በረሀ ተጉዛ ኢየሩሳሌም በታላቅ ክብርና ግርማ ገባች ። በዚያን ጊዜ ንጉሡ ሰሎሞን በክብርና በከፍተኛ ዝግጅት ተቀበላት ፤ ንጉሡ ሰሎሞንም ንግሥት ሳባን በጆሮ የሰማችውን ሁሉ በዓይንዋ ለማየት እንድትችል አድርጎ አስጎበኝቶአታል ።

በመጨረሻም ንግሥቲቱ ለንጉሥ ሰሎሞን የወሰደችለትን ገጸ በረከት አቀረበችለት ። ንጉሡም ለንግሥቲቱ ያዘጋጀላትን ስጦታ አቀረበላት ። ሰሎሞን ለንግሥተ ሰባ ያቀረበላት ገጸ በረከት እርስዋ ካቀረበችለት የተለየ ስጦታ ነበር ፤ እርሱም የከበረ ማዕድን ነበር ። ይህ ክቡር ማዕድን ዕንቍ ነበር ። ንጉሥ ሰሎሞን ለንግሥተ ሳባ ሲሰጣት ወይም ሲያበረክትላት «ዕንቍ ለጣትሽ» በማለት ነበር ።

አንዳንዶቹ ደግሞ «ዕንቍ ለጣጣሽ» ነው ያላት የሚሉም አሉ ። ነገር ግን አባባሉ ልክ ነው ከማለት ሌላ ማስተባበያ አንሰጠውም ። ምክንያቱም ለጣትሽም ፣ ለጣጣሽም ቢልም አባባሉ የተራራቀ አይደለምና ነው ። ዕንቍንጉሡ ለንግሥቲቱ የሰጣት ስጦታ ነው ። እንዲህ ከሆነ ለጣቷም ለጣጣዋም ብታደርገው የሚያስቸግር የሚያከራክር ታሪክ አያመጣም ። ዕቃው ግን ከሁሉም የተለየና የከበረ መሆኑን መረዳት ይገባል ። «ዕንቍ» ከወርቅ ከብርና ከሌሎችም የማዕድን ድንጋዮች ከፍተኛ ብልጫ ያለውና እጅግ ክቡር ስለሆነ ሰሎሞን ላቅ አድርጎ በማየት ለከበረችውና በታሪክ ለገነነችው ንግሥት ሳባ ሰጣት «ዕንቍ»በጨለማ የሚያበራ ከመሆኑም በላይ ብርሃኑም እስከ አራት ዓይነት እየለዋወጠ የማሳየት ጠባይ ነበረው ። (አለው)

በንጉሥ ሰሎሞንና በንግሥተ ሰባ መካከል ስለነበረው ግንኙነት በሀገራችን ሰፋ ባለ መልኩ የሚነገር ቢሆንም በዚሁ ጽሑፋችን ለመጥቀስ የፈለግነው ግን ስለዕንቍ ጣጣሽ አመሠራረትና አመጣጥ በሀገራችን ስላለው የዕንቁጣጣሽ ባሕላዊ ይዘት በመጠኑም ቢሆን ለመግለጽ ነው ። ዕንቍጣጣሽ ከላይ በተገለጸው መልኩ ተመሥርቶ አሁን የሚታየው የአከባበር ስነ ሥርዓትና ድርጊት የተለያየ መልክና ይዘት እንዳለው እንመለከተዋለን ።

በመሠረቱ «ዕንቍጣጣሽ» የሚውለው መስከረም አንድ ቀን ነው ። ሰሎሞንና ንግሥተ ሳባ የተገናኙበት ቀን ምናልባት በዚህ ቀን ወይም ወር ላይሆን ይችላል ። መሠረቱ ግን ንግሥተ ሳባ ለንጉሡ ሰሎሞን ባቀረበችው ገጸ በረከት ንጉሡ ደግሞ ለንግሥቲቱ የሰጣት አጸፋዊ ገጸ በረከት እንዴት እንደ ነበረ በዓይነ ሕሊና መገንዘብ ይቻላል ።

በመስከረም ወር ምድር በምልዓ በአዝርዕትና በአትክልት ልምላሜ የምትሸፈንበት በተለያዩ ሥነ ጽጌያት የምታሸበርቅበት በመሆኑ ይህ ወር የዕንቍጣጣሽ በዓል እንዲከበርበት የተመረጠ ነው ለማለት ያስችለናል ። በዕንቍጣጣሽ ቀን ልጃገረዶች የአበባ ዓይነቶች በማዛመድና ኅብረ መልክዕ በመፍጠር ለቤተ ሰቦቻቸውና ለወገኖቻቸው እንዲሁም ለጐረቤቶቻቸው «ዕንቍጣጣሽ» በማለት የአበባ ጉንጉን ያበረክታሉ ። ተቀባዮቹም «በየዓመቱ ያምጣሽ» እያሉ አበባውን ከተቀበሉአቸው በኋላ ገንዘብ ይሰጧቸዋል ። እነርሱም በሰጧቸው ገንዘብ የፈለጉትን ገዝተው «የዕንቍጣጣሽ በረከት» እያሉ እንደማስታወሻ አድርገው በክብር ይዘው ይጠቀሙበታል ። እነሆ በሁለቱ ታላላቅነገሥታት ዘመን የስጦታ መለዋወጥ የተመሠረተው የዕንሻቍ ጣጣሽ ታሪካዊ ባሕል እስካለንበት ዘመን በመድረሱ በዓሉ በዘመናችን በገነነ ሁኔታ ሲከበር ይታያል ።

በሀገራችን በዕንቍጣጣሽ ቀን ልዩ ልዩ ባሕላዊ ጨዋታ ይታያል ፤ በቤተ ክርስቲያናችንም የዘመን መለወጫ የዕንቍጣጣሽ ቀን በመሆኑና የመጥምቁ ዮሐንስ ምትረተ ርእሱ ዋዜማም ስለሆነ ልዩ ክብርና ትርጉም ያለው በዓል ነው ። በዕለተ ምጽዓት የሚመሰለው ወርኃ ክረምት አልፎ በመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ የሚታየው ወርኃ መጸው የሚተካበት ቀን ስለሆነ የዕንቍጣጣሽ በዓል ኢትዮጵያውያን በከፍተኛ ድምቀትና ስሜት አክብረውት ይውላሉ ።

የ፲፱፻፹፭ ዓ/ም የእንቍጣጣሽ በዓል ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ልዩ ዝግጅትና ትርኢት ባለው ሁኔታ ተከብሮ ውሎአል ። በዝግጅቱ በሥነ ሥርዓቱ የሰላም አየር የነፈሰበት ወቅት በመሆኑ እንዲሁም የእምነት ነጻብራቅ በስፋትና በጥልቀት ሲነገር በመዋሉ ከመቸውም በበለጠ ልዩ ያደርገዋል ።

እንዲሁም በ፲፯ኛው ቀኑ የዋለው በዓለ መስቀልም ካሁን በፊት ታይቶና ተሰምቶ የማይታይ ከፍተኛ ክብርና መብት ያገኘበት ዕለት ነበር ። በዜና መገናኛ ያየ የሰማና የተመለከተ ሕዝብ ሁሉ ልዩ ስሜት አሳድሮበታል ። በእምነቱ ድክመት ተሰምቶት የነበረው ተጽናንቶ ብርታትን አግኝቶ በዓሉን በሥነ ሥርዓት አከብሮታል ። ተስፋ ቆርጦ ተቀምጦ የነበረው ሌላው ወገንም ሙሉ ደስታና ሰላም አግኝቶ ለሃይማኖቱ ታጥቆ ለመሥራት ቆርጦ ተነሥቶአል ።

ሌላው ከእንቍጣጣሽ በዓላችን ጋር አብረን አዳምረን የምናየው የዘመናችን አዲስ ታሪክ አለን ። ከዚህ ከዕንቍጣጣሽ በዓላችን አኳያ ለቤተ ክርስቲያናችን በዕንቍጣጣሽ ዋዜማ የቤተ ክርስቲያኒቱ ራስ ወይም አባት ሆነው የተሰጡን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በሚያደርጉት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሁሉ እጅግ የሚያስደስት ስለሆነ ለቤተ ክርስቲያናችን አዲስ ምዕራፍ ነው ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ በቅዱስ ሲኖዶስ በገዳማት ፣ በአድባራትና በአብያተ ክርስቲያናት ተጠሪዎች በሊቃውንት ፣ በመምህራን በሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጆች በአውራጃ ሊቃነ ካህናት በሰበካ ጉባኤ ምክትል ሊቃነ መናብርት በምእመናን ተወካዮች በተላኩት ታላላቅ አዛውንት በሰንበት ት/ቤት ተወካዮች ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም በምልዓተ ድምፅ ተመርጠው ሐምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ሥርዓተ ሢመታቸው በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በከፍተኛ ድምቀትና ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞአል ።

በዚህ ታላቅ በዓል ላይም የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የገዳማትና የአድባራት አበምኔቶች ታላላቅ እንግዶችና የመንግሥታት ተወካዮች የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና የአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች ካህናትና ሊቃውንት ጥሪ የተደረገላቸው ታላላቅ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችና በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የከተማው ነዋሪዎች በተገኙበት በላቀና በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ ውሎአል ።

በዚህ ሥነ ሥርዓት ላይም ከሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ከካቶሊክና ከባቲካን ካቶሊክ ኤምባሲ ፣ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርና ከአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ከዓለም ሉተራን ማኅበር ወዘተ - - - ልዩ ልዩ ስጦታዎች ለቅዱስ ፓትርያርኩ ተበርክቶላቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ይህ ከባድና ከፍተኛ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ተረክበው አክሊለ ጽድቅ ደፍተው የኖላዊ አባግዕ ምልክት የሆነ በትረ ጽድቅ ከጨበጡበት ዋዜማ ጀምሮ ከአንድ የቤተ ክርስቲያን አባትና መሪ የሚጠበቀውን ግዳጅ ያለ ዕረፍት ሌት ተቀን ሲወጡት ይታያል ።

ስለዚህ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አዲሱ ዓመት የሥራ የአንድነት ፤ የፍቅር ፣ የወንድማማችነት የነጻነት የሰላም የዕረፍት የስብከተ ወንጌል ክንዋኔ ፣ የቤተ ክርስቲያን ዕድገትና መስፋፋት በቀለጠፈ ሁኔታ ለመወጣት ይችሉ ዘንድ ብርታትን ጽናትን ትዕግሥትንና ማስተዋልን እንዲሰጣቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዘወትር ጸሎትዋና ምኞትዋ ሊሆን ይገባል ፤ ኃያሉ እግዚአብሔር ቅዱስነታቸውን በተግባራቸው ሁሉ እየተገኘ እንዲባርካቸው ማዕዶት በዚህ አጋጣሚ ምኞቱን ይገልጻል ።

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በዘመን መለወጫ ሲያስተላልፉ ቃለ ምእዳን

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ በዓል ምክንያት በማድረግ በሬድዮ ፤ በቴሌቭዥንና በጋዜጦች ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተላለፉት ቃለ በረከት ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

— በበአታት ፣ በገዳማትና በአድባራት የምትገኙ አበው ግሑሳን መነኮሳት

— በየከተማው ፣ በየገጠሩ ያላችሁ ካህናት ፣ ምእመናንና ምእመናት ፣

— የሀገራችንን ክብረ ወሰን ለማስከበር በየጠረፉ የተሠማራችሁ የመከላከያ ኃይላት ፣

— በደዌ ዳኛ ፣ በአልጋ ቁራኛ ተይዛችሁ በየቤታችሁና በየ ሆስፒታሉ የምትገኙ ሕሙማን ፣

— በንግድ ዓለም ተሠማርታችሁ በአየር ፣ በየብስና በባሕር የምትመላለሱ ነጋድያን ፣

— በልዩ ልዩ ምክንያት ከውዲቱ ሀገራችሁ ወጥታችሁ በውጭ ሀገር የምትኙላሉ ኢትዮጵያውያን ፤

— በሕግ ሥር ሁናችሁ ፍትሕ ፣ ርትዕ ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ ያላችሁ ወገኖቻችን በሙሉ

— ልዑል እግዚአብሔር ወርኃ ክረምቱን አስፈጽሞ እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሰን አደረሳችሁ ።

«ወትባርክ አክሊለ ዓመተ ምሕረትከ

ወይጸግቡ ጠላት ገዳም

ወይረውዩ አድባረ በድው» ይህ ዛሬ በመላ ኢትዮጵያ በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ የሚውለው በዓል ርእሰ ዐውደ ዓመት እየ ተባለ ሲጠራ ይኖራል ። ስያሜውም ከጥንት ከቤተ ክርስቲያን አባቶችና ሊቃውንት ተያይዞ የመጣ ነው ፤



ቅዱስነታቸው እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰዎ ለማለት የመጡትን ቡራኬ ሲሰጡ

ርእስ የሚለው ቃል የአካላታችን መጀመሪያ ክፍል እንደሆነ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው ። ይህ በዓል የዓመቱንና የበዓላቱን መጀመሪያ በመሆኑ ርእሰ ዐውደ ዓመት ተብሎ ተሰየመ ። ዐውድ ዙሪያ ክብ ካመት እስከ ዓመት ያለ ጊዜ የሚያጠቃልል ማለት ነው ።

በዚሁ መሠረት ዐውደ ፀሐይ ፣ ዐውደ ወርኅ ፣ ዐውደ ዓመት ፣ ወይም የዓመቱን ሙሉ ዙር የሚያመለክት ማለት እንደሆነ መጻሕፍትና ሊቃውንት ያስረዳሉ ፤ ያስተምራሉ ። ይኸውም ዐውደ ዕለት ሰባት ቀን ሲሆን ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያለው ነው ። ዐውደ ወርኅ የጨረቃ ዐውደ ዓመት ፫፻፶፭ ቀን ነው ፤ ዐውደ ፀሐይ የፀሐይ ዐውደ ዓመት ፫፻፷፭ ቀን ተሩብ ይሆናል ።

ቅዱስ ዳዊት ዓመተ ኵነኔ ፣ ዓመተ ፍዳ ፤ ዓመተ ዓለም እየተባለ ሲቈጠርና ሲነገር የኖረው ዘመናት አብቅቶ ዓመተ ምሕረት የሚባል ዘመን እንደሚተካ በመንፈስ እግዚአብሔር ተረድቶ ከላይ በግእዝ የተጠቀሰውን ዘምሮአል ። የቃሉ ትርጉምም የበረሀ ልምላሜ እንዲጠግብ ፣ የምድረ በዳ ተራሮች እንዲረኩ የዓመተ ምሕረትህን ዐውደ ዓመት ወይም ራስ ትባርካለህ የሚል ነው ። በተጨማሪም ይህ በዓል ቅዱስ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራል እርሱም መጥምቁ ዮሐንስ ነው ። ቅዱስ ዮሐንስ በዓመተ ዓለም ማብቂያ በዓመተ ምሕረት መጀመሪያ ላይ ሆኖ ሕዝቡን የንስሐ ጥምቀት ሲያጠምቅ የነበረ የሃይማኖት አባት ነው ። በዚህ መሠረትም ነቢይም መጥምቅም ፣ ሐዋርያም ሰማዕትም እየ ተባለ ሲጠራ ይኖራል ።

ዛሬ ይህን በዓል ስናከብር ብዙ ትገዝ የሚሉን ነገሮች አሉ ። በተለይም ከጥቂት ዓመታት በፊት በሀገራችን ላይ በተፈጠረው አለ መግባባት በተነሣው የእርስ በርስ ጦርነት ተወግዶ የሰላም የፍቅር ፣ የአንድነት ፣ የነፃነት ፣ የእኩልነት የፍትሕና የርትዕ ዘመን ከተበሠረ አንድ ዓመት አልፎታል ።

በዚህም መሠረት እግዚአብሔር አምላካችን ባሁኑ ጊዜ በሀገራችን ላይ ከዳር እስከ ዳር ዝናመ ምሕረቱን ዕከለ በረከቱን መስጠት ጀምሮአል ። ወርኃ ክረምቱን በሰላም አስፈጽሞ ከድጡ ፣ ከማጡ ከመብረቁ ከጎርፍ ከዶፉ በዶህና አሳልፎ ፣ በደመና ተሸፍኖ የከረመውን ብሩህ ሰማይ ተገልጦ ለማሳየት በማብቃቱ ብሩህ ዘመን የማምጣቱን ምልክት ነው ።

ወንዞች ሲያወርዱት የከረሙትን ድፍርስ ጎርፍ ከዚህ ወር ጀምሮ እንደ በረዶ የጠራ ውኃ ያፈሳሉ ። ተራራው ሸንተረሩ በልምላሜ ተሸፍኖ በሥነ ጽጌያት አሸብርቆ ጌና መዓዛው ሲያውድ ፤ ንጹሕ አየር ሲነፍስ ሰላም አጥቶ ሲጨነቅ የነበረው ፍጥረት ሁሉ በሰላም ሲመላለስ እጅግ እንደሚደሰት የታመነ ነው ። አዲስ ልብስ ለብሶ የአዲሱን ዓመት በዓል በደስታ ሲያከብር ባሕላዊ ዘፈኑን ፣ መዝሙሩን ሲዘምር ርካታን ያሳድርበታል ።

ጠቢቡ ሰሎሞን «ከሰማይ በታች አዲስ ነገር የለም»ይላል ስለአዲሱ ዘመን ግን ብዙ ለመናገር ይቻላል ። ሁሉም ከተገኘው የተገኘ ወይም የሚገኝ ቢሆንም ማንኛውም አዝርዕትና አትክልት ከተዘራ በኋላ ፈርሶ በስብሶ በሌላ መልክ ተለውጦ ሲወጣ አዲስ እህል መባሉ አይቀርም ።

ያደፈ ልብስ እንኳ በሳሙናና በውኃ ታጥቦ ሲነጻ ወይም ለውጥ ሲያሳይ አዲስ መስሎ መታየቱ አይቀርም የሰው ልጆችም እንደዚሁ በዚህ በአዲስ ዓመት ከመጥፎ ጠባያቸው በኃጢአት ካደፈው ሰውነታቸው በእንብዓ ንስሐ ታድሰው ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡና ሲታረቁ አዲስ ይሆናሉ እግዚአብሔርን ከሚያሳዝን ፣ ሰውን ከሚያስቀይም ተግባር ተቆጥበው በመልካም ሥነ ሥርዓት ሲመሩ ፍሬ ትሩፋት ሲያፈሩ ለውጥ ያሳያሉ ።

ይህም ማለት በመንፈስም በሥጋም ታድሰው በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ የሚያገኙበትን የጽድቅ ኑሮ ሲመሠርት ነው ። በየዓመቱ የዘመን መለወጫና መታደስ ያለና የነበረ ሥርዓት ነው ። ነገር ግን ሰው ራሱ ከክፉ አስተሳሰቡና ከመጥፎ አድራጎቱ ካልተመለሰ በአእምሮውም ካልታደሰ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ፣ ከጭካኔ ወደ ርኅራኄ ካልተለወጠ ዘመን ተለወጠ ፣ ታደሰ ብሎ ለመናገር አይቻልም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በአእምሮአችሁ መንፈስ ታደሱ» ሲል በሰጠው ምክር ከሁሉም የሚበልጠው የአእምሮና የመንፈስ መታደስ ነው ሰውነቱን በልዩ ልዩ መናኛ ሥራ በክሉ አዲስ ዓመትን አከብራለሁ ቢል ተገቢ አይሆንም ።

በአዲሱ ዓመት ለሰው ልጆች ሁሉ ነፃነት ፤ እኩልነት ዕውቀትና ብልጽግና ፍቅርና ሰላም ደስታና ጤንነት ፣ እውነትና ፍትሕ ርትዕ እንዲሰፍን ካስፈለገ ሁሉም በያለበት ሆኖ ለሰላም መቆም ስለሰላም ጠቃሚነት በተግባር እንዲያበሥር ግዴታ አለበት ያለ ሰላም ያለ ፍቅር ያለአንድነት ማንኛውም ነገር አይታናም አይጸናም እነዚህ ሁሉ የሌሉት ሰውም ሃይማኖት አለኝ ቢልም ሊጠቅመው አይችልም በኑሮው በኩል አይስተካከልም ስለ ዚህ በዚሁ በአዲሱ ዓመት ሃይማኖታችንን ጠብቀን ፍቅርና ሰላምን ይዘን ሀገራችንን በሥራ ለማበልጸግ እንድንችል በእውነት ታጥቀን ለሥራ እንነሣ ቤተ ክርስቲያናችንም ማንም ሰው በሥራው በድካሙ እንጀራውን እንዲበላ በእምነቱ በሃይማኖቱ እንዲጸና የዘወትር ጸሎትዋና ምኞትዋ ነው ።

ልዑል እግዚአብሔር በዓሉን የደስታ በዓል ያድርግልን

ሀገራችን ኢትዮጵያን በነፃነትዋ በአንድነትዋ ያጽናልን ፤

ዘመኑ የሰላም የበረከት የረድኤት የጸጋ የጤንነት ዘመን ያድርግልን ።





www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት በከፍተኛ ድምቀት ተከበረ

አምስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም በመላው የቤተ ክርስቲያኒቱ እምነት ተከታይ ተወካዮች በከፍተኛ ድምፅ ተመርጠው እሁድ ሐምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥርዓተ ሢመቱ በከፍተኛ መንፈሳዊ ሥርዓት ተከናውኖአል ።

ስለበዓሉ አከባበር በወጣው መርሐ ግብር መሠረት በዋዜማው ሐምሌ ፬ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ ከምሽቱ ፬ ሰዓት ጀምሮ ስለበዓሉ ክብር በካቴድራሉ ማኅሌት ተቁሞ ስብሐተ እግዚአብሔር ሲደርስ አድሯል ።

ከሌሊቱ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች ፤ ልብሰ ተክህኖ የቅዱስነታቸውን መድረስ ሲጠባበቁ የነበሩት ቀሳውስትና ዲያቆናት የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ተማሪዎች በብፁዕ አቡነ ኒቆዲሞስ የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ መሪነት የወርቅ መስቀልና ወንጌል ዘወርቅ በመያዝ «ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ፣ ባረክናክሙ እምቤተ




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በበዓለ ሢመቱ ዕለት በዐውደ ምሕረቱ ላይ ቃለ በረከት ሲያሰሙ

እግዚአብሔር » የሚለውን መዝሙር በጣዕመ ዜማ እየ ዘመሩ አቀባበል አድርገውላቸዋል

በዚሁ ጊዜ ካቴድራሉና የሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ለአምስት ደቂቃ ያህል የደወል ድምፅ በማሰማት ለአዲሱ ፓትርያርክ ደስታቸውን ገልጸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩም ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ገብተው ጸሎት ካደረሱ በኋላ በብፁዓን ሊቃነጳጳሳት መሪነት በሦስቱም መቅደሶች ሥርዓተ ቅዳሴው ተጀምሮ ኪዳን እንደደረሰ ወደ ተዘጋጀላቸው የክብር ቦታ እም

የለበሱ ቀሳውስትና ዲያቆናት በካቴድራሉ ዓውደ ምህረት የተመደበላቸውን ሥፍራ ይዘው የቅዱስነታቸውን መምጣት በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ በሥርዓተ ሢመቱ አፈጻጸም ላይ ለመገኘት ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እስከ ንጋቱ ፲፪ ሰዓት ከሩብ ደርሰው የተመደበላቸውን ስፍራ ይዘዋል ።

ከዚያም ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ሆነው ከጥዋቱ ፩ ሰዓት ላይ ከካቴድራሉ ሲደርሱ

የብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ ሥርዓተ ሢመት የተፈጸመው የተለያዩ የውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ተወካዮች ፣ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የሽግግር መንግሥቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ተወካይ ፣ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤትና የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ተወካዮች ሚንስትሮች፣አምባሳደሮች ፣ ከፍተኛ የሀገር ሹማግሌዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምዕመናን ፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና ፣ ካህናት በተገኙበት ነው ።



ርተው ሢመተ ፓትርያርክናው ደረጃ በደረጃ ተከናውኗል ።

ለሥርዓተ ሢመቱ የተመደቡ ፲፫ ሊቃነ ጳጳሳት የሕንዱን ሊቀ ጳጳስ አቡነ ግሪጎርዮን ጨምሮ የሊጦን ልዩ ልዩ ክፍሎችን በንባብ አድርሰዋል ። ።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳስ የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የበላይ ኃላፊ ፤

ከዚያም ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል» አክሊለ ጽድቅ ዘየአስየከ እግዚአብሔር የሚለውን ጸሎት አድርሰው እንደመጀመሪያው ሁለት ሦስት አበው ሊቃነ ጳጳሳት የፓትርያርክናውን አክሊል በቅዱስነታቸው ራስ ላይ አስቀምጠዋል ።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ «መጠወኒ ኅሪተ ወርቅ ፤ ዘመጠነ በትር ወይቤለኒ በትር ዘእግዚአብሔር » የሚለውን ጸሎት አድርሰው ከሦስት አበው ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ሆነው አርዌ ብርቱንና የወርቅ መስቀሉን ሰጥተዋል ።

በየአንዳንዱ ሥነ ሥርዓት ጊዜ በበዓሉ ላይ የተገኙት ሁሉ ይደልዎ ፤ ይደልዎ ፤ ይገባዋል፤ ይገባዋል ፤ እያሉ ደስታቸውን በከፍተኛ ስሜት የገለጹ ሲሆን እንዲሁም ግሪካውያኑና የውጭ አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች በግሪክኛ «አኪዖስ ፤ አኪዖስ በማለት ፡ደስታቸውን ገልጸዋል።

የግሪክኛው አኪዖስም ይገባባዋል ማለት ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሃይማኖት አባትነቱን ተረክበው የፓትርያርክነቱን ኃላፊነት ከተቀበሉ

በኋላ የሚከተለውን ቃል በማሰማት በጸሎተ ሃይማኖት ቃለ መሐላ ፈጽመዋል ።

ቅዱስነታቸው የገቡት ቃለ ሃይማኖት ሙሉ ቃል ።

## ቃለ ሃይማኖት (መሐላ)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ሎቱ ክብር ወስብሐት ወላዕሌነ ሣህል ወምሕረት ለዓለመ ዓለም አሜን ።

ካለፈው ጊዜ ይልቅ በዚህች ቅጽበት የእግዚአብሔር ኃይልና ረድኤት በተለይ የሚያስፈልገኝ መሆኑ ስለሚሰማኝ አባቶቻችን ረድቶ እኛንም ደግፎ እስከ ዛሬ ያደረሰ አምላክ ሁሉን በሚችል ሥልጣኑ ይመራኝ ዘንድ ሕሊናዬን በሙሉ ለእርሱ እሰጣለሁ ።

በመጀመሪያ ጸጋውን በሚያድልባቸው ምሥጢራት እንዳገለግል መጠን በሌለው ቸርነቱ ስለፈቀደልኝ በአንድነትና በሦስትነት ለሚመሰገን እግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ።

አሁን ደግሞ እርሱ መሥርቶ እርሱ ራሱ የሚመራትን የኢትዮጵያ ቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሆተ ክርስቲያንን በፓትርርክነት እንዳገለግል በማይገመት ፍቅሩና ጸጋው ጠራኝ ።

ወገኖቼ ሆይ ይህ ጥሪ ከባድ ኃላፊነት ያለበት ጥሪ መሆኑን ስለምገነዘብ ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር አምላክ በሥራዬ ሁሉ እንዲረዳኝና እንዲመራኝ እጸልያለሁ ።

የሰጠኝንም መንፈሳዊ ተግባር በሚቻለኝ ሁሉ በሱ ፈቃድ መሠረት ለመፈጸምና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ያበረታኝ ዘንድ ሁላችሁም በጸጋው ዘሩን ፊትበምታደርጉት ጸሎት ሁሉ ያለማቋረጥ እንድታስታውሱኝ እለምናችኋለሁ ።

የጸሎታችሁንም ርዳታ በምጠይቅበት ጊዜ ከሁላችሁም ጋር አብሬ ስለምካፈለው በእግዚአብሔር ጸጋ ልጠብቀው ላስጠብቀውና ላስፋፋው ስለሚገባ እምነት ምስክርነትመስጠት መልካም ዕድል ሆኖ ታይቶኛል።

የቤተ ክርስቲያናችን እምነት በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት በሃይማኖት ቀኖናዎች የተወሰነ ነው እነዚህም ፤

— ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው የወሰኗቸው ቀኖናዎች ፤

— «ወልድ ፍጡር» የሚል የአርዮስ ትምህርት በተወገዘበት በ፫፻፳፭ ዓ/ም በኒቅያ ጉባኤ ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሊቃውንት አበው የወሰኗቸው ቀኖናዎች ።

— «መንፈስ ቅዱስ ሕፀፅ » የሚል የመቅዶንዮስ ትምህርት በተወገዘበት በ፫፻፹፩ ዓ ም በቁስጥንጥንያ ጉባኤ፩፻፶ሊቃውንት የወሰኗቸው ቀኖናዎች ።

— «ክርስቶስ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ነው» የሚለው የንስጥሮሳውያን ትምህርት በተወገዘበት በ፬፻፴፩ ዓ/ም በኤፌሶን የተሰበሰቡት ሁለት መቶ አበው የወሰኑአቸው ቀኖናዎች ናቸው።ቤተ ክርስቲያናችን እነዚህን ቀኖናዎች ተቀብላለች።

በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት እየተመሩ ያስተማሩትን የእነዚህን የቅዱሳን አበው ሲኖዶሶች ውሳኔና የተከታዮቻቸውንም የተቀደሰ ሥርዓት በመከተል አንድ አምላክ በምታስኝበቅድስትሥላሴ ያለኝን እምነት እመሰክራለሁ

እግዚአብሔር አንድ ነው እሱም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላል አብ ፍጹም አምላክ ነው ። ወልድ ፍጹም አምላክ ነው ። መንፈስ ቅዱስም ፍጹም አምላክ ነው ። ግን አንድ አም



www.ethiopianorthodox.org

ላከ ይባላል እንጂ ሦስት አማልክት አይባልም ።

እግዚአብሔር በአካል በስም በግብር ሦስት ነው በባሕርይ በሕልውና በፈቃድ በመለኮት አንድ ነው በግብርም ሦስት ነው ስንል በወላዲነትና አሥራፂነት በተወላዲነት በሠራፂነት ነው አንድነቱንና ሦስትነቱን አምነን እናመልከዋለን ። አንዲት ስግደት እናቀርብለታለን ። አንድነት በሦስትነት ሦስትነትም በአንድነት አለ ።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት በመለኮት አንድ ናቸው ። አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸው ። ያለትድምርት ሦስት ያለ መለያየት አንድ ናቸው ። አብ ይባላል እንጂ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይባልም ወልድም ወልድ ይባላል እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ አይባልም መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ይባላል እንጂ አብ ወልድ አይባልም ።

ከሥላሴ አንድ እግዚአብሔር ወልድ ለድኅነታችን ሲል ከሰማይ መውረዱን ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆኖ መወለዱን አምናለሁ እመሰክራለሁ ። ከድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ የነሳውን ሥጋ ከራሱ ጋር አዋሕዶ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር በባሕርይ አንድ የሆነው ዘለዓለማዊው እግዚአብሔር ወልድ እንደኛ ፍጹም ሰው ሆነ የእኛንም ባሕርይ ሳይለወጥ ነሣ ሳይለወጥ ሳይቀላቀል ይለያይ ሳይከፋፈል እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋውንና ለባዊት ነፍስ ከራሱ ጋር

ባአንድ አካል በአንድ ባሕርይ አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ። ሰውም ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው ። በሱም የመለኮት ባሕርይና የሥጋ ባሕርይ ያለመለያየትና ያለመከፋፈል አንድ ሆነዋል ።

ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው አንድ አካል አንድ ባሕርይ ስንል «አንድ ማለት የሚያስረዳው ፍጹም ተዋሕዶን ነው እንጂ መናፍቃን እንደሚሉት መጠፋፋትንየሚያሳይ አይደለም

ስለዚህ ክርስቶስ በምድር ሳለ የተናገራቸው ቃላትም ሆኑ ያደረጋቸው ተአምራት ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁሉት ባሕርይ አንድ ባሕርይ መሆኑን ይገልጣሉ ።

ቅዱስ አትናቴዎስ እንደተናገረው ሰው አምላክ ይሆን ዘንድ አምላክ ሰው ሆነ ። እሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። በዚህም ቸርነት ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ድኅነት ፈጸመ ። በአዳኝነቱም ሰውን ከእግዚአብሔር አብ ጋር አስታርቆ ለሰው የእግዚአብሔርን ልጅነት እንደገና መለሰለት ሰው በሚመጣው ዓለም የዘለዓለም ሕይወትን ለማግኘት በተስፋና በፍቅር እንዲኖር አስቻለው ። ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት በስተቀር የሰውነትን ሥራ እየሠራ በምድር ኖረ ።

ነገር ግን ይህ የሆነው ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ ነው ። የሰይጣንን ኃይል ድል ለመንሣት ክርስቶስ ስለ እኛ በመስቀል ላይ ሞተ በሦስተኛውም ቀን በአሸናፊነት ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ። ክርስቶስ በትንሣኤው ያስገኘው ድል በመላው ዓለም ለሚገኘው የሰው ልጅ ሁሉ ነው ። ዘርና ወገን ሳይለይ ድኅነቱ ለሁሉም ተሰጥቷል ።

የተሰቀለውና ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት በመስቀሉና በትንሣኤው ያስገኘው ድኅነት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለመላው ዓለም ይገለጥ ዘንድ ነው ። ክርስቶስ ሁል ጊዜ በቤተ ክርስቲያን አድሮ ይኖራል ። የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስም ሁል ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን ሕይወትና ተግባር ይመራል ። ቤተ ክርስቲያን በዓለም ሁሉ ያለች ማኅበረ ክርስቲያን ናት ።

የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እንደመሆኔ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት በእግዚአብሔር ጸጋና አጋዥነት ጠብቄና አስጠብቄ እኖራለሁ ።

<u>የተከበራችሁ ወገኖቼ</u> የኦርቶዶክስ ተዋሕዶን እምነትና ሥርዓት እስከ ሕይወቴ መጨረሻ ድረስ የምጠብቅ መሆኔንና በእለኝ ዓቅምና ችሎታ ለምእመናን ደኅነት ይሆን ዘንድ የማስተምር መሆኔን በልዑል እግዚአብሔር ና በዚህ ጉባኤ ፊት ቆሜ አረጋግጣለሁ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የሚቃወም (የሚጻረር) ማናቸውንም ትምህርት እቃወማለሁ ። ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን እንዲወገድም እጥራለሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥነ ሥርዓትና ሥነ ምግባር ተጠብቀው የሚኖሩባቸው የቤተ ክርስቲያን ሕግጋትና ትእዛዝት በምእመናን ተጠብቀው እንዲኖሩ አደርጋለሁ ።

በአለ ሕይወቴ ሁሉ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሆን በመላው ኢትዮጵያ አህጉረ ስብከት በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በካህናትና ምእመናን መካከል ፍቅር አንድነት እንዲጠነክር አደርጋለሁ።

በአምስቱ እኅት የመካከለኛው ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ለብዙ ዘመናት የኖረው አንድነትና አብሮ መሥራት እንዲጠነክርና እንዲስፋፋ ያለንን ግንኙነት በበለጠ ለማጠንከርና ለመጠበቅ እጥራለሁ። ከሌሎችም ወዳጅ አብያተ ክርስቲያናት ጋር መረዳዳትና አብሮ መሥራት እንዲስፋፋ በሚቻለኝ ሁሉ እጥራለሁ ።

ከአለፈው ጊዜ ይልቅ ይህ የምንኖርበት ዘመን የክርስትናን እምነት ለማዳከም ልዩ ልዩ ዓለማዊ ኃይል የተነሣሣበት ጊዜ ነው በእናንተ ጸሎትና ርዳታ ይህን ፈተና ለመቋቋም በመላው ዓለም ካሉት ክርስቲያኖች ጋር በመተባበር የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለመጠበቅ በሚበጅ መንገድ የማይቋረጥ ጥረት አደርጋለሁ ።

ለዓለም ሁሉ ሰላም እንዲሰፍን ተንኮልና ክፋት እንዲጠፋና እንዲሁም በሰዎች መካከል የዘርና የወገን ልዩነት እንዲወገድ በተቻለኝ ሁሉ እጥራለሁ ለዚህም የልዑል እግዚአብሔርን ርዳታ እለምናለሁ ።

ምእመናን ወገኖቼ በአንድነት በሦስትነት የሚመሰገን እግዚአብሔር ሁላችሁን ይባርካችሁ ። በሥራችሁ ሁሉ ይምራችሁ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም፣ የመላእክት፣የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣የሰማዕታትና የቅዱሳን ሁሉ በረከትና ረድኤት ከሁላችሁ‧ጋርይሁንአሜን ። በማለት ቃለ ሃይማኖቱን ፈጽመዋል

ቀጥሎም «አ ሥሉስ ቅዱስ» ተብሎ «መሐለ እግዚአብሔር ወኢይኔስሀ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ» የሚለው ምስባክ ከተሰበከ በኋላ ቅዱስ ፓትርያርኩ ከዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲ አንብበው ፍሬ ቅዳሴውን መርተዋል ።

ጸሎተ ቅዳሴው እንዳበቃ የክብር እንግዶች በዐውደ ምሕረቱ ቦታ ቦታቸውን እንደያዙ ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ሆነው ወደ ዐውደ ምሕረቱ በማምራት ከተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር ተቀምጠዋል ።

ወዲያው በዐውደ ምህረቱ የሚከናወነው ሥነ ሥርዓት ተጀምሮ ሦስት መዘምራን ከቅዱስነታቸው ፊት ቀርበው ለበዓሉ የተዘጋጀውን ግሥ ከቃኙ በኋላ ግራ ቀኝ የተሠለፉት መዘምራን ለ፳ ደቂቃ ያህል በደማቅ ሁኔታ አሸብሽበው እንዳበቁ ስለበዓሉ የተዘጋጁ መጽሔቶችና ጋዜጦች ታድለዋል ።

ወያዲው ደግሞ በቅኔ ሞያቸው የታወቁት ፭ ሊቃውንት በቅዱስነታቸው ፊት ቀርበው መወድስ ቅኔ አቦርከተዋል ። ቀጥሎም የታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን የሰንበት መዘምራን መዝሙር ካሰሙ በኋላ ብፁዕ ዶክተር አቡነ ገሪማ የኢሉባቦርና የጋንቤላ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ፣ የአምስተኛው ፓትርያርክ አስመራጭ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ቅዱስ ሲኖዶስን በመወከል የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል ።

«ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር »

«ኢትዮጵያ እጆቻን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» ይላል ነቢዩ መዝ ፣ ፷፯ ፣ ፴፩) ይህም የተዘመረው በነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ሲሆን ጊዜውም ወደ ሦስትሺ(፫ሺ)ዘመንየተጠጋነው።

ኢትዮጵያ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ በግዮን ወይንም <u>በዐባይ</u> ሸለቆ ዙሪያ በቀይ ባሕር አካባቢ ጥንታዊ የሃይማኖት ሥልጣኔ ካላቸው አህጉር አንዷ መሆኗ በቅዱሳት መጻሕፍትና በጥንታውያን የታሪክ ሰነዶች የተረጋገጠ ነው ።

ኢትዮጵያ ደጋ ፣ ወይና ደጋ ፣ ቆላማ የአየር ጠባይ ያላት ሀገር ስትሆን በተፈጥሮ አቀማመጥም «ቀርነ አፍሪካ» የአፍሪቃ ቀንድ እየተባለች ትጠራለች ።

ሦስት ሺህ ዘመን ያህል ወደ ኋላ መልስ ብለን የዓለምን ታሪክ ብንመለከት በዚያ ዘመን በዓለም ዙሪያ ታውቃ ፣ ከፍተኛ እድገትን አግኝታ፣ወዳጅነትን መሥርታ በመረዳዳትና በመቀራረብ ትኖር የነበረው በመካከለኛውና በቅርብ ምሥራቅ ከነበሩት ጥንታውያን አህጉር ጋር እንደነበር ከታሪክእንረዳለን።በዚያንዘመን የሠለጠነ ዓለም ይባል የነበረውም ይኸው አካባቢ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ሉቃ ፣ ፪) ።

ለዚህም መቀራረብና መወዳጀት መነሻውና መድረሻው የሃይማኖት ታሪክ መሆኑን እናውቃለን ።

የዛሬው ሢመተ ፓትርያርክ በዓል አከባበራችንም መነሻውና መድረሻው የኢትዮጵያ እጆች ወደ እግዚአብሔር መዘርጋቱ ነው ።

ኢትዮጵያ ትምሕርቱን፣ ታአምራቱን፣ ጥበቡን ያገኘችው ከሃይማኖቷ ነው የዓለም ሥልጣኔ የተገኘው ከውሀ ዳርቻ ነው ይባላል ።

እኛም እንደዐባይና እንደቀይ ባሕር ያለ ውሀ ቢኖረንም የኛ ሥልጣኔ ግን የተገኘው ከውሀ ዳርቻ ሳይሆን ከሃይማኖት ነው ።





www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በበዓለ ሢመቱ በዐውደ ምሕረቱ ላይ

«የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነውና መዝ ፩፻፲፩መቶ፲(፲፩)፡ እግዚአብሔር የሌለው ሀገር ለማንም ለምንም የማይበገር ሥልጣንና ኃይል ቢኖረውም ጥበቡና ኃይሉሁሉ ወገንና ሀገርን የሚገነባ አይሆንም ።

የኢትዮጵያ እድገት የተገነባው የኢትዮጵያዊነት ዓይነተኛ መለያ በሆነው እጆችን ወደ እግዚአብሔር በመዘርጋት ነው ከዚህም ጋር በዶጋውም ሆነ በወይና ደጋው እንዲሁም በቆላማው የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ፤ ሁሉ በነጻነቱ ተጋድሎ በሃይማኖት በምግባር ፤ በባህል ፤ በቋንቋ ፤ በመተሳሰብ ተቀራርቦ በፍቅር አንድነት መኖሩ ነው ።

ከሃይማኖት በመነጨ ያስተዳደር ዘይቤም ለብዙ ዘመናት ሕዝቡን በሃይማኖት አስተባብሮና አስተሳስሮ ለነጻነቱና ለአንድነቱ እንዲታገል ብዙ ድካምና ጥረት ተደርጓል ። ከዚህም አሠራር የተገኘው ውጤት ሀገር የዳበረበት ዳር ድንበር የከበረበት ፤ ወገን የኮራበት ፤ ነጻነት የተጠበቀበት ነው ።

የዚሁ ሁሉ ታሪካዊና ማኅበራዊ አሠራር መሠረትና ባለቤት የኢትዮጵያ እጆች ወደ እግዚአብሔር መዘርጋቱ ነው ። ይህም እጆችን ወደ እግዚአብሔር መዘርጋት በኢትዮጵያና በእግዚአብሔር ፤ በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያውያን መካከል ፤ ጸንቶ የነበረ ፡ ያለ የሚኖር ቃልኪዳን ነው ።

ኢትዮጵያ ከክርስትናው ታሪክ በፊት በሙሴ መጻሕፍት ትመራ እንደነበርና የክርስትናው ታሪክም ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአንደኛው መቶ ዓመት በ፴፬ ዓ ም በሐዋርያት ዘመን ሲሆን (ዮሐ፡ ፰፡ ፳፮-፴ ) ኤጲስ ቆጶስ ተሾሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ ህልውና ታውቆ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም የተጀመረውም በ፬ኛው መቶ ዓመት መሆኑን ታሪክ ያስረዳናል ።

እንደዚህም ስንል የኢትዮጵያ ታሪክ የቤተ ክርስቲያኗ ፤የቤተ ክርስቲያኗም ታሪክ የኢትዮጵያ መሆኑን እናውቃለን ። ሁለቱ ከተነጣጠሉ ግን ታሪክ የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው ።

ቤተ ክርስቲያናችን ወይንም ሀገራችን በዚህ ረጅም የታሪክ ዘመኗ የመውደቅና የመነሣት ታሪክ አጋጥሟታል ። ስለዚህም ከዛሬው በዓላችን ጋር ግንኙነት ያለውን በቅደም ተከተል ባጭሩ እንደሚከተለው ለማስታወስ እንሞክራለን ።

ከታሪካችን እንደምንረዳው ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ስሜት የነበረው ንጉሥ ሐርቤ (ገብረ ማርያም)የኢትዮጵያን ስፋት የሕዝቡን ብዛት በመመልከት መላ ኢትዮጵያን ዙረውና ተዘዋውረው የሚያስተምሩ ሰባት ኢትዮጵያውያን ቆሞሳት ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው እንዲሾሙለት የካይሮውን ቅዱስ ሲኖዶስ ጠይቆ ነበር ይህም የሕገ ሥጋ አሠራር ያለበት በመሆኑ የካይሮው ቅዱስ ሲኖዶስ መልስ አልሰጠም ። ራስን የመቻል ይህን የመሰለ ሐሳብ በዚያ በጨለማው ዘመን ማቅረብ በተጠያቂውም ፤ ሆነ በጠያቂው በሁለቱም ወገን እንደበደለኛ የሚያስቆጥር ነበር ንጉሥ ሐርቤ በ፲፩ኛው መቶ ዓመት ያቀረበው ጥያቄ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በ፳ኛው መቶ ዓመት በኛ ዘመን ሁሉም ተፈጽሞ ሲታይ ይህን ያዩ ዓይኖች የሰሙም ጆሮች ብፁዓን ናቸው እንላለን ።

ከጊዜ በኋላም በ፲፱ኛው መቶ አጋማሽ አጼ ዮሐንስ ወንጌልን በሰፊው በኢትዮጵያ ለማስተማር እንዲያመችና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም በራሷ ልጆች እንድትመራና እ ን ድ ትባረክ ከአጼ ዮሐንስ በፊት በ፲፭ኛው መቶ ዓመት በንጉሥ ሐርቤ ዘመነ መንግሥት ተጠይቆ ሳይሳካ የቀረውን እንደገና በማንሳት ኢትዮጵያውያን ቆሞሳት ጳጳሳት ሆነው እንዲሾሙ የካይሮውን ቅ/ሲኖዶስ ጠይቀው ነበር ነገር ግን ጥያቄያቸው መልስ ባለማግኘቱ ስለዚሁ ጉዳይ በቁስጥንጥንያ ከሚገኘው ከአርመን ፓትርያርክ ጋር መጻጻፍ ጀምረው እንደነበር ታሪካችን ይነግረናል ። ይሁንና «ማርቆስ አባታችን ፤ እስክንድርያ እናታችን» ከሚለው ትውፊት ርቆ መሄድ ሕዝበ ክርስቲያኑን ቅር የሚያሰኝ መስሎ ስለታያቸው ከችግሩ እንጻር አጼ ዮሐንስ አራት ግብጻውያን መነኮሳት ጳጳሳት ሆነው እንዲላኩላቸው የእስክንድርያውን ፓትርያርክ ጠየቁ ። የካይሮው ቅዱስ ሲኖዶስም አራት ግብጻውያን መነኮሳትን ኤጲስ ቆጶሳት አድርጐ ሾሞ ወደ ኢትዮጵያ እንደላካቸው ታሪክ ይነግረናል ።

በዚህ ዓይነት የታሪክ ሂደት ቤ/ ክርስቲያናችን እስከ፳ያኛው መቶ ዓመት ተጉዛለች ። «ወሰብአ ኢትዮጵያ ኢይሢሙ ሊቀ እማዕምራኒሆሙ» የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቻቸው ፤ ቸር ጠባቂ አባት አይሹሙ የሚል አንቀጽ በ፫፻፳፭ ዓ/ም በኒቅያ የተሰበሰቡት ሦስት መቶ አሥራ ስምንት (፫፻፲፰ ቅዱሳን አበው እንደወሰኑ አድርገው በማስመሰል የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ለእይታ አቅርበውታል ።

ይህም ሥርዋፅ ከጊዜ በኋላ በሰባተኛው መቶ ዓመት ሰውሰውኛውን የተጣፈ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለ፩ሺህ፮፻ (ለአንድ ሺ ስድስት መቶ) ዘመን ያህል በግብጻውያን መነኮሳት ስትመራ ቆይታ ፈቃደ እግዚአብሔር ሲሆን «ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር» ነውና በ፲፱፻፳፩ና በ፲፱፻፳፪ ዓ/ም ለመጀመሪያ ጊዜ አምስት ኢትዮጵያውያን ቆሞሳት በካይሮና በአዲስ አበባ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ ይህም በቤተ ክርስቲያናችን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የከፈተ ነው ። ሕገ ሥጋ የሆነው ሥርዋጽም በዚህ ጊዜ የተደመሰሰ ሆኗል ።

ይሁንና እውነትን ለመናገር ከሆነ ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው ከግብጽ ሐዋርያ ተልኮላት ሳይሆን በመጀመሪያ እንደተገለጠው የክርስትናው ታሪክ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአንደኛው መቶ ዓመት በ፴፬ ዓ/ም በሐዋርያት ዘመን ነው ብለናል ግን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ከኢትዮጵያ ወደግብጽ ተልኮ ጵጵስናውን የተቀተበለው በእስክንድርያ ከቅዱስ አትናቴዎስ ነው የፍሬ ምናጦስ ሐረገ ትውልድም በሶርያ ይኖር የነበር ግሪክ ነው ። ጵጵስናን ከእስክንድርያ ማምጣትም የክርስትናውን ታሪክ ከግብጽ ማምጣት አለመሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው ። ሐዋርያም የሚባለው ሄዶ ያስተማረ ነው ። ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ እንዳለች ፋሽስት ኢጣሊያ ወደ ሀገራችን ገብቶ ወረራውን እንደቀጠለ በጊዜው በአዲስ አበባ የነበሩት ግብጻውያን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ቄርሎስ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት በድንገት ወደ ሮም ተጓዙ ።

በሮምም አቡነ ቄርሎስ የጠየቁት ባለመሳካቱ ተቆጥተው መንጋውን ያለጠባቂ በትነው ወደ ኢትዮጵያ አለመመለሳቸውን ገልጸው በሀገራቸው ካይሮ ቀሩ ።

ይሁንና በ፲፱፻፳፭ ዓ/ም የተጀመረው እቅድ ወይንም በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ የተከፈተው አዲስ ምዕራፍ በፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ከ፲፱፻፳፰ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ድረስ ተቋረጠ ። በነዚህም አምስት የወረራ ፤ የመከራ ፤ የግድያ ዓመታት በቤተ ክርስቲያናችን አሠራር በግብጽና በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ኃላፊዎች መካከል አለመጣጣም ነበር ።

ከ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ወዲህ በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤና በካይሮ ቅዱስ ሲኖዶስ መካከል ስለተፈጠረው ቅራኔ ሰፊ ውይይት ተደርጎ ወደ አንድ ስምምነት በመደረሱ በ፲፱፻፵ ዓ/ም አምስት ኢትዮጵያውያን ቆሞሳት በካይሮ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ ። በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም የሊቀ ጵጵስናው ፈቃድ ተገኘ ። ይህም የሆነው ከግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ዕረፍት በኋላ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤ/ክርስቲያን በ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ከሊቀ ጵጵስና ወደ ፓትርያርክነት መስመር ከፍ አለች ።

ይህም በሀገራችንና በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ከፍተኛ መንፈሳዊ ዕድገት የታየበት ነው

በዛሬው ዕለት በከፍተኛ ደረጃ የምናከብረው የአምስተኛው ፓትርያርክ በዓለ ሢመትም የዚህ ሁሉ የታሪክ ጉዞ ውጤት ነው ።

ይህ ዛሬ ተሰብስበን የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት የምናከብረው በዓለ ሢመት ቤተ ክህነቱና ቤተ መንግሥቱ በጣም ራ ወደካይሮ በመጓዝ በብዙ ምልልስና ድካም የተገኘ ነው ። በመጀመሪያ ጵጵስናውን ከዚያም ሊቀ ጵጵስናውን በይቀጥላልም ፓትርያርክነቱን በማግኘት የተከፈለው መሥዋዕትነት ቀላል አልነበረም ።

ቤተ እሥኤል ከ፬፻ የባርነትዘመን ከግብጽ የባርነት ኑሮ በእግዚአብሔር ቸርነት በመልአኩ ተራዳኢነት በታላቁ ሙሴ መሪነትነጻ እንደወጣ ፤ የኛም ቤተ ክርስቲያን ከ፩ሺህ፮፻ ዘመናት የፈቃድ ተገዢነት ነጻ የወጣችበትን በማ





www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በበዓለ ሢመቱ ዕለት በዐውደ ምሕረቱ ላይ

ሰብ የአምስተኛውን ፓትርያርክ በዓለ ሢመት በታላቅ ደስታና ስሜት ነው የምናከብረው ።

የኢትዮጵያውያንን እጆች ተመልክቶ ቅዱስነትዎን በዚህ ታላቅ መንበር ላይ ያስቀመጠ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን ።

ቅዱሳን ነቢያት እነ ኤርምያስ ፤ እነሕዝቅኤል ፤ እነዳንኤል እነዕዝራ እነ አቤሜሌክና ሌሎችም ነቢያት ስለርስታቸው ማእከለ ምድር ኢየሩሳሌም መጥፋት ፤ ስለወገናቸው ስደት ፤ ስለቤተ መቅደሳቸው መፍረስ ስለሕጋቸው መደምሰስ ያዘኑ ፤ ያለቀሱ እንደነበር ሁሉ ቅዱስነትዎም ለሰባት ዓመታት ያህል በእሥር ቤት ፤ ከዚያም በስደት ሆነው ስለሀገራችን ኢትዮጵያ መደኽየት ፤ መራቆት ፤ መምከን ፤ ስለኢትዮጵያውያን ወገኖች በግፍ መገደል ፤ መሰደድ ፤ ስለሃይማኖትና ምግባር መዳከም ፤ እያዘኑ እያለቀሱ ቀኖና ይዘው ቆይተዋል ።

ከዚህም ጋር በእስር ቤት ከርስዎ ጋር የነበሩትንም በፍቅር አንድነት በማጽናናት በውጭ ሀገር በስደት የሚኖሩትንም ወገኖች በምግባር በሃይማኖት ጸንተው እንዲኖሩ በመምከር በማስተማር የቸር ጠባቂነት ግዴታዎን የፈጸሙ መሆንዎን ከተገልጋዮቹ መረዳት ችለናል ። ቅዱስነትዎ የትምህርቱን ፣የእስራቱን ፤ የስደቱንና የመሳሰለውን ፈተና ሁሉ በትእግሥት አልፈው ከዚህ መድረስዎ ታላቅ ገድል ነው ።

«ወአንበርከ አክሊለ ዲበ ርእሱ ዘእምዕንቁ ክቡር ከክበረ ዕንቁ የሆነ አክሊልን በራሱ ላይ አኖርህ « ይላል ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት (መዝ ፳፩)

ይህም አክሊል በቅዱስነትዎ ራስ ላይ የሚታየው ነው ።

የኢትዮጵያ ቤ/ክርስቲያን ስለ ሁሉም ደኅንነት በምትጸልየው ጸሎትና ለፈጣሪዋ በምታቀርበው መሥዋዕት እግዚአብሔር ጸሎቷንና መሥዋዕቷን በመቀበል በዘረጋችው እጅዋ የድል አክሊልን አሲዟታል ።

«እነግረክሙ አኃዊነ ጸጋ እግዚአብሔር ዘተውህበ ለቤተ ክርስቲያን» ዘመቄዶንያ» ወንድሞቻችን በመቄዶንያ ላሉችው ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ እነግራችኋለሁ» (፪ቆሮ ፰-፩) በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረውን በማሰብ በዛሬው ዕለት ለቤተ ክርስቲያናችን የተሰጠውን ጸጋና ክብር በዚህ ዐውደ ምሕረት ለምትገኙት ሁሉ ስንናገር ደስ ይለናል ።

ከዚህም ጋር ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስና ጳውሎስ በኔሮን ቄሣር ዘመነ መንግሥት ለአንድ ዓላማ ወደሮም ሐዋርያዊ ጉዞ አድርገው ፤ በዚያ ተገናኝተው ክርስቶስን ማስተማራቸው በአማልክት አምላኪዎች ዘንድ በደል ሆኖ በመገኘቱ በሰማዕትነት ያረፉበትን የዛሬውን ዕለት ከዚህ ታላቅ በዓለ ሢመት ጋር ቤተ ክርስቲያናችን ታከብራለች ። ስለዚህም የዛሬው በዓላችን የተደራረበ ነው ። ይህም የሰማዕትነት ዕረፍት በትናትናው ዕለት ከአከበርነው ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሥርዓተ ቀብር ጋር ተመሳሳይ ነው ።

ቅዱስነትዎም ባለፉት የመከራ ዓመታት ሞቱን ሕይወት ፤ መራራውን ጣፋጭ ፤ ከባዱን ቀላል አድርገው መከራውን ሁሉ እንደተቀበሉት በዚያው ዓይነት በተሰጠው ኃላፊነት ቤተ ክርስቲያናችንን በፍቅር አድነት እንዲመሯት የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ እንዲሆን የዘወትር ጸሎታችን ነው ።



ከሩቅም ከቅርብም መጥታችሁ በዚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያናችንን ሢመተ ፓትርያርክበዓል ላይ የተገኛችሁትን ሁሉ በቅዱስ ሲኖዶስ ስም እናመሰግናለን ።

«እምይእዜሰ ይኩን ሰላም» በማለት ብፁዕ አቡነ ገሪማ ንግግራቸውን ደምድመዋል ።

ከዚያም የውጭ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ተወካዮች በቅዱስነታቸው ፊት በየተራ እየቀረቡ ንግግር አድርገዋል ።

በተለይም የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወካይ ብፁዕ አቡነ ግሪጎሪ በዓለም ዙሪያ ዘረኝነት አገሮችን እየናደ መሆኑንና ኢትዮጵያንም ይህ ችግር እንደሚያሰጋት በአጽንኦት ገልጸው ፤ ቅዱስ ፓትርያርኩን ከትምህርት ቤት ጀምሮ ስለሚያውቋቸው ሰዎችን በዘር እንደማይለዩ መስከረው ቤተ ክርስቲያኒቱና አገሪቱ ለአለፉት ዐሥራ አምስት አመታት ብዙ ችግሮች ቢገጥሟቸውም በእግዚአብሔር ርዳታ ማለፋቸውን ሁልጊዜም እሱ በመከራም ጊዜ እንደሚደርስላቸው አስረድተዋል ።

አያይዘውም አገራቸውና ቤተ ክርስቲያናቸው ፓትርያርኩን ተቀብሎ ለማስተናገድ ያላቸውን ጥልቅ ፍላጎት ገልጸው ፣ የሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ይጎበኙ ዘንድ ጥሪያቸውን አቅርበዋል ። ቀጥሎም የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትርን በመወከል በሢመተ በዓሉ ላይ የተገኙት አቶ መረሳ ዓለማየሁ ፣ ቅዱስነታቸው የአለፈውን የ፲፯ ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይዎት በትክክል እንደሚያውቁ በንግግራቸው ጠቁመው ፣ እየተደረገ ለአለው ሰላምና ዲሞክራሲ የማስፈን ጥረት የእሳቸው መመረጥ ድርሻ እንዳለው ገልጸዋል ። እንዲሁም የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ጆሴፍ ቺፔንዳና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ተወካይ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያንአንጋፋነትና ብዙ የሚጠበቅባት መሆኑን በመግለጥ ንግግር አድርገዋል ።

ሌሎችም የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ተወካዮች በቅዱስነታቸው መመረጥና በቤተ ክርስቲያናችን መልካም የሥራ ርምጃ የተሰማቸውን መንፈሳዊ ደስታ በየተራ ገልጸዋል ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘ ኢ ት ዮ ጵ ያ የምስጋና ንግግር አድርገዋል ። ቅዱስነታቸው ቀደም ብለው ደስታቸውን ለመግለጽ ንግግር ያደረጉ ሁሉ የሚያሳስባቸውን ጉዳይ በመጥቀስ እንዲያስቡበት የጠየቁአቸው መሆኑን አውስተው እሳቸው ከእነሱ የተለዩ እንዳልሆኑና በእርግጥም እንደሚያሳስባቸው ገልጸዋል ። «እንደ ሰውነታችን በሰባዊነት ተመርተን ፤ በዕለቱ በዓመቱ ውስጥ የምን ሠራውን እናቅዳለን ። የምን ሠራውን የሚወስነው እግዚአብሔር ነው። ወደ ሀገሬ የመጣሁት አገሬን አይቼ ለመመለስእንጂ ለመሾም አልነበረም ካሉ በኋላ እናት አገራችን ኢትዮጵያና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደሚወራረሱ የቤተ ክርስቲያን ታሪክከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ያለውን መጣመር ዘርዝረው አስረድተዋል ።

ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያውያን ላይ እጃቸውን ያለ እርኅራኄ እንዲያነሱ ያደረጋቸው በአባቶቻችን ጊዜ የነበረው ከእራስ ጥቅም ይልቅ ለሌላው ማሰብ ፤ ከእራስ በፊት የሌላውን ፍላጎት የማርካት ፈቃድ በመጓደሉ መሆኑን ገልጸዋል ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ኢትዮጵያውያን በዘር የማይለያዩ የኖህ የልጅ ልጆች መሆናቸውን ፤ ይህ ሕዝብ ከአንድ ቤተሰብ የተገኘ፤ ቤተ ሰብ እየበዛ ልጆች ጎጆ እየወጡ ሲሄዱ መንደር እየተመሠረተ ሀገርና ሕዝብ የሆነ መሆኑን አስረድተዋል ።

ጎላ ባለ ድምፅ «አንድነት ያለን ሕዝቦች ሆነን ለምን በአንድ አንሆንም ! ብለው ቅዱስነታቸው ወደ መሠረታዊ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በበዓለ ሢመቱ ዕለት በዐውደ ምሕረቱ ላይ






www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በበዓለ ሢመቱ ዕለት በዐውደ ምሕረቱ ላይ



አንድነታችን እንምጣሲሉ ጥሪ አቅርበዋል ።

ቤተ ክርስቲያን የህዝብ ፣ የሲኖዶስ አባላትም የሕዝብ መሆናቸውን፣ ጠቅሰው ከሕዝብ የተገኘ በእግዚአብሔር የተጠራ ፣ የተወሰኑትን ለማቀፍ፤ ሌሎችን ለማገለል መብት እንደሌለውና፣ለእሳቸው ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ወንድሞቻቸው ፤ እኅቶቻቸውና አባቶቻቸው መሆናቸውን ገልጸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ባለፉት ፲፯ ዓመታት የተፈጸሙ ደባዎች በሕዝብ መካከል መራራቅን ማስከተላቸውን ጠቁመው ይህ ቁስል እንዲድን ከሕዝብ ጋር አብረው እንደሚሙሁ አረጋግጠዋል ።

«እኔ ከሕዝብ የተለየሁ አይደለሁም እኔ የተመረጥሁት የተላኩትም በሕዝብ መካከል የመፈቃቀርን መንፈሳዊ እሳት ለማሟሟቅ ነው ። » ያሉት ቅዱስነታቸው ፣ የተጣለባቸውን መንፈሳዊ ኃላፊነት ፍሬ እንዲሰጥ ለማድረግለምዕመናን የንስሐጥሪ ሲያቀርቡ ጥሪውን በመቀበል ይቅር ፣ ለእ ግዚአብሔርተባብሎ ይቅርታ በማድረግ ፤ ለተቀደሰ ሥራ እንዲጥሩ የተቀደሰ ሥራ ለመሥራት ሁሉም እንዲተባበሩዋቸው ጥሪ አቅርበው ጸሎተ ቡራኬ ከሰጡ በኋላ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።





«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን»

በበዓታት ፣ በገዳማት ፣ በአድባራት አብያተ ክርስቲያናት ተወስናችሁ ፣ በጸሎት ፣ በትሕርምት የምትገኙ አበው ፤ በከተማ ፣ በገጠር ያላችሁ ፣ በእፍኝ ጥሬ ፣ በጥሪኝውኃተወስናችሁየእመቤታችንን በረከት ረድኤት ለማግኘት በጾም ፣ በጸሎት የስነበታችሁ ምእመናን ፤ በሀገር ውስጥና በዳር አገር ያላችሁ ክብረ ወሰንን ለማስከበር በየጠረፉ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ልዑል እግዚአብሔር እንኳን ለእመቤታችን በዓለ ዕርገት በሰላም አደረሳችሁ ።

## «ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል» ። (ሉቃ ፩ ፣ ፵፱ ፤)

እመቤታችን ዓለም ሳይፈጠር በሕሊና አምላክ እንደነበረች በቅዱሳት መጻሕፍት ታውቆአል ። አዳም በኃጢአት እንደወደቀም ፣ እግዚአብሔር አምላክ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎ የሰጠው ተስፋ እመቤታችንን ያመለክታል ። በዘመነ አበውም እመቤታችን በልዩ ልዩ ምሳሌ ስትነገር እንደኖረች ግልጽ ነው ። ከሙሴ ጀምሮ እስከ ዳዊት ከዚያም እስከ ልደተ ክርስቶ፣ ድረስ እመቤታችን በአምሳለ ሐመልማል ወነበልባል በተራራ ፣ በዋሻ ፣ በእምባ በደመና ፣ በድንኳን ፣ በድልድይ ፤ በመሰላል፣ በጽርሕና በመሳሰሉት ሁሉ ነቢያት ትንቢት ተናግረውላታል ።

በተለይም ነቢዩ ኢሳይያስ «ናሁ ድንግል ትጸንስ ፣ ወትወልድ ወልደ ወትሰምዮ አማኑኤል» እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች ብሎ በኃላና በተረዳ ስለእመቤታችን ተንብዮአል ። (ኢሳ ፯ ፣ ፲፬ ። ማቴ ፩ ፡ ፳፫ ። )

ነቢዩ ዳዊትም «እስመ ሐረያ እግዚአብሔር ለጽዮን ወአብደራ ከመትኩኖ ማኅደሮ» እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወዶአታልና ብሎአል ። (መዝ ፩፻፴፩ ፣ ፲፫) እንዲሁም «እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ ወብእሲ ተወልደ በውስቴታ» ሰው እናታችን ጽዮን ይላል ከሷም ወልደ እጓለ እመ ሕያው ክርስቶስ ተወለደ እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት ሲል በመጽሐፈ መዝሙሩ አስፍሮአል ። (መዝ ፹፮ ፣ ፭ ።)«ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል»ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ በማለትም በመንፈስ ትንቢት ተቃኝቶ ዘምሮላታል ። እመቤታችን ኢያቄምና ሐና ከሚባሉ ደጋግ ምእመናን ተወለደች በስዕለት ስለወለዱአትም ልክ በሦስት ዓመትዋ ለሊቃነ ካህናት አስረከብዋት ። የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ እመቤታችን መጥቶ ትጸንሽያለሽ ወንድ ልጅም ትወልጂያለሽ ብሎ አበሰራት ። (ገላትያ ፬ ፡ ፬ ። ) እመቤታችን ይህ እንዴት ይሆንልኛል ? ብላ መለሰችለት ። መልአኩም ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም እነሆ ኤልሳቤጥ በስተእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች ቢላት«ይሁንልኝ እንደቃልህም ይደረግልኝ» አለችው ።

እንደመልአኩ ብሥራትም እግዚአብሔር ወልድ በማኅፀነ ድንግል አደረ ። ከዚህ በኋላ እመቤታችን የኤልሳቤጥን ነገር ለመረዳት ወደእክስትዋ ወደ ኤልሳቤጥ ሄደች ። ሁለቱም ተገናኝተው ሰላምታ በተለዋወጡ ጊዜ በኤልሳቤጥ ማኅፀን ያለው ጽንስ ዘለለ ።

በኤልሳቤጥም ላይ መንፈስ ቅዱስ ሞላባት ። ኤልሳቤጥም በታላቅ ድምጽ ጮኻ«አንቺ ከሴቶች ሁሉ የተባረክሽ ነሽ ። የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል ? እነሆ የሰላምታሽ ድምፅ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ጽንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ። ያመነች ብፅዕት ናት » በማለት ምስጋና ለእግዚአብሔር አቀረበች ።

በዚሁ ጊዜ እመቤታችን «ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች መንፈሴም በአምላኪዬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች ። የባርያዪቱን ውርደት ተመልክቶአልና ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ። ብርቱ የሆነ እርሱ በኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና» በማለት የአዳም ልጆች በሙሉ እመቤታችንን ስእሊለነ ቅድስት ቅድስት ወብፅዕት እያሉ ሲወድሱአትና ሲቀድሱአት እንደሚኖሩ በመረዳት ተናግራለች

እመቤታችን ጌታችንን በቤተ ልሔም ወለደችው ። ጌታም እንደ ሕጻናት ሁሉ በጥቂት በጥቂቱ አደገ ። ነገር ግን ጠላቶቹ እየበዙበት በመምጣታቸው እንዳይገድሉባት

ይዘው ካገር ወደገር እየተንከራተተች ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ ተቀብላለች ። በተለይም አይሁድ ጌታችንን በዕለት ዓርብ ይዘው በየአደባባዩ እያዞሩ ሲያንገላቱት ፣ ሲሰድቡት ፣ ሲተፋበት ሲደበድቡት በመጨረሻም ወደጎልታ ወስደው በመስቀል ላይ ሰቅለው ሲገድሉት በማየትዋ ኀዘንዋ ልዩና አሰቃቂ ሆኖባታል ።

ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አምላክነቱ መጠን ሞትን ረግጦ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ በመነሣቱ ኀዘንዋ ወደደስታ ተለውጦ ለማየት በመብቃትዋ ደስ አላት ። በአባቱ ቀኝ በዕሪና ለመቀመጥ ከደብረ ዘይት ተነሥቶ በይባቤ መላእክት ወደሰማይ ሲያርግ እመቤታችን ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ሆና በማየትዋ የደረሰባትን ኀዘንና መከራ ሁሉ ረሳችው ። ከዚያ በኋላም ለአሥራ ስድት ዓመታት ያህል ከሐዋርያት ከቅዱሳት አንስት በአጠቃላይ ፣ ከመቶ ሃያ ቤተሰብ መካከል ተቀምጣ ልጅዋ ወዳጅዋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እያመሰገነች በክብርና በልዕልና ኑራለች ።

በመጨረሻም እመቤታችን ከዚሁ ከንቱና ጸር ጋር ከበዛበት ዓለም ይልቅ ሰላምና ደስታ ክብርና ጸጋ ወደሰፈነበት ዓለም ወደገነትገብታእንድትኖር የልጅዋፈቃድ በመሆኑ የሞት ጽዋ ቀመሰች ።

ሐዋርያትም በቅድስና ያሸበረቀው የመቤታችን ቅዱስ ሥጋ በሐርና በበፍታ ገንዘው በጌቴሰማኒ በክብር ቀብረዋታል ። አልአዛርን በአራተኛው ቀን ከመቃብር ያስነሣ አምላክ ልጅዋ ወዳጅዋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን ከመቃብር አስነሥቶ በገነት በክብር አኑሮአታል፤ቶማስ የእመቤታችንን ዕርገት አይቶ ሐዋርያት ትንሣኤዋንና ዕርገትዋን ስላላዩ ከነሐሴ ፩ እስከ ነሐሴ ፲፭ ቀን ጾም ይዘዋል ፡ ሱባኤ ገብተዋል ። እምስተኛውን ቀን ውለው በአሥራ ስድስተኛው ቀን እመቤታችን ተድላ ደስታ በመላበት በገነት በክብር እንደተቀመጠች ገልጾ አሳይቶአቸዋል ። ሐዋርያትም ደስ ብሎአቸው ወደ ወንጌል ማስተማር ተግባራቸው ተሠማርተዋል ።

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ፣ ምእመናን ።

ይህ የእመቤታችን ጾም ወደ ሀገራችን ከገባ ጊዜ ጀምሮ ሲወርሲዋረድ እነሆ እስከኛ ደርሶአል ። ቤ/ክርስቲያናችን ካሏት ሰባት አጽዋማት አንዱ ይህ ጾም ነው ። በዚህ ጾም ብዙ አባቶች እናቶች ተጠቅመዋል ። በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስም አግኝተዋል ።

ነገር ግን ወደኋላ መለስ ብለን ያለፉት አባቶቻችን ባሳለፉት ዘመን የነበራቸው የእምነትና የፍቅር ጽናት ከኛ ጋር ስናገናዝበው በአያሌ ልዩነት እንዳለው ይሰማናል ። ይኸውም በእነርሱ ዘመን የነበረው ጽኑ እምነት ፤ ፍቅርና ወንድማማችነት ርኅራኄና መተሳሰብ በየትኛውም አገር የሌለ እጅግ ጽኑ ነበር ። አንድነታቸው ፤ ፍቅራቸውና ወንድማማችነታቸውም ተራራ ሸንተረር ፣ ወንዛወንዝ ኮረብታ ገደል ቋንቋና ዘር የሚባል የዕውቀትና የዕድገት ዕንቅፋት እምብዛም አይታይም ነበር ድንቁርና ፡ ረሀብ ፣ ቸነፈር ፣ ድርቅ ሐሩር ፣ ማጣት ፣ ችግር የሚባሉ የኅብረተ ሰቡ ነቀርሳዎችም አልፎ አልፎካልሆነ በቀር በጉልህየሚታይበት ጊዜ አልነበረም ። መነቃቀፍ ፣ የመሳሰሉት የሰላምና የፍቅር የአንድነት ጸሮችም በአንዳንድ ወረዳዎች በተወሰኑ ጥቂት ሰዎች እንደሆነ እንጂ በጉልህ ይፋ ወጥቶ በብዛት አይታይም ነበር ። ስለሆነም እነዚህንና የመሳሰሉትንም ሁሉ ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን ነቀርሳዎች ስለሆኑ መወገድ አለባቸው ።

ክርስቲያን መከተል ያለበትና ማሳየት የሚገባው መተሳሰብና መተዛዘን መረዳዳትና አንድነትን ማጠንከር ነው ። እነዚህ ሁሉ ከፍቅር የሚመነጩ ስለሆነ በቅድሚያ እያንዳንዱ በፍቅር መተያየት ፍቅርን አጽንቶ መያዝ አለበት ። በክርስቲያን መካከል ፍቅር ካለ ሁሉም ይገኛል ። ሰላም ፣ በረከት ረድኤት ይወርዳል ። እግዚአብሔር አምላክችን ሀብትን ጤንነትን ይሰጠናል ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነው ተብሎ ተጽፎ አልና ።

ጽኑ እምነት ፣ አንድነት ፣ ፍቅርና ትሩፋት የሌለው ክርስቲያን ክርስቲያናዊ ሕይወቱ አልተስተካከለም ያሰኘዋል፤ እንደነዚህ ላሉትም እግዚአብሔር አምላክ በነቢዩ በኢሳይያስ አድሮ «ይህ ሕዝብ በአፉ ወደኔ ይቀርባልና በከንፈሮቹም ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና ፣ በሰዎች ሥርዓትና ትምህርት ብቻ ይፈራኛልና ።» ብሎ ይገሥጻቸዋል ። (ኢሳ ፲፰ ፤ ፳ ፡ ፱ ።)

ስለሆነም እኛ ኢትዮጵያውያን ባሁኑ ጊዜ በእምነታችን በትሩፋታችንና በክርስቲያናዊ አርአያነታችን ያሳዩት ከነበረው ቢበልጥ እንጂ አያንስም ። ነገር ግን አንዳንድ መሰናክሎች በማሳየታችን አምላካችን ሳናስቀይመው አልቀረንም ይኸውም ከላይ የጠቀስናቸው እንቅፋቶች አልፎ አልፎ በመካከላችን ስለሚታዩብን ነው ። ይህም ደግሞ ከእምነታችንና ከፍቅራችን መላላት የተነሣ እንዳይሆን የየራሳችን ክርስቲያናዊ ሕይወታችን መመርመር አለብን ። ስሕተታችንን አውቀን ማረምም ተገቢያችን ነው፤ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የይቅርታ አምላክ ነውና በእውነት ይቅር ይለናል ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ከልብ እንደምንወዳት ታውቃለችና ከስሕተትና ከጥፋታችን ከምትወደው ልጅዋ እንድታማልደን በእውነት እንማጸናት ፣ እርስዋ የቃል ኪዳን እናታችን ናትና



## የዘመን መለወጫ በዓል ቅዱስነታቸው በተገኙበት በደብረ ኃይል ቅ/ራጉኤል ቤ/ክ/ተከብሮ ዋለ ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የቅዱስ ዮሐንስንና የዘመን መለወጫን በዓል ምክንያት በማድረግ መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው አክብረዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ከቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ እንደደረሱ የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ኃይል ኪዳነ ማርያም አየለ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች መዘምራንን በማሠለፍና በማዘመር ከሰበካ ጉባኤ አባላት ጋር ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ እንደደረሱ ወንጌል ዘወርቅ የወርቅ ካባ ላንቃ የወርቅ መስቀልና ማዕጠንታተ ወርቅ የያዙ ካህናትና ዲያቆናት መዘምራን የብር ጸናጽልና ከበሮ በመያዝ ያሬዳዊ ጣዕመ ዝማሬን እየዘመሩ በደማቅ ሠልፍ ሲቀበሏቸው ከቅጽረ ቤ/ክርስቲያኑ አልፎ ወደ መርካቶ እስከ ሚወስደው መንገድ ድረስ ግራና ቀኝ ሞልቶት የነበረው ሕዝበ ክርስቲያንም በሆታ በዕልልታና በደስታ ተቀብ ሎአቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ወደ ቤተ መቅደሱ ገብተው የሕሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ ታቦተ ሕጉ ወደ ዐውደ ምሕረቱ ሲወጣ ቅዱስ ፓትርያርኩ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን በመምራት ታቦተ ሕጉን በማስቀደም አጅበው ሥርዓተ ዑደቱ ሦስት ጊዜ እንደተከናወነ በተዘጋጀለት ሥፍራ ቆሞአል ቅዱስነታቸውም በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ እንደተገኙ መዘምራን ለዕለቱ የተዘጋጀውን ግሥ ቃኝተው ለ፭ ደቂቃ ያህል አሸብሽበዋል ።

ከዚህም በማያያዝ የደብሩ ሰንበት ት/ቤት ወጣት መዘምራን ተመሳሳይ ያሬዳዊ መዝሙር ለ፲፭ ደቂቃ ያህል በጣዕመ ዜማ አሰምተዋል ።

በቅዱስ ፓትርያርኩ ፈቃድ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የደ/ሸዋና የውጭ ጉዳይ ግንኙነት ኃላፊ እንዲያስተምሩ ስለፈቀዱላቸው ብፁዕነታቸው ምእመናኑን እንኳን አደረሳችሁ በማለት መልእክት አስተላልፈዋል ። ከዚያም የቅዱስ ፓትርያርኩ በረከት እንዲቀበሉ ምእመናንን አሳስበዋል ።

የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ቃለ በረከት «የዛሬው በዓል የመላ ኢትዮጵያውያን በዓል ነው በመሆኑም ሁሉ እንዲያውቀው ይገባል ። የሀገራችንና የሃይማኖታችን ሥርዓት በተግባር የሚገለጥበት ፣ ቀን ነው ። ሕዝቡ ይህ በዓል ዳርእስከዳር ለማክበር ልዩ ዝግጅትና ሥነ ሥርዓት እያደረገ ነው ። የምንዘጋጀው ወይም በዛሬው ዕለት ቃል የምንገባው ሁሉንም አዲስ ለማድረግ ነው ። ከዛሬ ጀምሮ አዲስ ምዕራፍ አዲስ የሥራ ጅምር ለማድረግ ነው

ወደ ኋላ መለስ ብለን ባለፈው ዓመት ምን እንደሠራን መመርመር ያስፈልገናል ። አዲስ ዓመት የምንለው ከአምናው ሥራችን አርመን ወይም አሻሽለን ያልፈጸምነው እንዳለም ለመፈጸም ታጥቀን ስንነሣ ነው ።

በአጠቃላይ ከአምናው ይልቅ በዘንድሮው ዓመት የበለጠ ሥራ ለመሥራት ከልብ መነሣት እንዳለብን በሙሉ ልባችን ስናምን ነው ስለታሰሩት ወንድሞቻችን ታስረዋል እያልን እናወራለን ። ነገር ግን እኛ ደግሞ ከታሰሩት ወንድሞቻችን የተሻለ ሥራ ለመሥራት ስንችል ጊዜአችንን በስንፍና ገመድ እጅና እግራችንን አስረን ምንም ሳንሠራ ዓመቱን ሙሉ እሳልፈነዋል ።

ቅዱስ መጽሐፍ ለታሰሩት መፈታትን እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ይላል ፤ መታሰር ብዙ ትርጉም አለው በልዩ ምክንያት ሕግ ያሰራቸው ብቻ አይደለም እስረኞች የሚባሉት ሙሉ አካላት እያላቸው ሠርተው ራሳቸውን ለመርዳት የማይፈልጉ በስንፍና ገመድ የታሰሩ እስረኞች ናቸው መሥራት ሲችል በወሬ፣በሐሜትበአሉባልታ፤በምቀኝነት ፣ በተንኮል ጊዜውን የሚያሳልፍ የአመል እስረኛ አለ ። በሃይማኖታችን ሥርዓት ደግሞ በኃጢአት መዘፈቁን እያወቀ ንስሐ ገብቶ ነፃ መውጣት ሲገባው እስከ ዕለተ ሞቱ ዝም ብሎ የሚቀመጥ ሰውም በኃጢአት ገመድ የተተበተበ ነው። ይህ ሁሉ ይዘን አዲስ ዓመት በመጣልን እያልን የምንመኝ ካለን ተሳስተናል አዲስ ከፋት አዲስ



www.ethiopianorthodox.org

ተንከል ፤ አዲስ ምቀኝነት ፣ አዲስ ጉብኝነት አዲስ የሐሰት ምስክርነት ይዘን አዲስ ዓመት ለመቀበል መዘጋጀት የለብንም ንጹሕ ልብ ንጹሕ ሥራ ፣ ንጹሕ ፈቃድ ንጹሕ ፍቅር ፡ ንጹሕ ወንድማማችነትና አገርን ወገንን ወዳድነት ይዘን አዲሱን ዓመት ለመቀበል ከተዘጋጀን ያሰብነውን መልካም ነገር ሁሉ ይሰምራል ይከናወናልና ። አለዚያ ነሐሴ አልፎ መስከረም ስለጠባ ሥራ ሊሆን ፤ የዕድገት ርምጃ ሊፈጥር አይችልም ።

ቅዱስ ጳውሎስ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆነ ይላል እንደ ሐዋርያው ቃል በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ከኃጢአት ርቃችሁ ንጽሕ ጠብቃችሁ ከክፉ ነገር ሁሉ ርቃችሁ ነፃ ወጥታችሁ ለክብር ስለተዘጋጃችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ኃጢአት አትሥሩ ሲል ነው ሰው የሆነውን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድስና ሥርቶ አሳይቶ ከሰጠን ለምን እንቅፋት ይጥለናል(ያደናቅፈናል )።

አገራችን ከሌሎች አገሮች የተለዩ ሥርዓት ፣ የተለየ ባሕል አላት ስለዚህ እኛ ይህንኑ የሠሩልንና የተውልንን አባቶቻችንን ሥራቸውን እንድንከተል አምልኮታቸውን አምኮታችን አድርገን ይዘን እንድንሠራበትና ለሌሎችም መልካም አርአያ መሆን ይፈለግብናል የክርስትና እምነት ማለት በቀላል ነገር የሚታይ አይደለም ዓለምን የሚዋጋ ተዋግቶም ድል የሚያደርግ ቀጥ ያለ የጸና የቀና የማይናወጽ ማለትነው ።

ስለዚህ የክርስትና እምነታችን በዓለም የታወቀ ነው ። ነገር ግን በዚህ እምነታችን አድልዎ ጠማማ አስተሳሰብና መጥፎ ጠባይ መቀላቀል አይገባንም ። በእምነታችን ውስጥ ሌላውን ገድለን እኛ እንድን እኛ እንድንኖር ሳይሆን እኛ ሙተን ሌላው እንዲድን ማድረግ ዓላማችን እንደሆነ ማወቅ ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን አድኖ ሌሎች እንዲሞቱ ራሱ ነግሦ ሌሎች ነገሥታት እንዲሻሩ የሚል አስተሳሰብ ቢኖረው አንድም የሚያምንበት ወይም የሚከተለው ባላገኝ ነበር ። ስለዚህ የክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮቹም እንደመሪያቸው እንደ ክርስቶስ መሆን (መምሰል) አለባቸው ።

ክርስቶስን ማምለክ ትእዛዙን መፈጸም በተመቸ ጊዜ አይደለም በችግርና በመከራ ጊዜ እንጂ ፤ ስለ ሆነም እምነታችን በተግባር የተፈተነ መሆን አለበት በፈተና ወድቀን እምነታችን እንዳናስወስድ አጠንክረን መያዝ ይገባናልና በርቱ ጊዜው ሰዓቱ የዝናም ወቅት ስለ ሆነ በሌላ ጊዜ በሰፊው ተገናኝተን በሰፊው እንነጋገራለን ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ በማለት አባታዊ ምክራቸውንና ቡራኬአቸውን ሰጥተው እንዳበቁ ታቦቱ ወደመንበረ ክብሩ ተመልሶአል ።

ከዚያም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መሪነት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተራዳኢነት ሥርዓተ ቅዳሴው ከስድስት ሰዓት ተኩል እስከ ስምንት ተኩል ተካሂዶ እንዳበቃ በዘጠኝ ሰዓት ሠርሆተ ኅኖ የበዓሉ ፍጻሜ ኾኖአል ። ቅዱስነታቸውም ወደ መንበረ ካናቸው ተመልሰዋል ።

## ቅዱስነታቸው እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰዎ ለማለት የመጡትን ቡራኬ ሰጡ ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መስከረም ፫ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰዎ ለማለት የመጡትን በቅዱስ ሲኖዶስ አዳራሽ ተቀብለው ቡራኬ ሰጡ ። በስነ ሥርዓቱ ላይም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የርእሰ አድባራት አክሱም ጽዮን ቤ/ክርስቲያን ዕድሳት ኮሚቴ አባላት ፣ የርእሰ አድባራት አዲስ ዓለም ቅ/ማርያም ቤ/ክርስቲያን ልማት ኮሚቴ ፣ የተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እድሳት ኮሚቴ አባላት ፣ ሠራተኞች የትንሣኤ ዘጉባኤ ፣ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ የማሳተሚያ ድርጅት ፣ የቅ/ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤትና የዳቦ ቤት ፣ የኅሩ ጥበበ እድና የሕፃናት አስተዳደግ ሠራተኞች ፣ ከአዲስ አበባና ከየክፍላተ ሀገራቱ የመጡ አዛውንትና ወይዛዝርት ተገኝተዋል ከላይ የተጠቀሱ ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናትና ድርጅቶች ወደ ቅዱስነታቸው እየቀረቡ እንኳን ለ፲፱፻፹፭ ዓ/ም አዲሱ ዓመት አደረሰዎ እያሉ ቡራኬ ተቀብለው ወደየቤታቸው ተመልሰዋል ። ለእንግዶቹም የለስላሳ ግብዣ ተደርጎላቸዋል ። ከሁሉ በፊት ግን ከላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች በቅደም ተከተል ያላቸውን ልባዊ ምኞት በአክብሮት ገልጸዋል ።

በቅድሚያ የአክሱም ጽዮን ርእሰ አድባራት ቤ/ክርስቲያን ዕድሳት ኮሚቴ ሊቀ መንበር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ገ/መድኅን እንኳን ደስ አለዎት በማለት ሲናገሩ ቅዱስነትዎ በከፍተኛ ድምፅ ተመርጠው ለዚህ ከፍተኛ ርእሰ ቤተ ክርስቲያን በመብቃትዎ ለደስታችን ወሰን የለውም ደግሞም እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሰዎ አዲሱ ዓመትም የደስታና የጤንነት ፡ የሥራ ዘመንም እንዲያደርግልዎ በርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን ቤ/ክርስቲያን ዕድሳት ኮሚቴ ስም ምኞቴን እገልጻለሁ ሲሉ አጭር የደስታ መግለጫ አሰምተዋል ።





ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ስለዘመን መለወጫ በዓል ቃለ በረከት በሰጡበት ወቅት

ቀጥሎም የርእሰ አድባራት አዲስ ዓለም ማርያም ቤ/ክርስቲያን ልማት ኮሚቴ አባላት መካከል አንዱ «ቅዱስነትዎ እንኳን እነዚያ የፈተና ዓመታት አልፈው «ነሪይኩከ እምከርሠ እምከ » ከጥንቱ ከጥዋቱ እግዚአብሔር መርጦ ለዚህ ከፍተኛ መንፈሳዊ አባትነት አደረሰዎ » በማለት ምኞታቸውን ገልጸዋል ። አያይዘውም ርግበ ኖኅ የወይራ ቅጠል ይዛ ሐጸ ማየ አይኅ ነትገ ማየ አይኅ ብላ እንዳበሠረችው እኛ ደግሞ በቅዱስነትዎ ፊት ቀርበን የጥልና የክርክር የመለያየትና የጦርነት ዘመን አክተመ የቅዱስትዎ ዘመነ ሢመት የሰላም የደስታና የጤንነት የሰላምና የፍቅር ዘመን ተበሠረ እያልን ከመግለጻችንም ፣ በላይ የቅዱስነትዎ ዘመነ ሢመት የሰላም የደስታና የጤንነት ዘመን እንደሚሆን ልዎ ምኞታችን ነው ብለዋል ።

አያይዘውም የተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እድሳት ኮሚቴ አባላት ቀርበው ቅዱስነትዎን እንኳን ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ በሰላምና በጤና አደረሰልን እያልን መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን ። ካሉ በኋላ ባሁኑ ጊዜ አንዳንድ ታላላቅ ቦታዎች «ተንተንኩ ለወዲቅ ወእግዚአብሔር አንሥአኒ»እንደተባለው ለመውደቅ በመፍገምገም ላይ በሚገኙበት ጊዜ ቅዱስነትዎ ስለደረሱላቸው በአደጋ ከመውደቅ ለመዳን ችለዋል ብለዋል ።

በዚህም ወቅት ለቅዱስነታቸውም ከልዩ ልዩ ሊቃውንት ልዩ ልዩ ቅኔያት ተበርክቶአል ። ልዩ ልዩ ጣዕመ ዝማሬም ተንቆርቁሮአል ። እንዲሁም በወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊዎች ከየአድባራቱ የተውጣጡ ወጣት መዘምራን ለበዓሉ የሚስማማውን መዝሙር በማዘጋጀት የዘመሩትን ለበዓሉ ድምቀት ሰጥቶት ነበር ።

ከመዝሙራቱ ጥቂቶቹ «ልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል ለዚህ ሰዓት በሰላም በጤና አደረሰን ፣ መስከረም ጠባዬ ኢዮሐ አበባዬ ፣ ኮከብ ብሩህ ቅዱስ ጳውሎስ ዘሠረጸ እምኢትዮጵያ ቤ/ክርስቲያን እንዘ ንሰምያ ፤ ኮኖሙ አበ ለኢትዮጵያ ፣ አማን በአማን ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያ ፤ ሰላም ለኢትዮጵያ ሰላም ላገራችን ይላክልን ቸሩ አምላካችን ። ሰላምን ስጠን አምላክ ሰላም ፤ የኢትዮጵያ አንድነት ይኑር ለዘላለም የቤ/ክርስቲያን አንድነት ይኑር ለዘላለም እያሉ በሰፊው ዘምረዋል ።

በዚሁ ጊዜ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ለሕፃናቱ ቃለ በረከት ሰጥተዋቸዋል ።
«እናንተ ሕፃናት እግዚአብሔር ይባርካችሁ ለዓመቱም በሰላም ያድርሳችሁ እናንተ እንዲህ ተዘጋጅታችሁ ስናይ ቤ/ክርስቲያናችን እጅግ እንደተደራጀች ይሰማናል ። ለወደፊቱ ቤ/ክርስቲያናችን ከዚህ የበለጠ ለመደራጀት እንድትችል እኔ ከእናንተ ጋር ሁኜ አደራጃለሁ ፤ እናንተም በርቱ ። ወንድሞቻችሁ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥራዝ ነጠቆች ቀበሮ የበጎች ግልገሎች እየነጠቁ እንደምትወስዳቸው እየነጠቁ ሲወስዱአቸው ዝም ብላችሁ መመልከት የለባችሁም እንደ እናንተ እንዲሆኑ ምክሩአቸው ። ለወደፊቱም ከዚህ የበለጠ



www.ethiopianorthodox.org

እንድትበረቱ አደራ እንላችኋለን ለሀገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ዕድገትና ብልጽግና ሰላምና መስፋፋት ታጥቀን እንሠራለን ።

ከተንኮለኞች ተጠበቁ የእናንተ ጸሎት የሚጠቅም ስለሆነ ለሀገራችሁና ለቤተ ክርስቲያናችሁ ጸልዩ በአንድነት በሰላምና በፍቅር ጽኑ እግዚአብሔር ይባርካችሁ ፤ ዘመኑ የሰላም ፤ የብልጽግናና የአንድነት የፍቅር ዘመን ያድርግልን በማለት አባታዊ ቡራኬ ሰጥተው አሰናብተዋቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሰንበት ት/ቤት መዘምራንን አሰናብተው ከዚህ እንደሚከተለው በወቅቱ ለነበሩት አባቶችና ሠራተኞች ቃለ ምዕዳናቸውን አስተላልፈዋል ። ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሊቃውንትና መምህራን ከሌሎቻችሁም የተሠነዘረው ንግግር የሚያበረታታና የሚያነቃቃ ነው ሆኖም ግን ሥራው እዚህ ካለን ሁሉ አንድ ስንኳ የማይመለከተው የለም እያንዳንዳችን የሚመለከተን ነው ። ቀደም ብሎ ባለፉት ዓመታት አባቶቻችንም እናቶቻችንም ወንድሞቻችን እኅቶቻችንም ሁሉ ጠራርጎ የወሰዳቸውን ማዕበል እኛን ወይም አሁን ያለነው ማስቀረቱ ለአንድ ዓላማ ነው ።

እንዲህ ከሆነ በጳጳሳቱ በካህናቱ የተነገረውና የተሠነዘረው ሐሳብ ከሁሉም ዘንድ የሚጠበቅ ነው ዲሞክራሲ ማለት እኩልነት ወንድማማችነት ፍትሕ ርትዕ የሰፈነበት አመራር ማለት ነው ።ስለዚህ ይህ መልካም ተግባር ለሁሉም ለማብሠር ሊቃነ ጳጳሳት ከደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር ሆነው ሰላም እኩልነት ስምምነት ማስተማር ፤ ዋና ተግባራቸው ነው ። የኛ ሥራ ይኸው ነው ። ከዚህ የበለጠ ሌላ ሥራ ያለን አይመስለኝም እግዚአብሔር እያለ ማንም ኃይለኛ ነኝ ባይ በኃይሉ ቢመካም አሳልፎ አይሰጠንም ብዙ ሰዎች በኃይላቸው በብዝኃ ሠራዊታቸው ይመኩ ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር ስላል ተባበራቸው አንዳችም ሳይሠሩ እንዳልነበሩ ሆነዋል ።

ስለዚህ ማንኛውንም በሀገራችን የምናየው ከእምነት ውጭ የሆነ ሥራ ሁሉ በሌሎች አገሮችም ሲፈጸም የሚታይ ነው በሀገራችን ብቻ አይደለም ይልቁንም በልጦ የሚታየው በሌላ አገር ነው ። ከክፉ ነገር ሁሉ ለመዳን የሚቻለው ግን በእምነት ጸንቶ መሥራት ስለሆነ በእምነታችን ጸንተን መሥራት አለብን ።

ልጆቻችን በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ እንዲጠነክሩ በርትተን ካስተማርናቸው ፈጽሞ ወደሌላ እምነት አይሄዱም ከሌላ እምነትም ሄደው አይቀላቀሉም ከዚህ በላይ አልፎ የሚመጣ ካለ ግን ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ (የሚለየን) የለም ብለን ጸንተን መቆም ይገባናል ። ለሁሉም ሁሉን የሚችል አምላካችን ክርስቶስ ከኛ ጋር ይሁን በማለት መርሐ ግብሩን በቃለ ቡራኬ አጠቃለው እንዳበቁ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።



ቅዱስነታቸው በዘመን መለወጫ በዓል ሕዝቡን ሲቀበሉ

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያን አንደኛ በዐለ ሢመተ ፓትርያርክ ምክንያት በማድረግ ከመሪጌታ ኤፍሬም በየነ የቀረቡ ቅኔዎች

ዘምሪ ጽዮን ወየብቢ ንግሥተ ጽዮን
አክሱም ፤
አምጣነ ተወልደ ካዕበ ሰላማ በዘ
ጳውሎስ ዓለም ።

## መወድስ

እመዝገበ መንግሥት አክሱም
መዝገበ ቅድምና ፤
በለብዎተ ጽድቅ ወሕግ ምሥጢራተ ካሌብ መተርጕም
መተርጕማነ ጽድቅ ወሕግ ሊቃውንተ ኵሉ ዓለም
ለእመ ሐተቱ በለብዎ
ለንጉሥ ፓትርያርክና ልደቱ አክሱም
ከመ ከመ ዝንቱሰ ይትዐወቅ
አምጣነ በልደት ክህነት ሰላማስ ይቀድም

## ለዓለም

ጳውሎስ አበ ኵልነ መምህረ ሰላም ፍጹም
በዘመነ ክረምት ቅድስናከ እሕመልማሴ ደብር ወገዳም
ያሕመለምል ምድር እስከነ ጽጌ ምድር አዳም
ዝናመ ሰማይ በረከትከ በኢትዮጵያ ዘይዘንም

## መውድስ ፪

ሕሲና ቅዱሳን ጸሎት መርሀ ብዙኃን ፤
በመልዕልተ ፍኖት ተጽናስ ምሕዋረ
እግረ ታኤል ሀቤ ምዕት
ዓመተፈጸመዮምበዘቅዱሳንሥርዓት
ለጽዮን ዘተመይጠ ።
ሀብተ ጽዮን ፓትርያርክና እንተ ጽዮን ሀብት
ንግሥተ ቅዱሳን ኢትዮጵያ
ለጽዮን ይኩን እምጣነ እዘዘት ወፈቀደት ።

## ለዓለም

ይትነገርሰ ወይትዐወቅ መጽሐፍ ዘአክሱም ነገሥት ፤
በልሣነ ጳውሎስ ተፋቅሮ ይቤሉ ሊቃውንት ፤
ምስለ ሐተታ ጽድቅ ሰላም ወንባበ ሰላም ፍጽምት ፤
ነአምር ትርጓሜሃ ለመልዕክተ ጳውሎስ በረከት

# ቅዱስ ፓትርያርኩ ደብረ ቅዱስ ደብረ ጽጌንና ደብረ ሊባኖስን ጐበኙ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌንና ታላቁ ገዳም ደብረ ሊባኖስን ጐብኝተዋል ። በጉብኝቱም ወቅት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የአስተዳደርና የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጆች ፤ ታላላቅ እንግዶችና የገዳማት አበምኔቶች ተገኝተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ቅ/ማርያም ቤ/ክርስቲያን ሲደርሱ የገዳሙ አስተዳዳሪ ፤ የገዳሙ አበው መነኮሳትን ልብሰ ተክህኖ በማልበስ ካህናትንና ዲያቆናትን ፤ የሰበካ ጉባኤ አባላትን ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራንና የአካባቢው ምእመናን ምእመናትን በማሠለፍ በደማቅ ሥነ ሥርዓት ተቀብለዋቸዋል ። እንዲሁም የገዳሙ መዘምራን ሊቃውንት «ጳውሎስ ቅዱስ አቡነ አበ ኵልነ ኖላዊ ኩነነ» የሚለውን ቃኝተው ለአሥራ አምስት ደቂቃ ያህል አሸብሸበዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ወደ ቤተ መቅደስ ገብተው አጭር የሕሲና ጸሎት አድርሰው እንዳበቁ ወደ ዐውደ ምሕረቱ ወጥተው በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ ተገኝተዋል ። የመዘምራኑ ሽብሻቦ እንዳበቃ ጸሎተ ወንጌል ደርሶ ከዮሐንስ ወንጌል ምዕ ፫ ፤ ፩—፳፪ ያለውን በቅዱስነታቸው ተነቦአል ።

ከዚህም በኋላ ቅዱስ ፓትርያርኩ አጭር መግለጫ ሰጥተዋል ። ቅዱስነታቸው ካደረጉት ንግግር «ይህ ደብር ታላቅ ደብር ነው ። በዚህ ታላቅ ደብር ዕውቀታቸው ያዳበሩ ምሁራን በየቦታው ተሰማርተው እናት ቤተ ክርስቲያናቸውን እያገለገሉ ምእመናንን እያስተማሩ ይገኛሉ ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ይህ ታላቅ ቦታ በከፍተኛ ወጭና ድካም ለሀገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን በረከትና ረድኤት የሚወርድበት ፤ ምሁራን የሚፈልቁበት እንዲሆን አስበው ነው ፤ ያሠሩት» ።


«ስለዚህ ይህ የቅዱስነታቸው ታላቅ ቦታ እንዳሰቡትና እንደተመኙት ሁሉ መቀጠል አለበት አባቶቻችን ሠርተው አቅንተው ያስተላለፉልንን ሁሉ እየጠበቅን ቤ/ክርስቲያናችን እንድትስፋፋ እንድትጠነክርና እንድትበረታ ማደራጀት አለብን ። ተቀናቃኞቻችን እየተፈታተኑን ስለሆነ ነቅተን ተግተን መሥራት መጠበቅና ምእመናንን በትምህርተ ወንጌል ማበርታት አለብን ። ምሁራን አባቶቻችን ካንዱ ወዳንዱ አገር እየተዘዋወሩ ደበሎ ለብሰው ቆሎ ቆርጥመው ከውሻ ጋር እየታገሉ ፤ ሲያገኙ በልተው ፤ ሲያጡ ተርበው በመማር የቤ/ክርስቲያናችንን ይትበሃል እስከዚህ አድርሰውታል ። እኛ ደግሞ እንደ ሃይማኖታችን ጽናት ለሃይማኖታችን በበለጠ ሠርተን መገኘት አለብን እንጂ ዝም ብለን መመልከቱ አይበጀንም ።

እንግዲህ እኔም በተቻለ መጠን የደብሩ ሥራ እንደነበረው እንዲቀጥል ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ ፤ በርቱ ጠንክሩ ፤ ሃይማኖታችሁን ጠብቁ በት ህርት ገበታ ያላችሁም ተማሩ እግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁንና በሌላ ጊዜ መጥተን በርጋታና በቀስታ እንገነኛችኋለን ፤ አሁን ግን ጊዜ ስለሌለን ልናነጋግራችሁና ሐሳባችሁን ልንቀበላችሁ አልቻልንም ፕሮግራማችን አጭር ነው» በማለት ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው እንዳበቁ ጉዞው ወደ ደብረ ሊባኖስ ቀጥሎአል ።





www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ሥርዓተ እርድዕት ሲያሳዩ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ልክ ከቀኑ ፯-፰ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሲደርሱ የገዳሙ አስተዳዳሪ አበው መነኮሳት ፣ ልብሰ ተክህኖ ጽንሐሕ መስቀልና የሻማ መብራት የያዙ ካህናት ዲያቆናት የደብረ ሊባኖስ ተግባር ቤት እድሳት ኮሚቴ አባላት ፣ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ተሳላሚዎች ምእመናን በሰልፍ ከፍተኛ የሆነ ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ወደቤተ መቅደስ ገብተው የሕሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ ወደ ዐውደ ምሕረቱ ወጥተው ሕዝቡን በቃለ ወንጌል አጽናንተው አባታዊ ቡራኬ ሰጥተው ወደማረፊያቸው ተመልሰዋል

ከጥቂት ዕረፍት በኋላም ቅዱስ ፓትርያርኩ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ቤተመስቀልን ጎብኝተዋል ። ቤተ መስቀሉ ከፎቅ ላይ ሆኖ ምድር ቤቱ አሥራ ሁለት አበው መነኮሳት የዘወትር ጸሎት የሚያደርሱበት በሥነ ስቅለት ፣ በእመቤታችን ፣ በመላእክትና በቅዱሳን ሐዋርያት ሥዕል ያሸበረቀ ነው ፤ ቅዱስነታቸው በዚያ ጸሎተ ማኅበር ሲያደርሱ ላገኙአቸው አበው መነኮሳት ከጸሎቱ ፍጻሜ በኋላ ቡራኬ ሰጥተዋቸዋል ። ከዚሁ በመቀጠል ወደ ፎቁ ዘልቀው በዓመት አንድ ጊዜ የመጋቢት ፲ ቀን የመስቀል ዕለት ብቻ የሚቀደስበትን ቤ/መቅደስ ጸሎት አድርሰው ከሰማይ የወረደውን መስቀል ተመልክተዋል ። ከዚሁም ሌላ በዚሁ በቤተ መቅደሱ ምድር ቤት ፲፪ አበው መነኮሳት በአሥራ ሁለት ሐዋርያት ምሳሌ ፣ ሆነው በምሥራቅ በምዕራብ ፣ በሰሜን በደቡብ እያንዳንዳቸው በግላቸው ግላዊ ጸሎት የሚያደርሱበትን ፲፪ ክፍል ጎብኝተዋል ። ቅዱሳን ሐዋርያት አባቶቻችን ይህን ዓለም በአራት መዓዝን ከፋፍለው እንዳስተማሩት ሁሉ እነዚህ አባቶችም የቤተ መስቀል ሕንጻውን እንደ ዓለም አድርገው በአራቱ መዓዝን ሲጸልዩበት ይኖራሉ ። ለመላ ኢትዮጵያም በአራት መዓዝን ሁነው ጸሎታቸውን ወደ አምላካቸው ወደ ክርስቶስ ሲያደርሱ ይገኛሉ ።


ቅዱስ ፓትርያርኩ በቤተ ምርፋቁ ለተገኙ አበው መነኮሳት አባታዊ ንግግር አድርገውላቸዋል ። የቅዱስነታቸው ንግግር «ዛሬ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመካከላችሁ በመገኘቱ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል ። በቅድሚያ ልናገር የምፈልገው እኒህ የመላ ኢትዮጵያ አባት የሆኑት ቅ ዱ ስ አባት አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር አብሬ ለማየትና ለመጎብኘት በመብቃቱ ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ

ከእኒህ ቅዱስ አባት እንኳንስ ኢትዮጵያዊ ከሌላም አገር ቢሆን በረከታቸውንና ረድኤታቸውን ያላገኘ ይኖራል ብየ አልገምትም ይህ ቤተ እግዚአብሔር ብዙዎቻችን አገልግለንበታል ። በረከትንም አግኝተንበታል ። ባሁኑ ጊዜ በዕርጅና የምንገኝም አለን ። ስለዚህ ይህ ምርፋቅ ወይም ቤተ ጸሎት እንደጥንቱ መሠረት ሳይነቃነቅ ፣ ሕጉ ሥርዓቱ ሳይፋለስ ጸንቶ እንዲኖር ሁላችንም መጣር አለብን ። በጨለማ ያሉት ወገኖቻችንንም ወደ ብርሃን ለማውጣት ታጥቀን መነሣት ይገባናል ። ለሁሉም እምነት ነው የሚያስፈልገው እምነት ብዙ ሥራ ይሠራል ። ሠለስቱ ደቂቅ በእምነታቸው ከነደደው እሳት እንደዳኑ እንመለከታለን ። አባቶቻችንም በእምነታቸው የጸኑ ስለነበሩ እንዲህ ዓይነቱ ሥራ ሠርተው ሥርዓት ደንግገውልን (ትተውልን) ሄደዋል ። አልፈዋል በዚህ ተግባራቸውም እጅግ እናደንቃቸዋለን ። ይህ የተቀደሰ ተግባር ሁሉ ለመፈጸም የቻሉት ወይም የታደሉት በአንዲት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት በአንድ ልብ በኅብረትና በአንድነት የጸኑ ስለነበሩ ነው ። እኛም እንደ አባቶቻችን በእምነታችን በአንድነታችንና ፤ በኅብረታችን ጸንተን መሥራት አለብን እኔ ትንሽ ወንድማችሁ ለዚህ ትልቅ ኃላፊነት የማልበቃ ደካማ ስሆን በኃያሉ እግዚአብሔር ፈቃድና ጥሪ ይህ ከባድ ኃላፊነት አደራ ተጥሎብኛል ። ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ የእምነት ማጠንከር ፣ የማስተባበርና በአንድነት ሆኖ የመሥራት ከፍተኛ ኃላፊነት አለብኝ ከእናንተ ጋር ሆኜ ለማገልገል ዝግጁ ነኝ ሁላችሁም ለተቀደሰ ዓላማ ታጥቃችሁ እንደምትነሡ እምነቴ ጽኑ ነው ። እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን በርቱ ጠንክሩ»በማለት ካበረታቱአቸው በኋላ ወደት/ቤቱ አምርተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከት/ቤቱ እንደደረሱ ብር ተቀብለዋቸዋል ። በዚሁ ት/ቤት የብሉይና የሐዲስ ደቀ መዛሙርት በጠቅላላ ሃያ አምስት እንደሚገኙ ተረጋግጦአል ።

በዚህ የቅዱስነታቸው ጉብኝት ወቅት መምህር ገ/ማርያም እጽብሐ የአ/አበባ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ት/ቤቱን በተመለከተ ስለት/ቤቱ ንግግር አድርገዋል ። ይኸውም «ይህ ት/ቤት በመምህር ገ/ኢየሱስ ስም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ የተመሠረተ ሲሆን ት/ቤቱ ብሉያትንና ሐዲሳትን መጻሕፍተ ሊቃውንትን እንዲሰጥበት ታስቦ ነው የተቋቋመው አሁን ብሉያትንና ሐዲሳትን ብቻ እንጂ መጻሕፍተ ሊቃውንት አይሰጥበትም ።

አብዛኛዎቹ ሊቃነ ጳጳሳት የተማሩት ከዚህ ት/ቤት ነው ። ታሪ



ቅዱስነታቸው የገዳሙን ምግበ ሠርክ በተግባር ሲያሳዩ

የብሉያትና የሐዲሳት ደቀ መዛሙርት «ሐረየከ ወሤመከ ከመ ትሢም ጳጳሳተከመ ታሳተራትዕ ሃይማኖተ ጳውሎስ አቡነ »እያሉ በከ

ኩንም ያውቁታል ። ለዚህ ት/ቤት ከአ/አበባ ሀገረ ስብከት ለእያንዳንዳቸው ብር ፫ በወር (ስልሳ ብር) ይሰጣቸዋል ። ከዚህም በቀር ብርድ ልብስ ብቻ ያገኛሉ ። ለልብስ ፣ ለሕክምና አይሰጣቸውም ፫ ብር ባሁኑ ጊዜ ለቀለብ እንኳ እንደማይበቃቸው የታመነ ነው ። ስለዚህ ቅዱስነትዎ በብሩህ ልቦና እንዲመለከቱትና አንድ መፍትሔ እንዲያገኝ ቢደረግ መልካም ይመስለኛል ብለዋል ።

ሌላው ከዚህ እየተማሩ የሚወጡ ደቀ መዛሙርት እንደሌላው ት/ቤት ዲፕሎም ወይም የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ቢደረግ ተገቢ ይመስለኛል ። ከዚህ በላይ ያቀረብኋቸው ሐሳቦች በሥራ እንዲውሉ አንድ ውሳኔ እንዲደረግላቸው ይገባል ስል በትሕትና ለቅዱስነትዎ አሳስባለሁ ።

ከዚህ በኋላ ከደቀ መዛሙርት መካከል ሦስቱ መግለጫና ልዩ ልዩ መወድስ ቅኔዎች አበርክተዋል ። ከባለ ቅኔዎች አንዱ ደቀመዝሙር ካቀረባቸው ሦስት መወድሳት ፣ ልሳነ ጳውሎስ መዝገበ ንጽሕና ዞሑለ ዓዕይንት ጳውሎስ ፍትወ
ስን ።

ኮከበ ጽባሕ ጳውሎስ ወሀቤ ብሩህ
ብርሃን ።
ጳውሎስ ዕውደ ጽሕም ።
ቀይሕ ከመ ጽጌ ረዳ ጳውሎስ ሮማን
ጳውሎስ አልባስጥሮስ ዕፀ ቀናን
ሞስ ጳውሎስ
መዓዛ አፈው ወስኂን ።
ጳውሎስ ዕንቈ ባሕርይ ዘታንጸ
በርቅ ለዓይን ።
ጳውሎስ ጽጌ ፍሕሶ ጳውሎስ ሐረገ
ወይን ።
ለመርድአ ብሉይ ወልድከ ዘልቡ
ናየ ኀዘን ።

ናዝዘኒ በቃልከ ናዛዜ ኀዙናን ወት
ኩዛን ።
እንበሌከ ባዕድ እስመ አልብየ ጸወን
ናዝዘኒ በቃልከ ናዛዜ ኀዙናን ወት
ኩዛን ።

አማርኛ መወድስ

ዝናህ የተሰማ ጳውሎስ ባለማችን
ዙሪያ
በመመራመር ደርሰህ እስከ ጥት
ርክና ጨረቃ ፤





www.ethiopianorthodox.org

በድንግልና ሳይንስ ስለሆንህልን
ጠንቃቃ ።
ያልሠለጠነ ሰው ቤተ ክህነት
እንግዲህ ባንተ ሥልጣን ይሠልጥን
ይንቃ ።
ወዘረኝነት ድንቁርና ከሀገራችን ፣
ይወገድ
ወገኖቻችንን ስላጠቃ ።

ጳውሎስሂ ሐዋርያችን ባለ ሰባ
ሁለት ቋንቋ
ዜና ትምህርትህ ተነገረ ከአሜሪካ
እስከ አፍሪቃ ።
ለዚህም ዕድልህ እኛ እንድንበቃ
የልቡናህ ሐሳብ መንፈስህን ከኛ
ዘንድ አታርቀ ።
መወድስ ከመሪጌታ ልዑለ ቃል
አካሉ ።
ትቤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሐዋ
ርያ ወንጌል ጳውሎስ ዘአጽናፈ
ዓለም ዖድከ ።
በምህሮ ወንጌል ሐዲስ እንዘ መን
ፈስ ቅዱስ ወልታከ
ትትዐሠይ አክሊለ ምዝጋና ተደ
ለወ ለከ ።
ዳዊት በከመ ይቤ እስከ ጽንፈሃ

ለምድር እስመ በጽሐ ነቢ
ብከ ።
ሰስሏሂ ግላ አሪት እምእመናኒከ ።
አምጣኒ ዓለም ተቀደሰት በስብከተ
ወንጌል ብርሃንከ ።

ንሕነ ናነክር እምግርማ ገጽከ ።
አምጣነ አክሊልከ ዘብርሃን ወሐ
መልማለ ወርቅ ክዳንከ ።

ከዚህም በኋላ ብፁዕ ወቅዱስአቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከዚህእንደሚከተለው ተናገሩ ። ቅኔያትን መጻሕፍትን ፈትተው ከሚያጎርሱ ሊቃውንት ይህን የመሰለ ንግግርና ረቂቅ የቅኔ ምሥጢር ለመስማት መብቃት ትልቅ ዕድል ነው ። ይህንኑ መንፈሳዊ ሀብት በቤተ ክርስቲያናችን ሳያቋርጥ እየሰፋና እየተስፋፋ እንዲሄድ ይገባል ። ምክንያቱም ቤ/ክርስቲያናችን እንደነዚህ ያሉትን ተቋሞች ከሁሉ በላይ አልቃ ማየት አለባት አባቶቻችን በዚህ ቅዱስ ዓላማቸው ቤ/ክርስቲያንን ለማጠንከርና ለማበልጸግ ፣በማሰብ



ቅዱስ ፓትርያርኩ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ከሰማይ የወረደውን መስቀል በተመለከቱበት ወቅት

ጥሩ የምሁራን ምንጭ ለማስገኘት አስበው ያቋቋሙት ስለሆነ እኛም የእነርሱን ሐሳብ ተከትለን ቢቻል እንደጊዜው ሁኔታ በበለጠ አሻሽለን አለዚያ ግን የተውልንን እንኳ በተቻለ መጠን አሻሽለን ጠብቀን ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ ትልቅ አደራ አለብን እንዲህ ካላ ደረግን ምንደኞች (ሙያተኞች) ፣ እንጂ እውነተኞች እረኞች ሊያሰኝን አይችልም ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ይህ ትልቅ ት/ቤት በትልቁ መምህር ስም ያቋቋሙት የብሉያት ፣ የሐዲሳትና የሊቃውንት ከነሙሉ ዝግጅቱና ድርጅቱ ነበር ይሁን እንጂ እንደነበረው እንዳይቀጥል በአንዳንድ እንከን የተቀደሰ ተግባሩ እንዳይገፋ እነሆ ከነበረበት ደረጃ እያሽቆለቆለ ነው የተገኘው።

አሁንም እናንተ ተማሪዎች የያዛችሁትን ዓላማ በአንዳንድምክንያት ከግቡሳታደርሱወደኋላ ማለት የለባችሁም።የመጻሕፍት የአቋቋም የዜማ፡ የቅኔ ተማሪዎች እናንተ ብቻ አይደላችሁም ። እነዚህ የምታዩአቸው አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት እየለመኑ ቅይጥ እህል እየተመገቡ ፣ አሻሮ እየቆረጠሙ ተምረው ቤ/ክርስቲያናቸውን በልዩ ልዩ የሥራ መስክ አገልግለው ለዚሁ ደረጃ ሊደርሱ ችለዋል ። ስለዚህ እናንተም በትምህርታችሁ በርትታችሁ ላቀዳችሁት ዓላማ በቅታችሁ የድካማችሁን ፍሬ ለማየት መብቃት አለባችሁ ። ማንኛውም ሞራልም ሆነ ርዳታ እያስፈልጋችሁም ማለቴ አደለም ። ይህ ካላገኘሁ እንዲህ ካልተደረገልኝ አልማርም ብላችሁ በስንፍና እንዳትታሰሩ ነው አደራ የምላችሁ ። ጠንክሩ ፤ ለደመወዝ ብላችሁ እንዳልገባችሁ አምናለሁ ተምሬ አውቃለሁ ቤ/ክርስቲያኔንም አገለግላለሁ በማለት ለመማር እንደገባችሁም እተማመናለሁ በማለት ምክራቸውን ለግሰው ወደ ተግባር ቤት አምርተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተግባር ቤቱን አንድ በአንድ እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል ። በዚያም ብዙ አበው መነኮሳት በክብር ተቀብለዋቸዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከጉብኝቱ በኋላ ከአንድ ረድዕ የሊጡን መለኪያ ተቀብለው የረድዕ ተግባር አሳይተዋል ። የተግባር ፣ ቤቱ ጣራና በረንዳው በቅርብ ጊዜ ቆርቆሮ እንደለበሰ ቢታይም አወዛጋቢ ቃላት ሲሰነዘር ሰምተናል ይኸውም ጸባቴ አርአያ ሥላሴ አጽብሐ እኔ ገዳሙን በማስተዳድር በት ብር ፰ሺህ (ስምንት ሺህ ብር) የገዳሙ እባንክ ስላለ ወጭ ሆኖ ይሠራ ብለን ወጭ አድርገን ያሠራነው እኛ ነን ሲሉ በአካባቢው ተወላጆችና በአዲስ አበባ በሚገኙት በጎ አድራጊዎች ተግባር ቤቱን ለማደስ የተቋቋመው የልማት ኮሚቴ ደግሞ እኛ ካስገኘነው ገንዘብ እኛው ነን ያሠራነው እንጂ ጸባቴ አርአያ ሥላሴ እንዳሉት ገንዘቡ ከገዳሙ የተገኘ አይደለም የሚል ነው ።

ያም ሆነ ይህ ተግባር ቤቱ ጣራውም ሆነ በረንዳው በቅርብ ጊዜ ቆርቆሮ የለበሰ መሆኑን ተገንዝበናል ነገር ግን ተግባር ቤቱ ወደ ውስጥ ገባ ብለን ስንመለከት በአሳዛኝ ደረጃ ነው የሚገኘው ። ሊወድቅ ተቃርቦአል ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያም «አባቶቻችን የተውልን ቅርስ እንዲህ እስኪሆን ድረስ ዝም ብለን መመልከት ባልተገባም ነበር አሁንም በዚህ በዓል አማካይነት የተሰበሰብን ሁሉ የነዕገሌ ሥራ ነው እነርሱ ይሥሩት ይጠግኑት ያድሱት የምንልበት ምክንያት የለንም ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን ይህም ሕንጻ የሠሩት ኢትዮጵያውያን ናቸው እነርሱም የኢትዮጵያውያን ሁሉ አባቶች ወገኖች ናቸው ለሀገራቸው ክብር ለቤተ ክርስቲያናቸው ብልጽግና ለመላ ዓለም በረከትና ረድኤት ሌት ተቀን ለሚጸልዩ አባቶች መገልገያ ሠርተው አልፈዋል ። እኛ ደግሞ መጠበቅ ፣ የጎደለውን ማሟላት የጠመመውን ማቃናት ዋና ዓላማችንና ተግባራችን መሆኑን መዘንጋት አይገባንም ሁላችንም በዚህ በጎ አድራጎት ለተግባር ቤቱ እድሳት መረባረብ ያስፈልገናል ግዴታችንም ነው ። በማለት ጥብቅ ማሳሰቢያ ሰጥተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከዚሁ ጉብኝታቸው በኋላም የንፍሮ ቤቱን የጠላና የወጥ ቤቱን ሁሉ እየተዘዋወሩ ከመጎብኘታቸውም በላይ በየክፍሉ የሚገኙትን አርድዕቶችንም አጽናንተው አባታዊ ምክራቸውን በመስጠት እንዲበረቱ በእምነት ጸንተው እንዲያገለግሉና የጸድቁን የተትረፈረፈ በረከት እንደሚያገኙ ጻድቁ አባታችን በጸሎትና በረድኤት እንደማይለዩአቸው ገልጸውላቸዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ ከዚሁ እያይዘው በጸባቴ አርአያ ሥላሴ አጽብሐ አስተዳዳሪነት ዘመን የተሠራውን የዳቦ ቤት ጎብኝተዋል ። የዳቦ ቤቱ ባሁኑ ጊዜ ሙሉ ድርጅት ሲኖረው በአቅርቦት ማጣት ምክንያት ቆሞ ይገኛል ። አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ግን ብዙ



ቅዱስነታቸው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ትምህርት ሲሰጡ

በረከት እንደተገኘበትና በመቆሙ ምክንያት ደግሞ ከፍተኛ ችግር ማስከተሉም ለቅዱስነታቸው ተገልጾላቸዋል ። በመጨረሻም ቅዱስ ፓትርያርኩ የገዳሙን ጽ/ቤትና የውስጥ ድርጅቱን እየተዘዋወሩ ጎብኝተው እንዳበቁ ወደማረፊያቸው ተመልሰዋል ። ለገዳሙ መርጃ ይሆን ዘንድ ቀደም ሲል ሁለት መቶ ሃምሳ ኩንታል ስንዴና ሁለት ሺህ ብር ርዳታ አድርገዋል ።

ከገዳሙ በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ምሽት ለነሐሴ ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም አጥቢያ በሁለት ሰዓት ደወል ተደውሎ ሊቃውንቱ ማኅሌት መነኮሳቱ ሰዓታት በመቆም እንገተውታል ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከሌሊቱ በዐሥር ሰዓት ከሊቃነ ጳጳሳቱ ጋር ከቤተ ክርስቲያኑ ሲደርሱ የገዳሙ አስተዳዳሪ መነኮሳቱና ዲያቆናቱ ልብሰ ተክህኖ በመልበስ ፣ መስቀል ጽንሐሕ በማስያዝ የሻማ መብራት በማብራት ከአበው መነኮሳት ጋር በክብር ተቀብለዋቸዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ወደ ቤተ መቅደሱ ገብተው የሕሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ ሆነው ስብሐተ እግዚአብሔሩን ሲያዳምጡ አድረዋል ።

ልክ ፲፪ ሰዓት ሲሆን በቅዱስነታቸው መሪነት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተራዳኢነት ሥርዓተ ቅዳሴው ተጀምሮ እስከ ሦስት ሰዓት




www.ethiopianorthodox.org

ድረስ ተካሂዶአል ። ጠቅላላ የቅዳሴው ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ታቦተ ሕጉ ወደ ዐውደ ምሕረቱ ወጥቶአል ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ታቦተ ሕጉን አምርተው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን በመምራት ሥርዓተ ዑደቱ ሲካሄድ ቅዱስነታቸው በቤተ ክርስቲያኑ ግቢና ዙሪያ ለነበረው ሕዝበ ክርስቲያን አባታዊ ቡራኬአቸውን ያስተላልፉ ነበር ።

ታቦተ ሕጉ ሥርዓተ ዑደቱን ፈጽሞ በተመደበለት ሥፍራ እንደቆመ ሊቃውንት በከበሮ በጸናጽል ፣ በዝማሬ ፣ ሴቱ በዕልልታ ፣ ወንዱ በሆታ የደስታ ምስጋናቸውን ለአምላካቸው አቀርበዋል ። ሊቃውንቱ ይሉት ከነበረው ወረባቸው «አብዕዎ ውስተ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ለተክለ ሃይማኖት አቡነ እንዘ ይብሉ ሃሌ ሉያ» የሚል ነው ።

ከዚህ በኋላ ሊቀ ካህናት ክፍሌ ገ/መስቀል በደብረ ሊባኖስ ገዳም እድሳት ኮሚቴ ስም ንግግር አድርገዋል ። ሊቀ ካህናት ክፍሌ ገ መስቀል ስለጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተጋድሎ በሰፊው ከተነተኑ በኋላ ይህ በእርሳቸው ስም የተቸከለው ገዳም ባሁኑ ጊዜ የነበረው እንዳልነበረ እየሆነ መሄዱን አውስተው በተለይም ይህ ከሦላሳ ዓመት በላይ ዕድሜ ያለው ቤ/ክርስቲያን እያፈሰሰ መሆኑንና ብዙ ቅርስና ንብረትም እየተበላሸ ስለሆነ ለተሰበሰበው ሕዝብ የርዳታ እጁን እንዲዘረጋ ተማጽነዋል ። በዕለቱም ከምእመናኑ በርከት ያለ ገንዘብ ተሰብስቦአል ።

ከዚህም ቀጥሎ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፈቃድ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የምዕራብ ጎጃምና የመተከል ሀ/ስብከቶች ሊቀ ጳጳስ ትምህርት ሰጥተዋል ። ብፁዕነታቸው የትምህርታቸው ርእስ «ምንተኑ ትርአዩ ወፃዕክሙ » ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ ? በሚል ተነሥተው እያንዳንዳችን ወደዚህ ሥፍራ ለምን እንደመጣን እናውቃለን ጽድቁንም ጸጋውንም ለማግኘት ነው በውኃ ዳር የተተከለች ተክል በየጊዜው ፍሬዋን ትሰጣለች ተብሎ እንደተጻፈ በዚህ ገዳም ደጅ የሚጸኑ ሁሉም የማያልቅ በረከትና ረድኤት እየተቀበሉ ተጠቅመውበታል ። ይኸውም ጻብአ አጋንንትን ግርማ ሌሊትን ታግሰው በጾም በጸሎት በትሕርምት በስግደት፣ሰውነታቸውን ገዝተው የማያልፈውን ክብር አግኝተው ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙበት አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቢሆኑም በርሳቸው እግር በየጊዜው እዚህ ክቡር ዐፅማቸው ባረፈበት ተማኅፅኖ እያደረጉ በዚህ ቦታ የተጠቀሙ እጅግ ብዙ ናቸው

አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገና ከእናታቸው ማኅፀን ሲወጡ «አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ»ብለው አንድነቱን ሦስትነቱን የመሰከሩ አባት ናቸው ። በመላ ኢትዮጵያም ዞረው አስተምረው ከአጋንንት ቁራኛ እያላቀቁ ወደ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት የመለሱአቸው ሰዎች በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ናቸው።በመጨረሻም አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ዚሁ ገዳም ገብተው በበአት ተከተው እንደቆሙ እግራቸውን ሳያጥፉ የተጋደሉት በግራና በቀኝ ጦር ተክለው እንቅልፍ እንዳይወስዳቸው ነቅተው ተግተው ፣ መከራ በመቀበላቸው ነው እግዚአብሔር አምላክ በዛሬው ዕለት ከዚህ ዓለም ዕረፍት ወዳለበት ቦታ ሲወስዳቸው ሰባት የክብር አክሊላት አቀዳጅቶአቸዋል ። ከዚህም በላይ በስማቸው የጸለየ የተማፀነ ሁሉ በረከታቸውንና ረድኤታቸውን እንደሚያገኝ ቃል ኪዳን ሰጥቶአቸዋል ። ስለዚህ እዚህ የተሰበሰብነው ሁሉ ከበረከታቸው ለመካፈል ከቃል ኪዳናቸው ጸጋና ደህንነት ለማግኘት ነውና በረከታቸውን ረድኤታቸውን ያድለን»በማለት ትምህርታቸውን ደምድመው ከዚህ ቀጥሎ ከቅዱስ ፓትርያርኩ በረከታቸውን ተቀበሉ ብለዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አባታዊ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል ። የቅዱስነታቸው ቃል «በረከቱን ረድኤቱን ይስጣችሁ ፤ዛሬ እዚህ የተሰበሰብነው ሁላችን የጻድቁ የአባታችን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን በረከትና ረድኤት ለመቀበል ነው ፤ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ ተቀብሎ የሰጠን ጸጋና በረከት እናስታውሳለን ።

ዛሬ እዚህ ድረስ የመጣነው አባታችን ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩበት ነው ብለን መርዶ ለመስማት ሳይሆን ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠንን የሞት አሸናፊነት መሠረት በማድረግ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዛሬው ዕለት ሞትን ድል የነሡበት ወይም ያሸነፉበት ዕለት በመሆኑ ይህን የደስታ ቀን ለማክበር ነው የተሰበሰብነው የተሰጣቸው ሰባት አክሊላት የሞት ድል አክሊል ነው ። ሞት ለአባታችን ብቻ ሳይሆን በሌሎች አባቶቻችን ጻድቃን ሰማዕታት ሐዋርያትም ተዋርዶ ድል ሆኖአል ።

ስለዚህ ሞት እንደድሮ ከባድና አስፈሪ ሳይሆን ቀላል ነው ይህም ማለት በእግዚአብሔር አምነው በተጋድሎ ፤ በትሩፋት ጸንተው ለሚኖሩ እንጂ ከእምልኮቱ ተለይተው ከትሩፋት ርቀው ሐልዎቱን ዘንግተው ወይም ከድተው ለኖሩና ለሚኖሩ ግን አሁንም ሞት ከባድ ነው አባታችን ይህ ታላቅ ክብር ለማግኘት የታደሉት ሲያሳድዱአቸው፣ ሲደበድቡአቸው ሲሰድቡአቸው ፣ ሲያስሩአቸው ሲገርፉአቸው መርቀው ይቅር ብለው ተጋድሎአቸውን በትዕግሥት በደስታ ተቀብለው ነው እንጂ እንዲሁ አይደለም

ጻድቁ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዚህ ቦታ ብዙ የጽድቅ ሥራ ሠርተዋል ።

ጻድቅ ማለት ሐቀኛ እውነተኛ ማለት ነው እውነት ማለትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ስለዚህ አባታችን እውነትን በሚሸፍኑ ሰዎች ፊት ቀርበው ስለጽድቅ ወይም ስለእውነት እንዲያውቁ ከፍተኛ ጥረት አድርገው ወደ እምነት መንገድ መልሰዋቸዋል ። ስለዚህ እኛ ደግሞ ከአባታችን የሰማነውን ጽድቅ ወይም እውነተኛ ትምህርት በተግባር መተርጐም ግዴታ አለብን እውነተኛ ትምህርታቸውንም ላልሰሙ እንድናሰማ በዐደባባይ እንድንመሰክር የሚገባን መሆኑ ነው ።

ስለሰላም ጠቃሚነት በየጊዜያቱ በየሥፍራውና በየአስፈላጊው ቦታ ሁሉ ሲነገር ይሰማል ሰምቶ ዝም ማለት ሳይሆን ሁላችንም ሰላም የሚገኝበት የሰላም ጎዳና የሚስተካከልበት መንገድ መጥረግ ማስተካከል ይፈለግብናል ። አለዚያ በኛ መካከልም የሰላም ደብዛ ሊጠፋ ይችላል ሰላምን ለማስፈን እያንዳንዳችን በርትተን መሥራት አለብን ።

አባቶቻችን በሃይማኖታቸው ጠንካሮች ብርቱዎች እንደነበሩ ከሕያው ታሪካቸው እንረዳለን ። ይኸውም ትእዛዙን ሰምተው በቸልተኝነት የማያልፉትና በተግባር የሚተረጉሙ ስለነበሩ ነው ። በየአብያተ ክርስቲያናቱ እየተገኙ ይህ የኔ አይደለም ይህ የኔ ነው ሳይሉ ዐቅማቸውና ዕውቀታቸው በፈቀደ መጠን ሥራው ሁሉ በጋራ ስለሚሠሩ ነው ። ሥምረት ኅብረት ነበራቸው በመካከላቸው ጠብ ክርክር ቢፈጠር እንኳ እስከ ዕርበተ ፀሐይ አያቆዩትም ነበር ። ታርቀው ተራርመው መንፈሳዊ ተግባራቸውን ያከናውኑ ነበር እንጂ ጭቅጭቅና ንትርክ መናናቅና መነታቀፍ ፈጽሞ የለባቸውም ነበር ።

የተወደዳችሁ ምእመናን እንደነዚህ ያሉት ገዳማትና አድባራት ባሉበት ሥፍራ ሁሉ በድካምና በወጭ ሄደን እንሳለማለን መልካም ነው ፤ በረከት ረድኤት ለመቀበል ነው ። ደግሞም መሆን ሚገባው የክርስቲያኖች ተግባር ነው ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኑ ሊፈርስ ነው ያፈሳል ርዳታ አድርጉ እየተባለ ሲነገር እንሰማለን እንጂ ጥቂቱ ሲተባበር አብዛኛው እየሰማ እንዳልሰማ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የሚሄደው ደግሞ እጅግ ብዙ ነው ። ይህ በብዙ ወጭ የተሠራ ቤ/ክርስቲያን ያፈሳል ፤ ሥዕሉም ንዋየ ቅድሳቱም እየተበላሸ ነውና እጃችሁን ዘርጉ ሲባል ዐሥራት ስንኳ ሳናወጣ ዝም ብለን መጥተን ዝም ብለን ብንመለስ ምን ጥቅም አገኘን ? ለመሆኑ ለምንድር ነው እባካችሁ እየተባልን የምንለመነው ? ነፍሳችን ሥጋችን አእምሮአችን ዕድሜአችን ጤናችን ገንዘባችን ቤታችን ሁሉ የማነው ? የእግዚአብሔር አይደለምን ? ሁለመናችን የእርሱ መሆናችን ካመንን እርሱ የሚመሰገንበት እኛም የምንከብርበትንና በረከት ረድኤት የምናገኝበትን ቤት ለምን አንሠራም እንላለን ? ቤተ ክርስቲያኑዋበውስጡ የሚገኘው አልባሳቱ ንያተ ቅድሳቱ ሌሎችም ነባር ቅርሶች የክርስቲያኖች የኛ ናቸው ።

ስለዚህ ሀብታችን ጥሪታችን ቅርሳችን ከመበላሸቱ ከመጥፋቱ በፊት ተግተን ነቅተን መጠበቅ ፣ አስፈላጊ ጉዳይ ሲያጋጥም አስተዋፅኦ አድርጎ መሥራት ማደስ ተግባራችን መሆኑን ተረድተን ፣ ለወደፊቱ እስክንነገር እስክንለመን መጠበቅ የለብንም ። ለሁሉም አስተዋይ አእምሮ ሰሚ ጆሮ ይስጠን በዓሉም የተቀደሰ በዓል ያድርግልን በማለት በዓሉን በቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ እንደተፈጸመ ታቦተ ሕጉ ወደመንበሩ ገብቶ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ቅዱስነታቸውም ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ከሰዓት በኋላ ወደ አ/አበባ ተመልሰዋል ።

## ቅዱስነታቸው የሕግ ተጠያቂዎችን ጐበኙ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን በዓለ ዕርገት ምክንያት በማድረግ ፤

፩ኛ/ በሰንዳፋ
፪ኛ/ በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት
፫ኛ/ በማእከላዊ ምርመራ የሚገኙትን የሕግ ተጠባቂዎችን ከሰዓት በፊትና ከሰዓት በኋላ አንድ በአንድ እየተዘዋወሩ ጐብኝተዋል ። በጉብኝታቸውም ወቅት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትም ተገኝተዋል ።

በመጀመሪያ ልክ ከቀኑ ሦስት ሰዓት ከሃያ አምስት ሲሆን ሰንዳፋ ድሮ አባ ዲና ኮሌጅ እየተባለ ከሚጠራው ሥፍራ ሲደርሱ የኢሕአዴግ ተወካዮች በክብር ተቀብለዋቸዋል።

ቅዱስነታቸው በተወካዮቹ አማካይነት የሕግ ተጠባቂዎች ወዳሉበት አዳራሽ በማምራት በሥፍራው ሲደርሱ የሕግ ተጠባቂዎቹ በክብር ተቀብለዋቸዋል ።

ወዲያውኑ ቅዱስ ፓትርያርኩ ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው የማጽናኛ ንግግር አደረጉላቸው ። ከንግግራቸውም ውስጥ«በዚህ ሰዓት በመካከላችሁ በመገኘታችን ደስታ ይሰማናል፤እኔና እነዚህ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ማለት ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ሊቀ ጳጳስና የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም የበላይ ጠባቂ ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢሳና ጎርጎራ ጳጳስ ቅዱስ ሲኖዶስን ፣ ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን ወክለን እናንተን ለማጽናናትና በዚህ በእመቤታችን ወርኃ ጾም ማብቂያ እንኳን አደረሳችሁ ለማለት ነው የመጣነው »ብለዋል ።

አያይዘውም «ልዑል እግዚአብሔር በዚህ ባላችሁበት ቦታ መጽናናቱን እንዲሰጣችሁ እናምና





www.ethiopianorthodox.org

ለን ። ሰዎች በዓለም በሚኖሩበት ዘመን የተለያዩ ሁኔታዎች ሲደርሱባቸው በትዕግሥት ማሳለፍ ግዴታቸው ነው ። ሁሉን ለማሸነፍ የሚቻለው ግን ሕያው እግዚአብሔርን በሙሉ ልብ በማመንና በትዕግሥት በመቀበል ነው ።

እግዚአብሔር የሁሉ ጌታ መሆኑን ካመንን ሁሉንም በትዕግሥት ለመቀበል ኃይሉን ትዕግሥቱን ይሰጠናል ፤ በቅዱስ መጽሐፍ ማንም ሰው ተጨንቆ በቁመቱ ላይ ስንዝር ለመጨመር ወይም ለመቀነስ እንደማይችል እንዲሁም ከጠጉሩ አንዷን ጥቁር ስንኳን ነጭ ወይንም ነጭዋን ጥቁር ለማድረግ ችሎታ እንደሌለው ይነግረናል ።

ማንም ሰው በሰው ብዛት ወይም ኃይል በጥበብ ሕንዳችም ለማድረግ እንደማይችል በመንፈሳውያን ጠበብት በቅዱሳት መጻሕፍት ተረጋግጦአል ። ነገር ግን የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ ተጽፎአልና ትምክህታችሁን ሁሉ በኃያሉ እግዚአብሔር አድርጉ ።

ስለዚህም ፀአላችሁበት መጽናናት ፤ እግዚአብሔርን በጽኑ እምነት ማምለክና ሙሉ ተስፋ ማድረግ ይገባችኋል ፤ ለቤተ ሰዎቻችሁ ብስጭትና ጭንቀት አታሳዩአቸው ከእናንተ ይልቅ በቤተ ሰዎቻችሁ ላይ ኀዘን መከራና ችግር ሊደርስባቸው ይችላል ።

እንደምታውቁት ሰሞኑን የእመቤታችን ወርኃ ጾም ነበር ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን በጾም በጸሎት ሥጋ ወደሙን በመቀበል ትምህርተ ወንጌልን በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ ሲያደምጡ ሰንብተዋል ።

ስለዚህ በዚሁ በጾሙ መጨረሻ ላይ በመካከላችሁ እንድንገኝ የፈለግንበት ዓላማ በዚሁ በጾሙ መገባደጃ ዕለት እንድትበረቱ ምክርና ትምህርት ለመስጠት መሆኑን ስንገልጽላችሁ ደስ ይለናል » ፤ ካሉ በኋላ ለእመቤታችን በዓለ ዕርገት መዋያ ይሆናቸው ዘንድ ብር ፪ሺህ (ሁለት ሺህ ብር) ሰጥተዋቸዋል ። ከዚህም ሌላ በዚሁ ቦታ ውስጥ በሕመም ተይዘው በመታከም ላይ የሚገኙት በሽተኞችን አንድ በአንድ ጐብኝተውና አጽናንተው ቡራኬ ሰጥተው ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ይህ ታሪካዊ ጉብኝት በመቀጠል ፰ ሰዓት ከሃያ ሲሆን አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው ወህኒ ቤትና ለሕግ ተጠባቂዎች ማጽናኛና ምስካዩ ኅዙናን እንዲሆን ታስቦ በመሠራት ላይ ያለውን የደብረ ምሕረት ቅ/ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ሥራና ውስጣዊ ይዘት እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል ፤ ይኸውም በቀጠሮ የሚገኙትንና በዕድሜአቸው መጠን ከመጥፎ አድራጎታቸው በትምህርትና በምክር በመታረም ያሉትን የሕግ ተጠባቂዎች የሆኑ ወጣቶችን አንድ በአንድ እየተዘዋወሩ አባታዊ ትምህርትና ምክር ሰጥተዋቸዋል ።

ከሰጡት ምክር ውስጥ እያንዳንዳችሁ እዚሁ የገባችሁ በተለያየ ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው ይኸውም በራስ ፍላጎትና በጓደኞች ገፋፊነት ሊሆን ይችላል ። በዚህ ወጣትነት ዕድሜአችሁ በብልሹ ጠባይ ምክንያት እዚህ መዋሉ እያንዳንዳችሁ ሳታዝኑና ሳይቆጫችሁ እንደማይቀር የታመነ ነው ። ነገር ግን አሁንም ልታጠኑት የሚገባችሁ ከዚሁ ሐሳብ የተለየ መሆን አለበት ፤ በራሳችሁ መጠየቅ ይገባችኋል ። ለምን እዚህ ገባሁ የሠራሁት ስሕተትስ ምን ነበር ? እስከዚህ የገፋፋኝስ ማን ነበር ? ብላችሁ ከሕሊናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ አሁን እግዚአብሔር ያወጣኝ እንደሆነ ዳግም እንዲህ ዓይነቱ ሥራ ላልሠራ በሙሉ ልቤ ወስኛለሁ ብላችሁ የድሮውን መጥፎ ድርጊታችሁን በሙሉ ሠርዛችሁ እንደ አሮጌ ጨርቅ ከላያችሁ ላይ አውልቃችሁ ጥላችሁ በሙሉ ልባችሁ ንስሐ ገብታችሁ በንስሐ ታድሳችሁ ለወደፊት አዲሱ ኑሮአችሁን ለመቀጠል ተዘጋጅታችሁ መቀመጥ አለባችሁ ።

ይህ ፤ ሥፍራ ትምህርት ቤት ነው አድራጎታችሁን ሁሉ የምትመረምሩበት የምትመለከቱት መስታወት ነው ። መንግሥት መሐሪ ነውና ነገ ምሕረት አድርጎላችሁ ስትፈቱ ተመልሳችሁ በእንደዚህ ዓይነቱ መጥፎ ስሕተት እንዳትገቡ መጠንቀቅ ይገባችኋል ። በዚህ የልጅነት ዘመናችሁ በማይረባ ለጆሮ በሚቀፍ ነገር እዚህ ገብታችሁ ወርቃማ ጊዜአችሁን በርካሽ ተግባር ማባከን አይገባችሁም ።

በዚሁ ሥፍራ ሁናችሁ ጊዜአችሁን በከንቱ አታባክኑት ። የተማረ ያስተምር ፤ ያልተማረ ይማር እንደተባለው እርስ በርሳችሁ ማስተማርና መማር ግዴታ አለባችሁ በማለት ሰፊ ትምህርት ከሰጡ በኋላ ለእመቤታችን በዓለ ዕርገት መዋያ ይረዳቸው ዘንድብር፪ሺህ፭፻ (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) ሰጥተዋቸዋል ።

ከስድስት ተኩል እስከ ዘጠኝ ሰዓት በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ካስቀደሱ በኋላ በቀጥታ ወደ ማዕከላዊ ምርመራ በማምራት ከዚያ የሚገኙትን የፖለቲካ እስረኞችን አንድ በአንድ ከመጎብኘታቸውም በላይ አጽናኝ ምክርና አባታዊ ትምህርትንም ፤ አሰምተዋቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ለተጠባቂዎቹ ካስተላለፉላቸው መልእክት በጥቂቱ «ማንኛውም ነገር ያልፋል ሁሉንም በትዕግሥት መጠበቁ ግን ትልቅ አስተዋይነት ነው ። ሰው ደካማ ነው ሁሉን የማድረግ ኃይልና ሥልጣን ያለው ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው ።

ዛሬ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ሁነን በመካከላችሁ ለመገኘት የፈለግንበት አንድ ምክንያት አለን



ይኸውም መጽሐፍቅዱሳችን ታስሬ አልጠየቃችሁኝም ፤ ታምሜ አልጎበኛችሁኝም የሚል አምላካዊ ቃል ስላለበት ልንጎበኛችሁ ልናጽናናችሁና ልናበረታታችሁ ነው የመጣነው ።

ይህም ሁሉ ለማድረግ የተቻለው በሽግግሩ መንግሥት ፈቃድ ነው ፤ ይህ የመጀመሪያ ሥራ ነው ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ ይህንኑ የተቀደሰ ተግባር ለማከናወን ስለፈቀደልን እናመሰግነዋለን

ማንም ሰው የደስታ ተካፋይ ብቻ አይደለም ፤ የችግርና የመከራ ተካፋይም እንዲሆን ግዴታው ነው ። ሰው ደካማ እንደመሆኑ መጠን ለመጽናት ፤ ማንኛውንም ችግር ለመቋቋም እንዲችል እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ አለበት ። ከእግዚአብሔር ጥበቃ የተለየ ሰውና ከገዛናም የተለዩ እጸዋት አንድ ናቸው ፤ ከእግዚአብሔር የተለየ ሰው መከራ ሲደርስበት ሊጽናና ሊታገስና ሊበረታታ አይችልም ፤ ዕጸዋቱም እንደዚሁ ዝናም ካላገኙ ከሐሩር ከፀሓይና ከቍር የተነሣ ደርቀው ይወድቃሉ ፤ ለእሳት ይዳረጋሉ ።

ሰው የሚኖረው በመብል ብቻ አይደለም ፤ በእግዚአብሔር ቃል ጭምር እንጂ እንደተባለው ያሳለፍነው ሳምንታት ምግበ ነፍስ ለማግኘት በጾም በጸሎት መሰንበታችን የታወቀ ነው ። ስለዚህ አሁን ሱባኤው ስለተፈጸመ እንኳን ለእመቤታችን በዓለ ዕርገት በሰላም አደረሳችሁ ልንላችሁ ነው የመጣነው ። በማለት ጸሎተ ቡራኬ ካደረጉላቸው በኋላ ለበዓሉ መዋያ ይሆናቸው ዘንድ ብር ፩ሺህ፭፻ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ለግሰዋል ።

እንዲሁም ነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም በሆሎታ የሚገኙ የፖለቲካ ተጠባቂዎችን ጐብኝተዋል ። በጉብኝቱም ወቅት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተገኝተዋል ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከሆሎታ ገነት ሲደርሱ የኢሕአዴግ ተወካዮች በክብር ተቀብለዋቸዋል ። የሕግ ተጠባቂዎች በታላቅ ደስታና በከፍተኛ ስሜት አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ሕዝቡ በተሰበሰበበት አዳራሽ ተገኝተው ጉባኤውን በጸሎተ ቡራኬ ከከፈቱ በኋላ ትምህርተ ወንጌልን በሰፊው ሰጥተዋል ። ሕዝቡ ሁሉ ባለበት ሆኖ ፈጣሪውን ማምለክ እምነቱንም አጽንቶ መጠበቅ ይገባዋል ብለዋል ።

በድሮ ጊዜ እንደዚህ ያለ ነጻነት አልነበረም ፤ ባንድ ላይ ተሰብስቦ መማር ማስተማር የሚቻልበት ጊዜ እንዳልነበረ የታመነ ነው ። ዛሬ ግን የፈለግነውን ለማግኘት ሀሳባችንን ለመግለጽ ጥያቄአችንን ለማቅረብና መልስ ለማግኘት በመቻላችን የሽግግር መንግሥቱን ክልብ እናመሰግናለን ። እያንዳንዱ ዜጋ በእምነቱ ማንም ጣልቃ ገብቶ ሊያስጨንቀው ወይም ሊያስለቅቀው እንደማይችልና የመብት ነጻነት በየመልኩ ለመጎናጸፍ በመብቃቱ ደስታ እንደሚሰማው የታመነ ነው ። ይህንን ሁሉ ለማየት ላበቃን አምላክ ምስጋና ይድረሰው እንላለን ።

ስለዚህ እናንተም በዚሁ ጊዜ በእምነታችሁ መበርታት ፤ መጠንከር ይገባችኋል ፤ ለዚህም በቤተ ክርስቲያን ስም አደራ እንላችኋለን ፤ በማለት አበረታትተዋቸዋል ተጠባቂዎቹም ቅዱስነታቸው በስጡአቸው ተስፋ መሠረት ለወደፊቱ በእምነታቸው እንደሚጠነክሩ ገልጸዋል ፤ አያይዘውም የሃይማኖታችን ቅዱሳት መጻሕፍት የቤተ ክርስቲያናችን ጋዜጦችና መጽሔቶች ቢላኩልን ሃይማኖታችንን ለማጠንከር ዝግጁዎች መሆናችንን በድጋሚ እንገልጻለን ብለዋል ።

በዚህም ቦታ ላይ ለሚገኙት የሕግ ተጠባቂዎች ቅዱስነታቸው ብር ፪ሺህ-(ሁለት ሺህ ብር)ርዳታ አድርገውላቸዋል ። ቅዱስነታቸው አስፈላጊውን ሁሉ በተቻለ መጠን ጥረት እንደሚደረግ አረጋግጠውላቸዋል ፤ በመጨረሻም አባታዊ ምክራቸውን ሰጥተው እንዳበቁ ጉባኤውን በቃለ ቡራኬ ፈጽመው ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል ። የሕግ ተጠባቂዎችም ሊወጡበት ካልተፈቀደው ቦታ አልፈው ቅዱስነታቸውን በደስታ በጋለ ስሜትና በጭብጨባ ከናፍቆት ጋር ሸኝተዋቸዋል።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስነታቸው በተገኙበት የቅዱስ ሩፋኤል በዓል

# በደብረ ዘይት ተከበረ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም የቅዱስ ሩፋኤልን በዓል ምክንያት በማድረግ ደብረ ዘይት በሚገኘው ቤ/ክርስቲያን ተገኝተው ፤ ቃለ ምዕዳንና አባታዊ ቡራኬ ሰጥተዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ ጳጉሜን ፪ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ከአ/ አበባ መንበረ ክናው ተነሥተው ለ፲፪ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ደብረ ዘይት ቅዱስ ሩፋኤል ቤ/ክርስቲያን ሲደርሱ የደብሩ አስተዳዳሪ መምህር ሙሴ ከሰ/ጉ/ አባላት ልብሰ ተክህኖ ከለበሱ ፤ የወርቅ መስቀልና ጽንሐሕ ከያዙ ካህናትና ዲያቆናት ሊቃውንትና መዘምራን በብዙ ሺህ ከሚቈጠሩ የከተማው ነዋሪ ምች ምእመናን ዩኒፎርም ከለበሱ የሰንበት ት/ቤት መዘምራን ሆነው በዝማሬ ፤ በሆታና በእልልታ ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ሊቃውንቱ «ተሰመይከ ቅ/ጳውሎስ ስምዓ ጽድቅ ኮንከ ወበእንተዝ ተሰመይከ ቅዱስ ጳውሎስ አበ ኵሉ አባ ቅዱስ ጳውሎስ አስተጋብነነ በስብሐተ እግዚአብሔር» እያሉ አለዝበው በሽብሻቦ አሰምተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ካህናቱ ፤ ምእመናኑ ና ምእመናቱ እንዲሁም ወጣቶቹ በነቂስ ወጥተው በደማቅ ስነ ሥርዓትና በክርስቲያናዊ ሰልፍ በዝማሬ ና በውዳሴ እኛን ለመቀበል ተዘጋጅታችሁ ስለጠበቃችሁን እግዚአብሔር በረከቱን ያድላችሁ» ካሉ በኋላ ይህ ከፍተኛ ዝግጅት ምን ጊዜም የማይረሳና ከሕሊናችን የማይፋቅ መንፈሳዊ ፍቅር የተመላበት ስለሆነ ለደስታችን ወሰን የለውም ብለዋል ። አያይዘውም ይህ መልካም ሥርዓትና የሃይማኖታችን እምነታዊ ባሕል ለልጆቻችን ማውረስ ተገቢ መሆኑን መዘንጋትና ቸል ማለት አይገባንም እኛ ኢትዮጵያውያን የዓለም ሕዝብ ሲያደንቀን (ሲደነቅብን) የሚኖር ባሕል አለን ። ስለሆነም ይህ ሃይማኖታዊ ባሕላችን በበለጠ ማዳበር ፣ ማክበርና መጠበቅ አለብን ለዚሁም እግዚአብሔር አምላክ በረከቱን ረድኤቱን ይስጠን እግዚአብሔር ይባርካችሁ በማለት ስነ ሥርዓቱን በጸሎተ ቡራኬ ደምድመዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ላይ ከተዘጋጀላቸው ማረፊያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን አምርተው እዚያው እንደደረሱ ፣ የደብሩ አስተዳዳሪ ከሰበካ ጉባኤ አባላት ልብሰ ተክህኖ ከለበሱ ካህናትና ዲያቆናት ከሰንበት ት/ቤት መዘምራን የሻማ መብራት በመያዝ ከፍ ያለ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ቅዱስነታቸውም ወደ ቤተ መቅደሱ ገብተው የሕሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ በተዘጋጀላቸው መንበር ተቀምጠዋል ። ከንጋቱ ፲፪ ሰዓት ሲሆን በቅዱስነታቸው መሪነት በብፁዕን ሊቃነ ጳጳሳት ተራዳኢነት ሥርዓተ ቅዳሴው ተጀምሮ እስከ ሁለት ሰዓት ተኩል ድረስ ተካሂዶአል ።

ይህ በዚህ እንዳበቃ ታቦተ ሕጉ ለአራት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ወደፀውደ ምሕረቱ ወጥቶአል ። ቅዱስ ፓትርያርኩም ታቦተ ሕጉን አምርተው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን በመምራት ሥርዓተ ዑደቱ ተከናውኖ በተዘጋጀለት ሥፍራ እንደቆመ መዘምራኑ ለዕለቱ የተዘጋጀውን ግሥ ቃኝተው ለ፳ ደቂቃ ያህል አሸብሸበዋል ። ከዚህም በማያያዝ በቅዱስ ፓትርያርኩ መልካም ፈቃድ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ ትምህርት ሰጥተዋል ።

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ከሰጡት ትምህርት «ዛሬ የተቀደሰ ሥራ ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ዕለት ነው ። ቅዱስ ሩፋኤል ከቅዱሳን ሊቃነ መላእክት ማለት ከቅ/ሚካኤልና ከቅ/ገብርኤል ሦስተኛ ነው ። እግዚአብሔር አምላክ ስምህን ንገራቸው ብሎ ለቅ/ሩፋኤል ቢነግረው እኔ ቅ/ሩፋኤል ነኝ እግዚአብሔር የፈቀደልኝ የመላእክት አለቃ ሥልጣን አለኝ ሲል ማንነቱንና ደረጃውንም ገልጾ እንደነገራቸው በመጽሐፈ ድርሳኑ ተጽፎአል ።

ቅዱስ ሩፋኤል በእውነት ሠርተው በእምነት ከሠሩበት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የሚያቀርቡ ምእመናን ሁሉ ጸሎታቸውንና መሥዋዕታቸውን እየተቀበለ በቅድመ እግዚአብሔር የሚያሳርግ (የሚያቀርብ) ታላቅ መልእክተኛ ነው ። ነገር ግን እኛ መሥዋዕታችን ጸሎታችንና ልመናችን ሁሉ ከማቅረባችን በፊት አስቀድመን ራሳችንን በራሳችን መጠየቅ አለብን ። ወገኖቻችንን አስቀይመን ይሆን? ብለን መመርመርና ካለብን ቅያሜ ነጻ ወጥተን የፈለግነውን መሥዋዕት ማቅረብ ይገባናል ብለዋል።

ቀጥሎም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መባህን ከማቅረብህ በፊት ከሰው ተጣልተህ እንደሆነ አስቀድመህ ታረቅ ይላል ዛሬ የተደረገበት በዓል ነው ። አንዱ ፣ ቅዱስ ሩፋኤል ሁለተኛ ካህነ ዓለም መልከ ጼዴቅ ፣ ሦስተኛ የዘመኑ መጨረሻ አራተኛ ርኅወተ ሰማይ ይባላል ። ሰማያት ሁሉ የሚከፈቱበት ወይም ተከፍተው የሚውሉበት ቀን ነው በማለት አብራርተዋል ተንትነውም አስተምረዋል።

አያይዘውም ብፁዕነታቸው ሲናገሩ በዛሬው ዕለት ሰማያት የተፈቱበት ምክንያት የኛን መሥዋዕትና ጸሎት (ልመና) በቅ/ሩፋኤል አማካይነት እንዲያርግልን ነው ። ከዚሁ በዓል ጋር ዛሬ አብረን የምናየው የዓመቱ መጨረሻ ቀን መቃረቡ ነው ። ሁላችን እንደምናውቀው በዚሁ የዘመን መለወጫ ቀን በፊት የእያንዳንዱ ሥራ የሚመዘንበት ነው ። እንዲሁ የዓመቱን በጀት በትክክል በሥራ ላይ ውሎ እንደሆን ወይም ገንዘቡ የትም ባክኖ ቀርቶ እንደሆን ይመረመራል ። በቸልተኝነት ገንዘቡን አባክነው ያለፉት ሰዎች በተቈጣጣሪ ተጣርቶ ነጻ ወይም ባለዕዳ የሚሆኑበት ወራት ነው ።

በመንፈሳዊ ረገድ ደግሞ እያንዳንዱ ክርስቲያን ባመት ውስጥ ምን እንደሠራ መንፈሳዊ ሕይወቱን የሚመረመርበት ወራት ነው በዚሁ በወርኃ ጳጉሜን ባለፈው ዓመት ውስጥ ምን ስሕተት ጥፋት ሠራሁኝ አምላኬ በምን ዓይነት ጥፋት አስቀይሜው ይሆን ? እያልን ራሳችንን በራሳችን እየመረመርን በእንብአ ንስሐ ከፈጣሪያችን ጋር የምንታረቅበት ሳምንት ነው ። ስለዚህ አዲሱን ዓመት በአዲስ ሕይወት ለመቀበል በአድራጎታችን ተጸጽተን ንስሐ ገብተን ከፈጣሪያችን ታርቀን መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ያብቃን በማለት ትምህርታቸውን አጠቃለለዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ለሕዝቡ አባታዊ በረከት እንዲያስተላልፉላቸው ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ አሳስበው እንዳበቁ ቅዱስነታቸው ከዚህ የሚከተለውን ቃለ ምዕዳን ሰጡ «ከሩቅም ከቅርብም የመጣችሁ ምእመናን ምእመናት ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ እንኳንም በዓሉን ለማክበር አበቃችሁ ካሉ በኋላ በዓሉን በተመለከተ በብፁዕነታቸው በሰፊው ትምህርት ተሰጥቶአል ።

ስለ ሃይማኖታችን አከባበር ስለ ባሕላችን አጠባበቅ ያዩ አንዳንድ መንፈስ ደካሞች ከልባችን አንቅተን እንዲሁ በስሜት እንደምንሰበሰብ ይመስላቸዋል ። ነገር ግን እኛ እምነታችንም ሆነ ባሕላችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጣ አይደለም ።

እግዚአብሔር\አስቀድሞ ሰማይንና ምድርንም ከመፍጠሩ በፊት መላእክትን እንደፈጠረ ፣ ከዚያም ሰዎችንና ሌሎች ፍጥረታትንም ፣ ሁሉ ፈጥሮአል ። እንግዲህ እኛ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እንደማይቻለን ብዙ ማስረጃዎች ተጽፈዋል ። ስለዚህ መላእክት በእርሱና በሰዎች መካከል የሚቆሙ አስታራቂዎች ጸሎታችን ምህላችን መሥዋዕታችንና ልመናችን ሁሉ ወደፈጣሪ ፊት አቅርበው የሚያማልዱን መላእክት እንደሆኑ የተረጋገጠ እውነት ነው።

መላእክት በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል እንደሚቆሙ መጻሕፍት ይነግሩናል ። እግዚአብሔር በዓለማት ፣ በባሕርና በቀላያት የማያውቀው ነገር ምንም የለም ሁሉንም የፈጠረና ያስገኘ እርሱ ብቻ ነው ። ታድያ እኛ የምናደርገውን ነገር ሁሉ የእግዚአብሔርን ኃያልነት ሁሉን ቻይ ነትና አዋቂነት የሚነቅፍና የሚያጎድፍ አስመስለው ስም የሚያጠፉ ካሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው ለማለት አያስደፍርም ።

እኛ ኢትዮጵያውያን እንዲህ እግዚአብሔርን ስናመሰግን ኑረን ሌላ ጠባይ ማሳየት የለብንም እግዚአብሔር ሁሉንም እንዲሁ ወደደ ስለዓለም ሰዎች ሁሉ ሕይወቱን አሳልፎ ለሞት ሰጠ የሚል በቅዱስ ወንጌል ተጽፎአልና ነፍስ ሁሉ ከእርሱ ተገኘች ለእርሱ ትገዛለች ።

እግዚአብሔር ዘመናትን አሳልፈን ዘመናትን ለመቀበል ያበቃናል ። ሆኖም ግን የእኛ የሆነ እኛ ያስገኘነው ምንም የለንም ይህ ቃል በየጊዜያቱ ደጋግሜ እናገረዋለሁ ሁሉም የእግዚአብሔር ነው እኛም የእግዚአብሔር ነን ። ሌላው በዚህ ሰሞን የምናስታውሰው ከአባቶች ሲነገርና ሲታወስ የኖረው ዐቢይ ጉዳይ አለ እርሱም በነዚህ ሳምንታትና ቀናት የምጽአት ጊዜያት እንደሆነ ነው ። «እግዚአብሔርሰ ገሃደ ይመጽእ ወአምላክነሂ ኢያረምም እሳት ይነድድ ቅድሜሁ» ይላል ። እግዚአብሔር ዛሬ ፣ ነገ፣ ተነገ ወዲያ ማንም በማያውቃትና ባልጠበቃት ሰዓት ይመጣል፣ የሚያውቅ የለም እንጂ ይመጣል ። ነገር ግን በዚያን ጊዜ ከፈጣሪያችን ፊት በመንቀርብበት ሰዓት የታዘዝነውን ሠርተን በአግባቡ ፈጽመን እንገኝ ይሆን ?

እግዚአብሔር ያዘዘንን ትእዛዛት ሁሉ ከባዶች አይደሉም ። መሥራት ስንችል ስላልሠራናቸው ግን ለወቀሳ ለከሰሳ ተመቻችተን ተቀምጠናል ። አላበላችሁኝም አላጠጣችሁኝም ፤ አላለበሳችሁኝም አልጎበኛችሁኝም አልጠየቃችሁኝም ፤ ይላል ሌላው ቢከብድብን እንኳ አንድ ብርጭቆ ውኃ ትልቅ ዋጋ እንዳለው ተጽፎ እያለ ቀዝቃዛ ብርጭቆ ውኃ ሰጥቶ ሕጉን የፈጸመ ሰው ስንት እንደሆነ ባለ ቤቱ ብቻ ነው የሚያውቀው ።

እኛ ክርስቲያኖች ክርስቲያን የሚለውን ስም ያገኘነው ከሰላሙ ባለቤት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ስለዚህ እኛ ኑሮአችንና ሕይወታችንም ሁሉ በሰላም የተመሠረተና የሰላም ድምፅ ያለበት እንዲሆን ይገባል ።

በአንድ ክፈል (ደብር)የሚኖሩ (የሚያገለግሉ) ካህናት ለሌላው ፤





www.ethiopianorthodox.org

አርአያና ምሳሌ መሆን አለባቸው ምእመናን መልካም ምሳሌ አያሳዩም ማለቴ አይደለም ። ነገር ግን የካህናት ምሳሌ ነት ከምእመናን የተለየ በሩቅ የሚታይ መልካም ምሳሌ መሆን አለበት ማለቴ ነው ።

አንድ ሰው በአንድ ቦታ ለሰላም ጠንቅ ሆኖ ከተገኘ ከቦታው መነሣት አለበት ፤ በሁለት ወይም በአንድ ቤተሰብ በልጆች መካከል ጠብ ፡ ክርክር ፥ ቢነሣ ወላጅች ፥ ዝም ብላችሁ ነው የምታዩአቸው? ከመካከላቸው ገብታችሁ አንተ ተው አንተም ዝም በል አንተ ከዚህ ተቀመጥ ፣ አንተ ደግሞ ከዚህ እዚያ ሄደህ ተቀመጥ ብላችሁ አትገላግሉአቸውም ? እንደዚሁም ሁሉ ቤ/ክርስቲያን በአንድ ደብር ልጆችዋ ጠብ እንሥተው ቢጣሉ አንዱ ወዳንዱ አዘዋውራ የማስቀመጥ መብት አላት ፤ ይኸውም ለምእመናን ለእናንተ በማሰብ ነው ። እንዳትረበሹ ሰላም እንዳታጡና እንዳትጨነቁ በማሰብ ነው ። አንድ ነገር ሲፈጸም ኑና ንገሩን ሀብታችን ጉልበታችን የቤተ ክርስቲያናችን ክብርና ሞገስ እናንተ ስለሆናችሁ ጉዳዩ ወደ እናንተ ነው ይዘነው የምንቀርብ ፤

ክህናት መካከለኞች ናችሁ ሁሉንም በአንድ ዓይነት ማየት አለባችሁ አንዱን ጠልቶ አንዱን የሚወድ ካህን ካህን አይደለም አድላዊ ነው ። አድራነቱን የዘነጋ ካህን ከቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ወጥቶ በመገኘቱ ክህነቱም ሊያዝበት ወይም ሊወሰድበት ይገባል።

ሰማዩን የዘጉ እነ ኤልያስ ፥ ባሕሩን የከፈሉ እነሙሴ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የቆሙ የእግዚአብሔርና የሕዝብ አገልጋይነታቸውም አረጋግጠው ሳያዳሉ ሳይወላውሉ በእምነታቸው ጸንተው በመሥራታቸው ነው ። ታላላቅ አባቶች በእምነተ ጽኑነታቸው በሰሩት ተአምራትና ድንቅ ሥራ ታይቶ ተገምቶ ሰው ትንሹ እግዚአብሔር ነው እንዲባል አድርገውታል ስለዚህ እኛ በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠርን እግዚአብሔርም በሰጠን ጥበብና ዕውቀትም ብዙ አስደናቂ ሥራ ለመሥራት የምንችል ከቡራን ፍጥረታት ስለሆን ከኃጢአትና ከጥፋት መራቅአለብን» ። በማለት ቃለ ምዕዳናቸውን አስተላልፈው በዓሉን በጸሎተ ቡራኬአቸው ተፈጽሞአል ። ቅዱስነታቸውም ከምሳ በኋላ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጳጉሜን ፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ከሰዓት በኋላ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር የአስኮ ደብረ ገነት ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ ክርስቲያን ሕንጻ ሥራ ጎብኝተዋል ።

ቅ/ፓትርያርኩ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር እንደደረሱ የደብሩ አስተዳዳሪ መምህር ኃይለ ኢየሱስ እጅጉ ከሕንጻው አሠሪ ኮሚቴ አባላት አንዱ አቶ ጌታቸው መኩሪያና ሌሎችም እንዲሁም ከደብሩ ካህናት ከአካባቢው እምመናንና ምእመናት ከሰንበት ት/ቤት መዘምራን ጋር በሰልፍ ሆነው ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ቅዱስነታቸውም ወደ ቤተ መቅደሱ ገብተው የሕሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ በመሠራት ላይ ወዳለው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በማምራት ሕንጻውን በምሥራቅ ፣ በምዕራብ ፤ በሰሜንና በደቡብ እንዲሁም ለንዋያተ ቅድሳት ማኖሪያ ተብሎ በስተምሥራቅ የሚገኘውን ምድር ፤ ቤት እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል ። በደብሩ አስተዳዳሪና በሕንጸ አሠሪ ኮሚቴዎችም ማብራሪያና ገለጻ እየተደረገላቸው አንድ በአንድ ተመልክተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አራኑ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሕንጻው ጉብኝት እንደፈጸሙ የሕንጸ አሠሪ ኮሚቴ ጽ/ቤትን ጎብኝተዋል ። ስለቤተ ክርስቲያኑ መሠረተ ፕላን በአቶ ጌታቸው መኩሪያ አማካይነት በቅደም ተከተል ዝርዝር ሁኔታውን ተመልክተዋል ። ቀጥሎም በዘመናዊ አሠራር የተዘጋጀውን የውኃ ማጣሪያ አባሎቹ አንድ በአንድ በማስረዳት አስጎብኝተዋቸዋል ።

ቅዱስነታቸውም ጉብኝታቸውን በመቀጠል በደብሩ ሰበካ ጉባኤ አማካይነት የተሠራውን ዘመናዊ አደራሽ ተመልክተዋል ። ቅዱስነታቸው ከአዳራሹ ለተገኙት ምእመናንና የሰንበት ት/ቤት መዘምራን በሰጡት ቃለ ምዕዳን «በዚህ ደብር የምትሠሩት ከባድ ሥራ በማየታችን በጣም ደስ ብሎናል። በየኢትዮጵያችን ያለው መንፈሳዊ እሽቅድድም በጣም የሚያስደስትና የሚያስቀና ነው ። ስለዚህ ይህ በዚህ ቤ/ክርስቲያን የሚካሄደው ሥራ ሁሉ በሁሉም ዘንድ የሚደነቅና ሰፊ የሥራ መስክ እንደተከፈተም ነው የምንመለከተው፣በዚሁ መሠረት ወጣቶችም በአባቶታችሁ ሥራ ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖራችሁ ይገባል ። ወላጆቻችሁ እንዲህ አድርጉ ይህን አምጡ ሲሉአችሁ ትእዛዛቸውን ተቀብላችሁ መፈጸም አለባችሁ ወላጆችም ልጆቻችሁ የማይከብድባቸውን ሥራ እንዲታሠሩአቸው ይገባል ። ከባድ ሥራ ልጆቹን ያስመርራቸዋልና በውሉድና ወላዲ መንፈስ እንድትመሩ አደራ እንላለን ።እንግዲህ እኛንም እንለያችሁም በየጊዜው እየመጣን እንጎበኛችኋለን በርቱ ጠንክሩ የሚያስፈልገውንም ከመርዳት ወደኋላ አንልም በማለት ቡራኬ ሰጥተው ወደ መንበረ ካናቸው ተመልሰዋል ።



# ቅዱስ ፓትርያርኩ ከኤርትራ ለመጡ ተፈናቃዮች ብር ፳ ሺህ ርዳታ ሰጡ ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከየመምሪያው ኃላፊዎች ጋር በመሆን ከኤርትራ ወደ አዲስ አበባ የመጡትን ተፈናቃዮች መስከረም ፮ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ።

፩ኛ/ በመሳለሚያ

፪ኛ/ በኮልፌ

፫ኛ/ በልደታ

፬ኛ/ በቃልቲ

፭/ በሾላ

፮ኛ/ በቀበና

፯ኛ/ በእንግሊዝ ት/ቤት አጠገብ

፰ኛ/ በጃን ሜዳ የሚገኙትን ሁሉ እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል ።

በጉብኝቱም ወቅት አጽናኝ ምክርና አባታዊ ቃለ ምዕዳን ሰጥተዋቸዋል ።

ከዚህም በላይ የመስቀልን በዓል ምክንያት በማድረግ ለተፈናቃዮቹ ለበዓሉ ምሳ ይሆናቸው ዘንድ ብር ፳ ሺህ (ሃያ ሺህ ብር) ርዳታ አድርገውላቸዋል ። ለወደፊቱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ሲል ለወገኖችዋ ታደርግላቸው ከነበረው ርዳታ በበለጠ የምትረዳቸው መሆንዋንና በሀሳብም በጸሎትም እንደምታስባቸው ቅዱስነታቸው ሙሉ ተስፋ ሰጥተዋቸዋል ።

ተረጅ ወገኖችም ከመንደራቸውና ከቀያቸው ተፈናቅለው ከተሰደዱበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ፈጥና በመድረስ ተገቢውን ርዳታ ስታደርግላቸው መቆየትዋንና ወገናዊ እንክብካቤዋንም ያልተለያቸው መሆኑን ገልጸው ባሁኑ ወቅት ደግሞ ርእሰ ቤተ ክርስቲያን የሆኑት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በተሰጣቸው መጠለያ እየተገኙ ፥ በረከታቸውንና አጽናኝ ትምህርታቸውንም ስለሰጡአቸው የተሰማቸውን ደስታ ከፍ ባለ ምስጋና በቅዱስነታቸው ፊት ገልጸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከኤርትራ ተፈናቅለው ለመጡ ወገኖቻችን ከላይ በተጠቀሱት የመጠለያ ጣቢያዎች እየተዘዋወሩ በጎበኙበት ወቅት በጉብኝቱ ጊዜ በሰጡት አጽናኝ ቃለ ምዕዳን «የተወደዳችሁ ወንድሞችና እኅቶች ልዑል እግዚአብሔር እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላምና ጤና አደረሳችሁ አዲሱን ዓመት የሰላም የጤንነት ፥ የአንድነት ዘመን ያድርግልን እግዚአብሔር ቸር ነውና የለመንነውን ሁሉ እንደሚያደርግልን እንተማመናለን ። ባለፉት ዓመታት ብዙ ችግር ፤ መከራና ሥቃይ አሳልፈናል ። ሰዎች ምን ጊዜም ቢሆን በዓለም ላይ በሚኖሩበት ወቅት ሁሉ ነጻነት ፥ ፍትሕ ርትዕ የጎደለበት ዘመን ሳያጋጥማቸው አያልፉም ። ይህም ዓይነት ከፉ ዘመን በጊዜአችን ተከስቶ አል በኛም ላይ ደርሶአል ።

አሁን ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ሁሉም ተወግዶልናል ፥ በሰላም በጤና እንገኛለን ። ራሳችንን ለመርዳትም ነጻነትና እኩልነት አግኝተናል ከዚያ እጅግ የተሻለ እንደ ሆነም ሁላችን እንገነዘበዋለን ። ባሳለፍናቸው ዘመናት ለመናገር እንኳ የማይቻልበት ዘመን እንደነበረና ችግርንም ለመወያየት አስቸጋሪ ጊዜ እንዳሳለፍን የትናንትና ትዝታ ነው ።

ዛሬ ግን እያንዳንዱ ስለራሱ በራሱ ለመከራከር ፤ ለመናገር መብት አለው ። እናንተም ባሁኑ ጊዜ ችግራችሁን እንደልባችሁ ለማመልከት ለመናገርና ሀሳባችሁንም ለመግለጽ በመቻላችሁ ጉዳያችሁ ሁሉ እየተታየላችሁ ነው ። ለወደፊቱም ቢሆን እኔም ከእናንተ አልለይም ለማጽናናት ሀሳባችሁንም ለመካፈል እየመጣሁ እጠይቃችኋለሁ ።

የሰው ልጅ ሁሉም እኩል ነው እያንዳንዳችን ምንጫችን መገኛችን አንድ ነው ስለሆነም አብረን መወያየት ችግር ሲደርስብን ባንድ ላይ ሆነን ማስወገድ ለችግሩ መፍትሔ መፈለግ ይገባናል ።

ችግር ከሰው ልጆች የተለየበት ጊዜ የለም ምን ጊዜም ቢሆን አይለይም በችግር ያልተፈተነ ሰው ደግሞ ሰው አይደለም ። በችግር የተፈተነ የሌላውን ችግር ያውቃል እኔ ከእናንተ የበለሥ ፈተና ተቀብያለሁ ስለዚህ እናንተም በተፈተናችሁ ጊዜ አትዘኑ ታገሡ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነውና አንድ ቀን ፈተናውን አሸንፋችሁ የትዕግሥትን ፍሬ ለማየት ትችላላችሁ ሁሉንም በእምነት መለመን ይገባችኋል ።

ጸሎታችሁን ልመናችሁን በእግዚአብሔር ላይ አድርጉ እግዚአብሔር በእምነት የሚለምኑትን ሁሉ ይሰማል ይቀበላልም መልስም በበረከት ይመልሳል ነገ እንዲህ ነበርን ለማለትም ያበቃል ይህ ግድ እንደሚሆንም የታመነ ነው» በማለት አጽናኝ ምክር ሰጥተዋቸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በመጠለያ ጣቢያ የሚ ገኙትን ወገኖቻችንን በጎበኙበት ወቅት የየጣቢያዎቹ ተወካዮች ባደረጉላቸው ገለጻ ሃያ ሺህ ሁለት መቶ ሁለት አባዎራዎች እንዳሉ በጠቅላላ ያለው ተፈናቃይ ብዛት ፶፱ ሺህ ፩፻፷ እንደሚገኙም አስ ረድተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በዚህ አጋጣሚ ጊዜ በእያንዳንዱ ጣቢያ ለሚገኙት ወገኖች የመስቀል በዓል መዋያ ይሆናቸው ዘንድ በየተወካዮቻቸው አማካይነት እንዲደርሳቸው በማ ስታወቅ ብር ፳ ሺህ (ሃያ ሺህ ብር) ለግሰው ወደ መንበራቸው ተመልሰዋል ።

በቅዱስነታቸው ሀሳብ መሠረት የየጣቢያው ተወካዮች ሰንጋዎችን ገዝተው ከአድባራት አለቆችም እን ዲባርኩላቸው አድርገው በዓለ መስ ቀሉን በጥቀና በደመቀ ሥነ ሥር ዓትና በታላቅ ደስታ አክብረው የዋሉ መሆናቸውን ከየሥፍራው የተላለፈልን ዘገባ ይገልጻል ።



# ቅዱስ ፓትርያርኩ በዝዋይ ለሠለጠኑ ወጣቶች የምስክር ወረቀት ሰጡ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በዝዋይ የካህናት ማሠ ልጠኛ ተቅዋም ወርኃ ክረምቱን በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ላሳ ለፉ ፷፰ ወጣቶች ነሐሴ ፴/፲፱፻፹፩ ዓ/ም በቦታው ተገኝተው የምስ ክር ወረቀት ሰጥተዋቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ከላይ በተጠቀሰው ዕለት ከንጋቱ ፩ ሰዓት ከ፳ ላይ ብፁ ዓን ሊቃነ ጳጳሳትን ቆሞሳትንና የመምሪያ ኃላፊዎችን ይዘው ከመ ንበረ በትረ ካናው ተነሥተው መቂ ለመድረስ ጥቂት ኪ/ሜትር ሲቀ ራቸው ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የደ ቡብ ሸዋ ሀ/ስብከት ሊ/ጳጳስና የ ውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ ከሀ ገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅና ሠራ ተኞች ጋር በክብር ተቀብለዋቸዋል።

ልክ ፬ ሰዓት ተኩል ገደማ መቂ ከተማ ሲደርሱ የደብረ አሚን ቅ/ ጊዮርጊስ አስተዳዳሪ ልብሰ ተክ ህኖ የለበሱ ካህናትና ዲያቆናት የቾቦ መብራት ያበሩ የክልሉ ወጣ ቶችና የሰንበት ት/ቤት መዘምራን ፣ የሰበካ ጉባኤ አባላትና የሕንጻው አሠሪ ኮሚቴ አባላት እንዲሁም በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የሰበካው ምእመናን እጅግ ከፍተኛ የሆነ ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስፓት ርያርክ ርእሰሊቃነ ጳጳሳት ዘኢት/ በመሠራት ላይ ያለውን የደብረ አሚን ቅ/ጊዮርጊስቤ/ክርስቲያንን እንዲጎበኙላቸው ምእመናን ስለ ጋበዙአቸው ወደ ቤ/ክርስቲያኑ አምርተው ሕንጻውን አንድ በአንድ እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል ። አያይ ዘውም ወደመቃረቢያው ሄ ደ ው የሕሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ ወደ ዐውደ ምሕረቱ በመውጣት ለም እመናኑ አባታዊ ቡራኬ ሰጥተዋል፤

ቅዱስነታቸው በዚሁ ወቅት ካ ሰሙት ንግግር«እግዚአብሔር ይባ ርካችሁ የጀመራችሁትንም ሕንጸ ቤ/ክርስቲያን አስፈጽሞ ለማየት ፣ ለመገልገልና በረከት ረድኤት ለመ ቀበል ያብቃችሁ ። እኛ ኢትዮጵያ ውያን የምንመሳሰልበት ባሕልና ሥርዓት አለን ። ይኸውም በእን ግዳ አቀባበላችን በመከባበራችን ነው ። በዚህም እንኮራለን ። አሁን እናንተ እንዲህ ስትታዩ ምንም የሌላችሁ ትመስላላችሁ ነገር ግን ይህ በፊታችን እንደመብራት ጎልቶ የሚታየው ሕንጸ ቤ/ክርስቲ ያን ሀብታችሁን ጥሪታችሁ ጉልበ ታችሁን ድካማችሁ ሁሉ እፍስሳ ችሁ ሠርታችሁ ለሌላው አርአያና ምሳሌ ስለሆናችሁ በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ዋጋና ክብር ያላችሁ ባለጸጎች ናችሁ ።

ደስ ይበላችሁ» በማለት ቡራኬ ሰጥተው ጉዞአቸውን ወደዝዋይ ፤ ቀጥለዋል ።

እንዲሁም የመቂ ደብረ ምሕረት ቅ/ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን ካህናት ና የሰበካው ምእመናን በነቂስ ወ ጥቶ የከተማውን መንገድ ግራና ቀኝ ተሰልፎ ለቅዱስነታቸው ክብ ር በዕልልታ በዝማሬና በሆታ አ ቀባበል ሲያደርግላቸው ቅዱስነታ ቸውም ከመኪና ወርደው እስከ ከተማው መጨረሻ ድረስ በእግር እየተጓዙ ግራና ቀኝ የተሠለፈውን ሕዝበ ክርስቲያን ሲባርኩ ሕዝቡ የተሰማው ደስታ ምን ያህል እንደ ሆነ ከፊቱ ለመረዳት ይቻል ነበር ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ዝዋይ ካህናት ማሠል ጠኛ ተቋም እንደደረሱ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የደቡብ ሸዋ ሀ/ስብ ከት ሊቀ ጳጳስና የውጭ ግንኙነት መምሪያ ኃላፊ እንዲሁም የገዳሙ አስተዳዳሪ ቆሞስ አባ ተጠምቀ ገ/ተክለ ሃይማኖት አበው መነኮ ሳትን ፤ ካህናትንና ዲያቆናትን ልብሰ ተክህኖ በማልበስ መስቀ ልና ጽንሐሕ የሻማ መብራት በማ ስያዝ ተመራቂዎቹ መዝሙር በማ ዘመር በከፍተኛ ክብር ተቀብለ ዋቸዋል ። ሦስት ተማሪዎችም ለቅዱስነታቸው ዕቅፍ አበባ አቅ ርበውላቸዋል ።

ወጣቶቹ «በሰላም ላመጣ አባቶ ቻችን እናቅርብ ምስጋና ለፈጣሪያ ችን » አብርሂ ፤ አብርሂ ሐመረ ብርሃን ፣ ብርሃንኪ በጽሐ ጳውሎስ አቡን ፣ «ተፈሣህነ ወተሐሠይነ በመዋዕ ሊነ በምጽአቱ ፣ በምጽአቱ ለፓትርያርክ አቡነ «እንኳን ደህና መጣችሁ ወደኔ ወደናታችሁ እጇን ዘርግቼ ስጠብቃችሁ»እያሉ ግራና ቀኝ ተሠልፈው በክብር ተቀብለዋ ቸዋል ። ቅዱስነታቸውም ብፁ ዓን ሊቃነ ጳጳሳትን በመምራት ወደ ሐመረ ብርሃን ቤ/ክርስቲያን ገብተው ጸሎት ካደረሱ በኋላ ወደ ዐውደ ምሕረቱ ወጥተው በተዘጋ ጀላቸው የክብር ሥፍራ ተገኝተ ዋል ።

ከዚያም ፣ ልብሰ ተክህኖ የለ በሱ የወርቅ መስቀል የያዙ ሦስት ዲያቆናት ከቅዱስነታቸው ፊት ቀር በው «እስመ መምህረ ሕግ ይሁብ በረከተ» የሚለውን የዳዊት መዝ ሙር በጣዕመ ዜማ አሰሙ ። ጸሎተ ወንጌሉ በቅደም ተከተል እንደደ ረሰ«ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ሉቃስ» በማለት በአንድ ገዳማዊ መነኮስ ተዜመ ።



www.ethiopianorthodox.org

ቀጥሎም ከሉቃስ ፲፤፩—፲፪ ያለውን በቅዱስ ፓትርያርኩ ንባብ ተሰማ

ከዚሁ በማያያዝ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የደቡብ ሸዋ ሊቀ ጳጳስና የውጭ ግንኙነት መምሪያ ኃላፊ «ጳውሎስ ፍቁሩ ለክርስቶስ ዘተጸውዓ ወተፈልጠ ምሀሮ ወንጌሉ ለክርስቶስ » በሚል ርእስ ሲናገሩ « ይህ ቃል ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ለነበሩ በጻፈው መልእክቱ በመግቢያነት የተጠቀመበት ቃል ነው ። እንደቃሉም ቅዱስነታቸው ወደዚህ ቦታ መጥተው በረከትዎን ፣ አባታዊ ቡራኬዎን ለመስጠት ስለሆነ ደስታችን እጥፍ ድርብ ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ ይህ ቦታ ከዛሬ ሃያ ዓመታት በላይ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የተተከለ ነው ። ቦታው ለቤ/ክርስቲያናችን ተከልሎ እንዲሰጣት ያስፈለገበት ምክንያትም በባሕሩ አካባቢና በባሕሩ ውስጥ በደሴቶቹ ለሚኖሩ ሕዝቦች በትምህርትም በእምነትም ይረዳል ይጠቅማል ብለው ያለሙት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፣ ቤተ ክርስቲያን ላይ ጠንካራ እምነትና ኩራት የነበራቸው የጤና ጥበቃ ሚኒስትር የነበሩት ክቡር አቶ አበበ ረታ የተባሉ ታላቅ ሰው ናቸው ።

ይሁን እንጂ ለ፲፯ ዓመታት እንደማዕበል ሆኖ አገሪቱን ጠራርጎ ያጠፋ አብዮት የተባለ የተስፋፋውንና ተደራጅቶ የተቋቋመውን ድርጅታችን ዓውድሞታል ።ካሉ በኋላ ወደ ገዳሙ ሐሳባቸውን በመመለስ ታድያ ይህ እንዳልነበር ሆኖ ወድሞ የነበረውን ቦታ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ለአሥራ ሦስት ዓመታት ያህል በብዙ ድካምና ጥረት ይህን የመሰለ ሥራ ተከናውኖ ዳግም ትንሣኤ አግኝቶ እነሆ ዛሬ እንደዚህ አምሮና ሠምሮ ይገኛል

እኔ ከመጣሁ ጊዜ ጀምሮም ቅዱስነትዎ እስከ ጎበኙው እስከ ዛሬ ይቱ ዕለት ይዘቱኝ ሳይለቅ ሳይቀንስ በዚህ ዓይነት መልክ ሲራመድ ይታያል ። ባሁኑ ጊዜ የደብረ ዓባይ ቅዳሴ መምህር ፣ የቅኔና የአቋቋም መምህራን አሉን ብዙ ደቀ መዛሙርት እያሠለጠንም እናስመርቃለን ። ስለዚህ አሁንም የቅዱስነትዎ መምጣት በዚህ ገዳምና በአካባቢው የሚገኘው ሁሉ በጣም አስደስቶታል ።» በማለት ንግግራቸውን እንዳበቁ ኮርሰኞቹ « ተዋሕዶ» የሚለውን መዝሙር ዘምረዋል ።

ከዚሁ ቀጥሎም የኮርሱ ርእሰ መምህር ንግግር አድርገዋል። ከንግግራቸውም «ቅዱስነትዎ የቱን ያህል ትምህርት ወዳድ መሆንዎንና ለቤተ ክርስቲያናችንም ትምህርት የቱን ያህል እንደሚጠቅማት የተረዱ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያናችን አባት መሆንዎን የምንረዳው በበዓለ ሢመትዎ ማግሥት ይህ የኮርሰኞቹ ት/ቤት ጐብኝተው የምስክር ወረቀቱንም ለመስጠት በመካከላችን በመገኘትዎ ለዘንተ ዓለም ሲያዘክረን ይኖራል ብለዋል ።

እያይዘውም ይህ ሁሉ እንዲሳካ ላደረጉ ለብፁዕ አቡነ ገብርኤል ምስጋና በማቅረብ በዚሁ ዕለት ቅዱስነትዎ የምስክር ወረቀት እንዲሰጡልንና ለዚህ ከፍተኛ ምርቃት የደረሱ ተማሪዎች ፳፭ ሲሆኑ አርባው ከዩኒቨርስቲ የመጡ እንዲያውም እንደዛሬው በዲግሪ ተመርቀው ከወላጆቻቸው (ከቤተሰዎቻቸው)እንኳ እንደሰት ሳይሉ ለሚበልጠው ጸጋ ለሃይማኖታቸው ሲሉ በበነጋታው በዚሁ የኮርስ ሥፍራ በመገኘታቸው እጅግ አስደንቆናል አስደስቶናልም ። ሲሉ ሰፋ ያለ መግለጫ ሰጥተዋል ።

እያይዘውም ከኮርሰኞቹ መካከል ንግግር እንዳደረጉ የሰንበት ት/ቤቶች መምሪያኃላፊአጭር መግለጫ ሰጥተዋል።ከመግለጫውም ውስጥ «እኔ በዚህ አጋጣሚ ብዙ የምናገረው ጉዳይ የለኝም ነገር ግን ወጣቶች ከተመረጡበት ጊዜ ጀምሮ ከቅዱስነትዎ ፊት ቀርበው ሐሳባቸውን ለማቅረብ ሲመኙ እንዳጋጣሚ ዛሬ ከዚሁ ተገኝተው በስፋት ለመወያየት በመብቃታቸው ደስ የሚል ስለሆነ ለማመስገን ነው በተጨማሪም ብፁዕ አቡነ ገብርኤልን እናመሰግናለን ብለዋል ። ከዚህም በኋላ ከልዩ ልዩ ሊቃውንት ልዩ ልዩ መወድስ ቅኔያት ተበርክተዋል ።

ከዚህ በመቀጠል ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቃለበረከታቸውን ሲያስተላልፉ ፣ «ይህ ዕለት ከፍ ያለ ትርጓሜ ያለው ነው ። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ይህ ቦታ የተገኘው ፡ የተቋቋመው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ነው ። ቅዱስነታቸው በዚህ ቦታ ይህ ት/ቤቱ በሚያቋቁሙበት ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙ ፣ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ማሠልጠኛ እንዲሆን በማሰብ ነው ። ለዚህ ቦታ ማቋቋሚያም ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት በመነጋገር ርዳታ በመጠየቅ ነው ።

ሕንጻው ተሠርቶ እንዳበቃ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዋና ጸሐፊ መጥተው መርቀው ሲከፍቱት እኔም በአስተርጓሚነት በዚህ ሥፍራ ተገኝቼ ነበር ። ሃያ አራት ዓመታት ይሆነዋል ። በሃያ አራት ዓመታት ብዙ ነገሮች አልፈዋል ። የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ለማዳበር ቤተ ክርስቲያናችን በአዲሱ ዓለም ወይም ዘመን የሚያጋጥማትን ሁሉ በዚህ ተምረው የሚወጡት ምሁራን ለመቋቋም ይችሉ ዘንድ ታስቦ የተሠራ ነው ።

አባቶቻችን የምናደንቃቸው በመልካም ሥራቸው በመልካም ሥነ ምግባራቸው ነው። ይህ ሥፍራ ይህ ሥራ አባቶቻችን ከምናደንቅላቸው ቀዋሚ ሥራቸው አንዱ ነው ። ባለፉት ዓመታት አስከፊ ሁኔታዎች እንደነበሩ ግልጽ ሲሆን ቤ/ክርስቲያናችን ሁሉንም ተቋቁማ እዚህ ደርሳለች ።

ወደ ኋላ መለስ ብለን ይህ ቦታ ምን እንደነበረ እናስታውሳለን ። በጣም በረሀ ስለነበረ እንኳንስ እንዲህ አምሮ ሰው ሊኖርበት - ሊሰበሰብበትና ዕውቀት ሊገበይበት ይቅርና እጅግ የሚያስፈራ ስለነበር ባሁኑ ጊዜ ያን አይተን ይህንንም ደግሞ ስናይ በጣም ያስገርመናል ። አባቶቻችን «ሰብእ ይቄድሶ ለመካን ወመካን ይቄድሶ ለሰብእ»እንዳሉት ሁሉ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከላይ የተጠቀሱት የተቀደሱ ተግባራት ተከናውነው ፣ ከእርሳቸው በኋላ ደግሞ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ወደዚሁ ቦታ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ሌት ተቀን ሳያርፉ እዚህ በማድረሳቸው የቤተ ክርስቲያን አባትነታቸው በተግባር አስመስክረው አልፈዋል።

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ከመካከላችን በአካለ ሥጋ ስለተለዩን በጣም እናዝናለን ። ነገር ግን ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ አልሞቱም ሕያው ናቸው ። ዛሬ በሙቶ የሚቈጠሩ ጎርጎርዮሶች የቤተ ክርስቲያን ልጆች አፍርተውልን ስለሄዱ ፍሬአቸው በዓይናችን እያየነው ነው ። አቡነ ጎርጎርዮስ አልሞቱም ሙተዋልም አይባሉም ያልነውም ስለዚህ ነው ።

አንድ ሰው ሙተዋል የሚባለው ምንም ሥራ ሳይሠራ ከዚህ ዓለም የተለየ እንደሆነ በዐጸደ ሥጋ ሆነ በዓጸደ ነፍስም የሞተ ነው ሊባል ይገባል ። ብፁዕነታቸው ግን ይህ ገዳም በኢትዮጵያችን ካሉት ታላላቅ ገዳማት በበለጠ ደረጃ አስቀምጠውት (አደራጅተውት) ስለሄዱ በዓጸደ ሥጋ ቢለዩንም በሥራቸው ከመካከላችን እንዳሉ እንቈጥራቸዋለን ።

አብርሃምን ምሰል (ምሰሉ) እየተባለ - ለክርስቲያኖች ሲነገር ይሰማል አብርሃምን መምሰል ማለት በቁመቱ ፤ በቅላቱ ፣ በሀብቱ ሳይሆን በሃይማኖቱ በእምነቱ በትሩፋቱ ማለት ነው ። አብርሃም አርከ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ፣ ወዳጅ ሲባል ይሰማል እግዚአብሔር ለምንድር ነው አብርሃምን የወደደው ? ትእዛዙን ስለሚፈጽምለትና ስለሚጠብቅለት ብቻ ነው ።

የአብርሃምን ሥራ የሚሠራ ሁሉ የእግዚአብሔር ወዳጅ ነው ። ስለዚህ አባቶቻችን እንደአብርሃም ፣ የእግዚአብሔር ወዳጆች እንዲባሉ ስለፈለጉ የአብርሃምን ሥራ እየሠሩ አልፈዋል ። ስለሆነም አባቶቻችን ሠርተው አደራጅተው ከተውልን ድርጅት አንዳችም ሳናጠፋ ሳናጎድልና ሳናፈርስ ጠብቀን ለትውልድ ማስተላለፍ አለብን » ከተቻለንም ማስፋፋትና በይበልጥ ማደራጀት ይገባናል ። በዚህ አጋጣሚ እኔም ከገዳሙ ኃላፊዎች ጋር በመሆን የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማሟላት ግዴታ አለብኝ ተልእኮየን ለመፈጸምም ብዙ ሥራ እንደሚጠብቀኝ መዘንጋት አይገባኝም

ከዚህም ጋር ላሳስብ የምፈልገው ቤተ ክርስቲያን የሰላም ፣ የፍቅርና የአንድነት ምንጭ እንደመሆንዋ መጠን እኛ የመንፈሳውያንና የሰላማውያን ሰዎች ተግባር ሰላም መሆኑን አምነን በሰላም ጎዳና መራመድ አለብን በያለንበት ሁሉ ስለሰላም እንድናስብ ስለሰላም ጥረት እንድናደርግ ይገባናል ። የዚህ ዓለም ሥራ የሰላም ተቃራኒ ስለሆነ እኛ የሰላም ሰዎች ስለሰላም ብለን ሲሰድቡን ታግሰን በፍቅር ማሸነፍ አለብን ። ማንኛውም ክፉ ነገር ሁሉ በትዕግሥት ካሳለፉት የማሸነፍ ውጤቱ መልካም ፍሬ መሆኑን እናምናለን ።

ቀደም ሲሉ ስለእናንተ መልካም ተግባር በሰፊው ተነግሮአል ። እኔ ደግሞ የተነገረላችሁን ብቻ ሰምቼ ተቆጥቤ አልሄድም ፤ የምላችሁ ነገር አለኝ ። ባሁኑ ጊዜ ቤ/ክርስቲያናችንን ያለስሟ ስም የሚሰጡ ስም አጥፊዎች አሉ ። ስለዚህ እኛ ዓይን በዓይን ጥርስ በጥርስ እንደተባለው ሳይሆን በትዕግሥት ፣ በፍቅር ሆነን ድል ልናደርጋቸው ይገባናልና ተልእኮአችሁን በትዕግሥት አድርጉት ።

እናንተ የሳይንስ ተማሪዎችና ፤ ተመራማሪዎች ስትሆኑ በእምነታችሁ ጸንታችሁ ሃይማኖታችሁን ጠብቃችሁ ለሃይማኖታችሁ ስትሉ በዚህ ቦታ ተገኝታችሁ የኮርሱ ተካፋዮች ሁናችሁ ይህን የመሰለ ጥሩ ውጤት በማሳየታችሁ እግዚአብሔር ይባርካችሁ እንግዲህ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ እንደተባለው አኗኗራችን ያማረና የተወደደ ከሆነ ሌሎችን በምሳሌነታችን መሳብ አለብን ።

እነሆ ወደፊታችን አዲስ ዓመት ለማክበር በመዘጋጀት ላይ ነን ይህ አዲስ ዓመት የምንለው ወደፊት ስለምንሠራው ወይም ስለምናየው ብቻ ሳይሆን ባለፈው ዓመት ያልሠራነው ካለ በአዲሱ ዓመት እንድንሠራው ይገባል ። ይህም ማለት አዲስ ተንኮል ፣ አዲስ መለያየት አዲስ ክፋት ፣ አዲስ ምቀኝነት አዲስ ጥላቻ ሳይሆን ፣ አዲስ ሐሳብ አዲስ ፍቅር ፣ አዲስ ጥሩ ሥራ ፣ አዲስ ግንባታ አዲስ ኑሮ አዲስ ትዕግሥት አዲስ ትምህርት ነው ።

በልዩ ልዩ ሥራ በዚህ ቦታ የምትኖሩ ሁሉ በሰላም ፣ በፍቅርና በስምምነት በኅብረት መሥራት ፣ አለባችሁ ። ስለዚህ በኑሮአችሁ በተግባራችሁ ሁሉ የእግዚአብሔር በረከትና ረድኤት አይለያችሁ በማለት የፕሮግራሙን ሥነ ሥርዓት በቡራኬና በጸሎት ፈጽመው እንዳበቁ አትክልቱን ፣ የትምህርትና የመኝታ ክፍሎቹን እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል ።

በመጨረሻም የዕረፍትና የምሳ ፕሮግራም ከሰባት ተኩል እስከ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ተከናውኖ ጉዞ ወደ ዝዋይ ኪዳነ ምሕረት ቤክርስቲያን አምርተው በዚያ ተሠልፈው የቅዱስነታቸውን መምጣት ሲጠባበቁ ለነበሩ ካህናትና ምእመናን ቡራኬ ሰጥተዋል ። የቤ/ክርስቲያኑ ሰንበት ት/ቤትም ጣዕመ ዝማሬ እያሰሙ በክብር ተቀብለዋቸዋል ። ቅዱስነታቸውም ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ወደቤተ መቅደስ ገብተው የሕሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ በስተምሥራቅ ከቤቱ ልሔሙ አጠገብ የሚገኘው የብፁዕ አቡነ ሳሙኤል መቃብር ቤትን ተመልክተዋል ። ባርከው ጸሎት አድርሰው እንዳበቁም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል ።





www.ethiopianorthodox.org

## በቅዱስ ሚካኤልና በቅ/ገብርኤል አማላጅነት

ወ/ሮ በቀለች ተስፋዬ አድራሻ አ-አ- ኮተቤ ልዩ ከፍተኛ ፩ ቀበሌ 03 የቤት ቊጥር 395 ነዋሪ የሆኑ ባደረባቸው የሆድ ውስጥ በሽታ ለ፯ ዓመታት ያህል ሲሰቃዩ ቆይተው በየሐኪም ቤቱም እየተዘዋወሩ የታዘዘላቸውን መድኃኒት ቢወስዱም ፈጽሞ ሊድኑ ስላልቻሉ ተስፋ ቆርጠው እንደነበር ከዘገቡት መዝገብ ለመረዳት ተችሎአል

ነገር ግን በዶ/ር ሐኪም መለሰ ማሞ እጅ ብዙ ሕሙማን እንደ ተፈወሱ ሰምተው ፈልገው አግኝተው ከተመረመሩ በኋላ በሰጡአቸውና ባዘዙላቸው መድኃኒት መሠረት ተከታትለው መድኃኒቱን ስለ ወሰዱ፡ ግንቦት ፣ ፲፩ ቀን ፣ ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ከሚያሰቃያቸውና ከሚያስጨንቃቸው በሽታ ተገላግለው ወደ ቤታቸው በሰላም ተመልሰዋል ።

በአ-አበባ በከፍተኛ 16 ቀበሌ ፣ 04 የቤት ቁጥር 344 ነዋሪ የሆነ ተማሪ ትልቁ ዓለም ተስፋዬም ባደረበት የአእምሮ መታወክ ከብዙ ልዩ ልዩ ሐኪም ቤት ሄዶ ምንም ለመዳን እንዳልቻለና በተለይም ፣ ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ወስደውት ምንም ተስፋ ካለማግኘቱ የተነሣ ወላጆቹ በከፍተኛ ጭንቀት ወድቀው እንደነበሩ ገልጸ ወደ ሐኪም ዶ/ር መለሰ ማሞ ይዘውት መጥተው ተመርምሮ የመንፈስ ጭንቀት ስለሆነ አሁን ይድናል ብለው ተስፋ ሰጥተውት ሕክምና እንደጀመረ በጥቂት ቀናት ውስጥ ፍጹም ጤነኛ ሆኖ ወደ ት/ቤቱ ለመመለስ መብቃቱን ከሰጠው ዘገባ ለመረዳት ችለናል ።

አ-አበባ ከፍተኛ ፫ ቀበሌ ፳፫ የቤት ቊጥር 1852 ነዋሪ የሆኑ ወ/ሮ ፀሐይ ታየ በደረሰባቸው የሆድ ውስጥ ከባድ በሽታ ለአያሌ ዘመናት ሲሰቃዩ ከቆዩ በኋላ በየሐኪም ቤቱ እየተዘዋወሩ ባደረጉት የመዳን ሙከራም ፈጽሞ እንዳልተሳካላቸው ገልጸው ሰውበሰው ነውና እንድ ዘመድ ይዞኝ ወደ ዶክተር መለሰ ማሞ ስለመጣ ተመርምሬ መድኃኒት አዘውልኝ ኃትእዛዙ መሠረት ተከታትዬ በመውሰዴ ፍጹም ጤናና ሰላም አግኝቼ ወደ ቤቴ ስመለስ ቅዱስ ሚካኤልና ገብር ኤል ከሐኪም ዶ/ር መለሰ ማሞ እንዲሆን እየተመኘሁ ድኜ ሙሉ ጤንነት አግኝቼ ተመልሻለሁ ብለዋል ።

አ/ አበባ ከፍተኛ ፲፯ ቀበሌ ፳፬ የቤት ቁጥር ፬፻፺፭ ነዋሪ የሆኑ ወ/ሮ ዓለም ፀሐይ ገብሬ በሰው እጅ በሽታ አንድ ዓመት ሙሉ ሲሰቃዩ ኑረው አሁን በዶክተር መለሰ ማሞ ታክመው ድነዋል ።

ወ/ሮ ፀሐይ ስለበሽታቸው ሲያብራሩ በዚህ በ፹፬ ዓ/ም በጥቁር አንበሳና በየካቲት ሆስፒታሎች እየተመረመርሁ ምንም መፍትሔ ስላላገኘሁ በአንድ ሰው አማካይነት ወደ ዶክተር መለሰ ማሞ መጥቼ ከተመረመርሁ በኋላ የታዘዘልኝን መድኃኒት ተከታትዬ በመውሰድ በሆዴ ውስጥ የነበረው በሽታ ወጥቶልኝ ባሁኑ ጊዜ ሙሉ ጤናና ሰላም አግኝቼ ወደቤቴ ተመልሻለሁ ሲሉ በፊርማቸውና በቃላቸው አረጋግጠዋል ።

## ቅዱስነታቸው በተገኙበት የመድኃኔ ዓለምና የመጥምቁ ዮሐንስ በዓል ተከበረ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ቦሌ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለምና መጥምቁ ዮሐንስ ቤ/ክርስቲያን ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት ሲደርሱ የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ሕይወት ወልደ ሰንበት አድሐና ከሰበካ ጉባኤ አባላት ፣ ልብሰ ተክህና ፣ መስቀል ዘወርቅ ማዕጠንታተ ዘወርቅ ከያዙ ቀሳውስትና ዲያቆናት እንዲሁም የደብሩ ሰንበት ት/ቤት መዘምራንን አስልፈው «ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር» የሚለውን የዳዊት መዝሙራዊ ቃል በጣዕመ ዝማሬ እያዘመሩ የደመቀና የላቀ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩም በግራና በቀኝ የተሠለፉትን ምእመናን የተቀደሰ ቡራኬአቸውን እየሰጡ ወደ ቤተ መቅደስ ገብተው ጸሎት አድርሰው በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ ሆነው የሊቃውንቱን ወረብ አዳምጠዋል ።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የተቀደሰ ፈቃድ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የሰሜን ጐንደር ሊ/ጳጳስ ሠራይነት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተራዲኢነት ሥርዓተ ቅዳሴው ከአንድ ሠዓት እስከ ሦስት ሰዓት ተከናውኖ እንዳበቃ ታቦተ ሕጉ ወደ ዐውደ ምሕረቱ ወጥቶአል ።

ቅዱስነታቸው ታቦተ ሕጉን በመምራት ሥርዓተ ዑደቱ እንደ ተፈጸመ በተዘጋጀለት ሥፍራ ቆሞአል ። ቅዱስ ፓትርያርኩም በተዘጋጀላቸው ሥፍራ እንደተገኙ ፣ መዘምራኑ ለበዓሉ የተዘጋጀውን ግሥ ቃኝተው ለ፰ ደቂቃ ያሬዳዊ ጣዕመ ዝማሬ አሰምተዋል ። ከዚህም በመቀጠል የደብሩ ሰንበት ት/ቤት መዘምራን ተመሳሳይ መዝሙር ዘምረዋል ።

የቤ/ክርስቲያኑ ሰ/ጉባኤ ም/ሊቀ መንበር ንግግር አድርገዋል ።

በንግግራቸውም ውስጥ በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ቤ/ክርስቲያኑ እንደተፈቀደ በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም መቃኞው ተሠርቶ የመድኃኔ ዓለምና የመጥምቁ ዮሐንስ ታቦት እንደገባ ባሁኑ ጊዜም የአቡነ አረጋዊ ጽላት እንዳለ ገልጸዋል ። ስለወደፊቱም የኢትዮጵያ ቤ/ክርስቲያንን ይዞት ሳይለቅ እጅግ ዘመናዊና ከፍተኛ የሆነና ጎላ ብሎ የሚታይ በብዙ አርስቲስቶች ተጠንቶ ለቦታው ተስማሚ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ ቤተ ክርስቲያን በቅርብ ጊዜ እንደሚጀመር አብሥረዋል ።

ከዚህም ቀጥሎ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የምዕራብ ጎጃም ሊ/ጳጳስ በቅዱስ ፓትርያርኩ ፈቃድ ትምህርት ሰጥተዋል ። የትምህርታቸውም ርእስ «እምኄሶ ለሄሮድስ ይብላዕ መሐላሁ » በሚል ተነሥተው ዮሐንስ በመሠረቱ በቅ/ገብርኤል አብሣሪነት ከኤልሳቤጥና ከዘካርያስ ከተወለደ በኋላ ልዩ ጸጋና ሀብት ነበረው «ከመ ይሚጥ ልበ አበው ኀበ ውሉድ ወሕሊና ከሐድያን ኀበ አእምሮ ጻድቃን ። »

እንዲህ ያለ ቅዱስ አባት በምስክርነቱ ማንንም ሳያበላልጥ እግዚአብሔር የገለጠለትን በእውነት ያስተምር ነበረ ይሁን እንጂ ምቀኞች አይሁድ የምትፈልገው ሕፃን የዘካርያስ ልጅ ነው እያሉ ለሄሮድስ ስለነገሩት ሊገድለው ሲል አባቱ ሰምቶ ከከንፈረ ምሥዋዕ ወስዶ ካጠመቀው በኋላ በምድረ በዳ ወስዶ አስቀምጦታል ዮሐንስ እንደ አሞራ እየበረረ በፍጥነት ያስተምር ነበር ።

ዮሐንስ እውነትን ጠብቁ ኃጢአትንም አትሥሩ እያለ ይገሥጽ ነበር ። ዛሬም በሃይማኖታችን ስንላላ የሚገሥጹንን ሰዎች መጥላት የለብንም መስማትና መመለስ አለብን በማለት መልእክታቸውን አጠቃልለዋል ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስነታቸው የተባረካችሁና የተቀደሳችሁ ከሩቅም ከቅርብም የመጣችሁ አባቶች እናቶች ወንድሞች እኅቶች ልዑል እግዚአብሔር በሰላም ወደ የቤታችሁ ይመልሳችሁ ።

አዲሱን ዓመት በምን እንደምናከብረው ማስታወስ ይገባናል ዮሐንስ ያስተማረው ት/ስለንስሐ ነው ዮሐንስ በድፍረትም የሚመራ ነው ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ስለማያስችል በንስሐ መታጠብ አስፈላጊ ነው መጽሐፉ ካሁን በፊት የሠራችሁትን ኃጢአት በንስሐ ታጠቡ ከእንግዲህ ወዲያም ኃጢአት አትሥሩ ነው የሚለው ። በዚህም መሠረት በዚያን ዘመን የነበሩ ሰዎች በምቀኝነት ነቢይም ሐዋርያም ሰማዕትም ስለነበረ እርሱን ለማጥፋት ነው ሰዎች ሲከታተሉት የነበሩት ስለዚህም የመጣበትን መከራ ችግርና ሥቃይ ሁሉ በምስጋና ነው የተቀበለው ።

ሄሮድስም ሆነ ከርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች በዘካርያስና በአባቱ የፈጸሙት በደል በዚያን ጊዜ ብቻ ተፈጽሞ ያከተመለት ሳይሆን አሁንም እንደዚሁ ዓይነት ሥራ ካልሠሩ ሰላም የማያገኙ መስሎ የሚታያቸው ሰዎች ብዙዎች ናቸው ።ስለዚህ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ወደንስሐ ለመመለስ መትጋት ያስፈልጋል መታገስም ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው የለም ካልተበቀልን አይሆንም አንመለስም የሚሉ ካሉ ደግሞ በሃይማኖታችን እንዲህ ካላደረጋችሁ አትጸድቁም የሚል ትምህርት ስለሌለን እንዲታገሡ መምከር ይገባል ።

አንዳንድ ሰዎች ሥራ አያስፈልግም ጌታ ይሰጠናል እያሉ ቤት ዘግተው የሚጮኹና ስንፍናን የሚያስተምሩ አሉ ከእንደዚህ ያሉ ሰዎች መራቅ ያስፈልጋል ዮሐንስ ከተናገረው ቃል ተራራው ዝቅ ይበል ጎድጓዳው ይሙላ ይላል ይህ ተራራ ይህ ጎድጓዳ ምንድር ነው?የሰው ልብ ነው እንደለስላሳ መሬት መልካም ዘር እንደሚቀበል የምእመናን ልብ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበል በትምህርተ ወንጌል የተመቻቸ የለሰለሰ መሆን ይገባዋል ።

ምእመናን ዮሐንስ ያስተማረውን ትምህርት መሠረት አድርገን ልባችን አለስልሰን ከተንኰል ከምቀኝነት ከልዩ ልዩ ኃጢአት አጽድተን ሃይማኖታችንን መጠበቅ ግዴታችንና ዓላማችን ነው በክርስቶስ ዓለም የሚለያይ አጥር የሚለያይ ግድግዳ የለም ከእግዚአብሔር የሚለይ ኃጢአት ብቻ ነው ።

ክርስቶስን የተቀበለች ነፍስ ኃጢአት አትሠራም ሁልጊዜ ከኃጢአት ትሸሻለች ሁል ጊዜ ኑሮዋ ሁሉ ከእርሱ ብቻ ታደርጋለች ስለዚህ የሃይማኖት ፍሬ ነገር ንስሐ ነው ። ይህ አዲስ ዓመት መልካም ሥራ እንሥራበት ከንስሐ ወደኃጢአት ተመልሰን የምንገባው በቁጭት ምክንያት ነው ይህም ደግሞ አጥፊ እንጂ ጠቃሚ አይደለም ስለዚህ የዮሐንስን ትምህርት ምን ጊዜም መዘንጋት የለብንም እንግዲህ ይህንኑ እያስታወስን ወደ የቤታችን እንሂድ እግዚአብሔር ይባርካችሁ በሰላምም ወደየቤታችሁ ይመልሳችሁ ። አዲሱን ዓመትም የሰላምየደስታ በዓልያድርግላችሁ» በማለት አባታዊ ቡራኬ ሰጥተው እንዳበቁ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ። ቅዱስነታቸውም ወደ መንበረ ክናቸው ተመልሰዋል ።





www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስነታቸው አዋሳን ጐበኙ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም አዋሳን ጎብኝተዋል ። ቅዱስ ፓትርያርኩ ከቀኑ ፬ ሰዓት ከአዲስ አበባ ተነሥተው አዋሳ ሊደርሱ ሃያ አምስት ኪ-ሜ ሲቀራ ቸው ብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ የሲዳሞ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ መም ሀር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው የሀ ገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ከሀ ገረ ስብከቱ ሠራተኞች ከምእመ ናን ተወካዮች ከፍተኛ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ከዚህም ጉዞው ቀጥሎ አዋሳ ከተማ ሲደርሱ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናትና ዲያቆ ናት ጥንግ ድርብ የለበሱ ሊቃው ንት መዘምራን የአዋሳ ደብረ ምሕ ረትና መንበረ ሥላሴ አድባራት ሰንበት ት/ቤት ወጣት መዘምራን ባርከኒ አባ እያሉ በመዘመር ታላላቅ የከተማው አዛውንት በ ብዙ ሺህ የሚቈጠር የከተማው ነዋሪ ሕዝብ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ስሜት ተቀብለዋቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ በማምራት ጸሎት ካደረሱ በኋላ በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ እን ደተገኙ ብፁዕ አቡነ በርተሎሜ ዎስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ዛሬ የቅዱስነትዎ መልካም ፈቃድ ሆኖ የሲዳሞ ሀገረ ስብከት ርእሰ ከተማ የሆነችው አዋሳን ለመጎ ብኘት በመካከላችን በመገኘትዎ የተሰማን ደስታ እጥፍ ድርብ ነው።

ይህ ቦታ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በየጊዜው ይጎበኙት ነ በር ። ከእርሳቸው በኋላ የተሾሙት ፓትርያርኮችም ጎብኝተውታል ቅ ስነትዎ ግን ከበዓለ ሢመትዎ ማግ ሥት ስለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ መጥ ተው በመጎብኘትዎ ከሌሎቹ ሁሉ ልዩ ያደርገዋል ። ለወደፊቱም በየ ጊዜው እየመጡ ርምጃችንንምሁሉ እያዩ እንደሚጎበኙልንና የተ ቀደሰ ቡራኬዎም እንደማይለየን ሙሉ ተስፋ አለን ።



ቅዱስነታቸው በደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ቀድሰው ወደ ዐውደ ምህረቱ እንደወጡ

ይህ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በሦስት ፓትርያርኮች መሠረት ተጥሎአል ቅዱስነትዎ ግን እዚህ ደርሶ አግኝተውታል እንግዲህ በቅዱስ ነትዎ ዘመነ ሢመት ተፈጽሞ በቅ ዱስነትዎ ተባርኮ መንፈሳዊ አገል ግሎቱ እንደሚቀጥል ሳንጠራጠር ሙሉ ተስፋ እናደርጋለን » ። በማ ለት ገለጻቸውን አጠቃለዋል ። የብፁዕነታቸው ንግግር እንዳበቃም ከሁለት ሊቃውንት ቅኔ ተበርክቶ አል ከዚያም ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ሦስት ዲያቆናት ከቅዱስነታቸው ቀርበው እስመ መምህረ ሕግ ይሁ ብ በረከተ» የሚለው በጣዕመ ዜማ አስምተዋል ። ከዚያም ሦስት መነ ኮሳት ወንጌል ቅዱስ የሚለውን በዜማ ካሉ በኋላ ከዮሐንስ ወንጌል ፲፥ ከ፲፩—፲፭ በቅዱስነታቸው ተነ ቦአል ።

ከዚህ ቀጥሎ ቅዱስ ፓትርያርኩ «የተባረካችሁና የተወደዳችሁ የክ ርስቶስ ቤተሰዎች ልዑል እግዚ አብሔር በሰላምና በጤና ጠብቆ ለማገናኘትና ሀልዎቱንም ለማዘ ከር ፈቃዱ ሆኖ በዛሬዋ ዕለት እንዲህ ተሰብስበን በዓይነ ሥጋ ለመተያየት ስላበቃን ክብር ምስ ጋና ይግባው» ብለዋል ።

እያይዘውም ከሥራ እንደዋላች ሁ ደከመን ሰለቸን ሳትሉ እኛን ለመቀበል በዚህ ዐውደ ምሕረት በመገኘታችሁ እግዚአብሔር ይባ ርካችሁ ይቀድሳችሁ ሰላሙን ረድ ኤቱን ፍቅሩን አንድነቱን ይስጣ ችሁ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዓለም ሕዝ ብ ልዩ ባሕል ፣ ሥርዓትና እምነት አለው ፤ በዕልልታው በሆታው በመዝሙሩ ፣ በከበሮው በጸናጽሉ ፈጣሪውን የሚያመሰግን ከኢትዮ ጵያ ሌላ በየትም አገር የለም እኔ እግር ጥሎኝ በብዙ አገር ተዘዋ ውሬ አይቻለሁ ። እንዳየሁትም



መዝሙራቸው ከአንገት በላይ እን ጂ ከልብ አይደለም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደምን አደርክ እንደምን ዋልሽ ሲሉት እግዚአብሔር ይመ ስገን ነው መልሱ ይህ ሁሉ በሁሉ አገር የለም ። ሀገራችን ኢትዮጵያ ማንም ሰብኮ አይደለም ያሳመናት ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚ አብሔር ትዘረጋለች ብሎ ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር የተቃኘው ማንም ሳያስተምራት የተማረች አ ገር መሆኗን ስለተረዳ ነው ። ሲሉ ቅዱስነታቸው አባታዊ ቃለ በረከ ታቸውን አሰምተዋል ።

በሀገራችን እምነት እንደሌለ ሕ ዝቡ ሌላ እምልኮት እንደሚከተል አድርገው የሚመለከቱና በሰበብ በአስባቡ ወደ ሀገራችን ገብተው የቅብጥርጥር ሃይማኖት ለማስፋፋ ት ይፈልጋሉ ። የኢትዮጵያ ኦርቶ ዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው መጽሐፍ ቅዱስ ነው የምታመልከው በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረው አምላክ ነው ከዚህ ውጭ እምነት የለንም ።

ልጆቼና ወንድሞቼ በየሰው ቤት ዘው ብላችሁ አትግቡ ብቅ ጥልቅ አትበሉ የሰው ልብስ አያሞቅ የሰው ወርቅ አያደምቅ ተብሎ እን ደተነገረው የተውሶ ሃይማኖት ያ ውም መሠረት የሌለው አያስፈል ጋችሁም ። ቤታችሁ ሙሉ ነው ። እኛ በሰው የምንመራ እንስሳት አይደለንም ። ዐዋቂዎች የዐዋቂ ዎች ልጆች ነን የእሳት ልጅ አመድ መሆን የለብንም ።

ወጣቶች የእግዚአብሔር ፍቅር የወንጌል ትምህርት ጥማት እንዳ ላችሁ ከፊታችሁ ለማንበብ ይቻ ላል ። ነገር ግን ዛሬ ቤተ ክርስቲያ ናችን ጥዋት ማታ ከቤተ ክርስ ቲያን ሳይለዩ የወንጌል ትምህርት በትጋት በማስተማር ላይ ስለሆኑ የምትፈልጉትን ሁሉ ይሟላላችኋል በማለት አባታዊ ትምህርታቸውን አጠቃልለዋል ።

ከዚህ በኋላም ወደ ካህናት ማሠ ልጠኛው ት/ቤት በማምራት የሙ ዝ የሸንኮራ ፤ የፓፓየ ፣ የባሕር ዛፍ አትክልቶችንና ቅልብ ሰንጋ ዎችን እየተዘዋወሩ ጐብኝተዋል ። በዚያ የነበሩ ወጣት መዘምራንም «ባርከኒ አባ እንግዕ በረከተከ በእ ንተ ሰላማ ለቅድስት ቤተ ክር ስቲያን»እያሉበሚያስደስትና በሚ ማርክ ጣዕመ ዜማ ተቀብለዋቸዋል

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ለመስከረም ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም አጥቢያ ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ላይ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ደብረ ምሕረት ቅ/ገብር ኤል ቤ/ክርስቲያን ሲደርሱ የደ ብሩ አስተዳዳሪ መስቀል ከለበሱ ካህናትና ዲያቆናት ከሰበካ ጉባኤ አባላትና የሰንበት ት/ቤት መዘ ምራን ጋር በክብር ተቀብለዋቸ ዋል ።

ቅዱስነታቸውም ወደ ቤተ መቅ ደስ ገብተው ጸሎት ካደረሱ በኋላ በተዘጋጀላቸው ሥፍራ ተገኝተው ለካህናቱና ለሕዝቡ የተቀደሰ ቡራ ኬአቸውን ሰጥተዋቸዋል ። ልክ ፲፪ ሰዓት ሲሆን በቅዱስ ፓትርያ ርኩ ሠራዒነት በሊቃነ ጳጳሳት ተራዳኢነት ሥርዓተ ቅዳሴው ተ ጀምሮ በሦስት ሰዓት ፍጻሜ ሆ ኖአል ።

ሦስት ሰዓት ተኩል ሲሆን ቅዱ ስ ፓትርያርኩ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ወደ ዐውደ ምሕረቱ ወጥተው በተዘጋጀላቸው ሥፍራ ሆነው ሕዝቡን ባርከዋል ። ቀጥ ሎም ሊቃውንት መዘምራንና የሰ ንበት ት/ቤት መዘምራን ለሃያ ደ ቂቃ ያህል አሸብሽበዋል ። ከሦ ስት ሊቃውንትም ቅኔያት ተበር ክተዋል ። ከመሪጌታ እስጢፋኖስ ተመስገን ከቀረቡ መወድሶች አን ዱ ፤


፩ኛ«ተክለ አቤል አቤል ዘቴዎፍሎ
ስ ሢመተ ጳውሎስ ዘእምነ ኪሩ
ቤል ዓዕማድ ፤
ዘወለደት ሔዋን ቤተ ክርስቲ
ያን ወላድ
ተናዘዘት እምነ ኀዘና ምንታዌ
ክቡድ

ወነገደ ቃየል ያርዕድ ኀዘነ ወላዲ
አዳም ማዕበለ ካህናት መዋግድ
ለሔዋንሂ እምኵልነ መቅደስ
ወልደ አብ ዋሕድ
ከመ በዝኀ መከራሃ ፍሥሐ ዚአሃ
ይፈደፍድ
አምጣነ ጽሑፍ ዘልብ እንተ
ፍጡራን ዘመድ
ምዕረ የአምን ወምዕረ ይክሕድ
ቃለ እግዚኡ እግዚእ ጸዋሬ
አእጋር ወእድ ።» የሚል ሲሆን



ቅዱስ ፓትርያርኩ በብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ የአዋሳን ልማት ሲጎበኙ

www.ethiopianorthodox.org



በቅዱስ ፓትርያርኩ መልካም ፈቃድ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ትምህርት ሲሰጡ

እንዲሁም ከአንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ከዚህ የሚከተለውን መወድስ ተሰጥቷል ።

— ሕንጻ ደብረ ምሕረት ዘቆመት በቃለ ፈጣሪ
ግብረ ኩለን፡ታሃ ጽኑዕ ወመሠረታ ረቂቅ
እርእስተ ዜና ያብሥርከ በርተሎሜዎስ ልሒቅ
ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን ወበገላትያ አተሐንጾ ንጽቅ
ወሕዝበ አዋሳ ዘይትፌሥሑ በቅድመ ዘናትናኤል አብ
ወቅድመ ያዕፉብ ሊቅ ።

— ባርካሂ ጳውሎስ በመስቀልከ ዘወርቅ
ወሐመልማለ ወርቅ ገብርኤል ተዋነይ በእንተ ጽድቅ
ኅበ እንተ ርኁቅ ምዕራብ ወእንተ ርኁቅ ምሥራቅ
እስመ እንበሌሃ ወዚአሃ አልብነ ዘንጤይቅ ። ይላል

ከዚህ መቀጠል የሰበካው ጉባኤ ም/ሊቀ መንበር ባላምበራስ ፍቅሬ ወልደየስ ከዚህ የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል ።

ቅዱስነትዎ በተመረጡት ማግሥት በዘመናዊ ፕላን በመሠራት ላይ ያለውን ታሪካዊውን የደብረ ምሕረት ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ሥራ ሂደት ለመጎብኘት በዛሬዋ የተቀደሰች ዕለት በመካከላችን በመገኘትዎ የተሰማንን ታላቅ ደስታ በአዋሳና አካባቢዋ በሚገኙ ምእመናንና በቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ አሠሪ ኮሚቴ እንዲሁም በራሴ ስም ከፍ ያለ መንፈሳዊ ኩራት ይሰማኛል ካሉ በኋላ ሕዝቡ በደስታ ተውጦ ይህን ከፍተኛ ዕድል ስላገኘን ቸሩ አምላካችን ከልብ የመነጨ ምስጋና እናቀርባለን ብለዋል ።

ከዚህ ቀጥለውም የአዋሳ ከተማ በ፲፱፻፵ ዓ/ም እንደተቆረቆረ አውስተው የዚህ ታሪካዊ ሕንጻ መሠረትም ምክንያቱ ምን እንደሆነ መግለጽ አስፈላጊ ይሆናል ። በመሠረቱ ይህ አካባቢ ቀደም ሲል የእርሻና ከብት ማርቢያ እንደነበር ይነገራል ካሉ በኋላ ከተማው ዕድገት ሳያሳይ እስከ ፲፱፻፶፫ ዓ/ም በመቆየቱ የከተማው ሕዝብ ቤተ ክርስቲያን ለማግኘት እስከ ፳ ኪ/ሜትር ይጓዝ እንደነበረና ከፍተኛ ችግር እንዳጋጠመው ጠቅሰዋል ።

ከተማው ጥቂት በጥቂት ባሳየው እድገት ከላይ በተጠቀሰው ዓ/ም መቃኞ ተሠርቶ ታቦተ ቅዱስ ገብርኤል በጊዜው በነበሩት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ቡራኬ ገብቶ መገልገል ጀመረ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የከተማው ሕዝብ እየጨመረና እያደገ በመሄዱ ይህ ዘመናዊና የተሻሻለ ቤ/ክርስቲያን ሊሠራ መቻሉን(ማስፈለጉን)አመልክተው ይህ ታላቅና ተወዳዳሪ የማይገኝለት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የካቲት ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የመሠረት ድንጋይ ማኖራቸውንና ከመስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም የመሠረት ቁፋሮ ሥራ ተጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በመካሄድ ላይ መሆኑን በዝርዝር አስረድተዋል ።

ባላምባራስ ፍቅሬ ወልደየስ ንግግራቸውን በማራዘም በ፲፱፻፸፯ ዓ/ም የተጀመረው ሕንጻ ሥራ እስከ ፲፱፻፸፰ ዓ/ም የካቲት ወር ድረስ ሲካሄድ ቆይቶ ከመጋቢት ወር እስከ ሰኔ ፲፱፻፸፰ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ገንዘብ ሲገኝ የሰው ኃይል በመጨመር ገንዘብ ሲያጥር የሰው ኃይል በመቀነስና ጥንቃቄን በማድረግ ሥራው ሳይቋረጥ በመካሄድ ላይ ይገኛል ብለዋል። እያይዘውም በመጀመሪያ ጊዜ በመጠነኛ የኮሚቴ አባላት የተጀመረው የአባላት ብዛት ከፍ እንዲል ሁኔታው በማስገደዱ ዛሬ የሕንጻ ሥራ ኮሚቴ ብዛት ፩፻፴ የደረሰ መሆኑን አብራርተዋል ።

ኮሚቴዎቹ እንደብዛታቸው መጠን ልዩ ልዩ እቅድ ወጥቶ ከ0.50 ሳንቲም ተነሥቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ድረስ የሚሰጠው የምእመናን ርዳታ በየመልኩ ለመቀበል ያስችል ዘንድ በየደርጅቱ የሙዳየ ምጽዋት በማስቀመጥ በማዞርም ሆነ ተቀምጦ በመለመን በሰባት ቡድን ተከፋፍሎ መሥራቱን አንድ በአንድ ሰፋ ባለ መልኩ ገልጸዋል። ከዚህም ሌላ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መንበረ ፓትርያርክና ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ በተገኘ ከፍተኛ ርዳታ ጠ/ቤተ ክህነት ለርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ደብዳቤ በመጻፍ ትብብርና ሌሎች አንዳንድ የሃይማኖት ድርጅቶችና ግለሰዎች ባደረጉት አስተዋፅኦ የሕንጻው ደረጃ እዚህ ሊደርስ ችሎአል ሲሉ ገለጻቸውን ተንትነው አብራርተዋል ።

ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ እስካሁን ድረስ የፈጀው ፪ሚሊዮን፩፻፺፩ሺ፭፻፳፯ ከ፸፫(ሁለትሚልዮን አንድ መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ሰባትብር ከሰባ ሦስትሣንቲም)የፈጀ መሆኑን ጠቁመው ይህንንም ወጭ ጉልበት ሳይጨምር መሆኑንም አስረድተዋል ።

ባላምባራስ ፍቅሬ ወልደየስ ሪፖርታቸውን በመቀጠል ሲናገሩ «ከላይ እንደተገለጸው በ፲፱፻፸፬ ዓ/ም ኮሚቴ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ የኮሚቴው አባላትና ሌላውም ምእመን ሁሉ በገንዘብ ፤ በዕውቀትና በጉልበት ጭምር ደከመን ሰለቸን ሳይሉ የግል ሥራቸውን በመተው አንዳንዶቹ በራሳቸው መኪና በራሳቸው ወጭ የርዳታ ገንዘብ ለመሰብሰብም ሆነ ዕቃ ለመግዛት ወደ አዲስ አበባና ወደሌላም ሥፍራ በመሄድ አስፈላጊ ርዳታና ትብብር በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል ። ቀጥለውም የቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ በቶሎ ተሠርቶ እንዲያልቅ ማነቆ ከሆኑት ምክንያቶች ፤

፩ኛ/ ገንዘብ እንደተፈለገው አለመገኘቱ

፪ኛ/ ገንዘብ ሲገኝ ተፈላጊ ዕቃዎችና ማቴሪያሎች በመታጣቱ

፫ኛ/ ዕቃው ከተገዛም በኋላ ጭኖ የሚያመጣ መኪና በወቅቱ ባለመገኘቱ ።

፬ኛ/ እዚህ ቦታ ገንዘብ ተገኝቶአል ሲባል ሮጠን ሄደን ለማምጣት መኪና ከማጣታችን

የተነሣ ያስብነው ሳይሳካልን በመቅረቱ ነው በማለት አስገንዝበው በንግግራቸው መጨረሻም በቤተ ክርስቲያናችን የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ዘወትር በቅዳሴ ጊዜ ከሚነሡ ጸሎቶች ውስጥ አንዱን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ ካሉ በኋላ ይኸውም«ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ ሡናየ መልእክት ፈዋሴ ድውያን» የሚለውን ነው በማለት ሰፋያለው ሪፖርታቸውን ደምድመዋል ።

እያይዘውም ብፁዕ አቡነናትናኤል ትምህርት ሰጥተል ከትምህርታቸውም «እንኳን ከዚህ ዓመት ከዚህ ወርከዚህ ዕለት በሰላም አደረሳችሁ በተጨማሪም ካለፈው መስከረም ፲፯ ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በመላ ኢትዮጵያ ሲዘከር ሰንብቶአል ።

መስቀል በአንገት መስቀል በልብስ መስቀል በልዩ ልዩ መሣሪያችን በልዩ ልዩ ንብረታችን የምን ስለው የምንቀርጸው ጌጣችን ነው «ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ ከመ ያመስጡ እምገጸ ቅስት ወይድኀኑ ፍቁራኒከ»ለሚወዱህ ለሚያፈቅሩህ ለሚያምኑህ ለሚያመኩብህ ኃይለ መዊዕ (የድል አርማ ምልክት) ሰጣኻቸው ከጦር ተወርዋሪ ከጥይት በራሪ ይድኑ ዘንድ መስቀልን ምልክት አደረግህላቸው ይላል»ቅዱስ ዳዊት በመጽሐፈ መዝሙሩ ።

መስቀል መድኃኒት ነው፤መድኃኒት ስንል ሰዎች በልዩ ልዩ ቅመማ የሚያዘጋጁት አለ ግን የመስቀል መድኃኒት ከዚህ የተለየ ነው። የመስቀል መድኃኒትነት በተለይም መስቀል ለኢትዮጵያ ልጆች ፍቱን መድኃኒት ነው መስቀለ ኢይግፋዕ ይላል በሀገራችን መስቀልን የሚገፉ አይጠቀሙም ካሁን በፊት መስቀልን ለመግፋት የተነሡ ጠፍተዋል ። ዛሬ ደግሞ በሃይማኖት ስም መስቀልን የሚገፉ በሀገራችን ተነሥተዋል ። ነገር ግን መስቀል ለገፊዎች አይሆንም ኢትዮጵያዊ ሆኖ መስቀልን የሚገፉ መፈጠር የለበትምና ነው ።

ከሰው ሰው ከቦታም ቦታ ይመረጣል በተመረጡት ሰዎች አነሣሽነት በዚህ በተመረጠ ቦታ ይህን የመሰለ ሕንጻ ተሥርቶአል ። እግዚአብሔር በጭቃ በጨፈቃ በተሠራ ቤትም ይመለካል ይመሰገናል እርሱም ምስጋናው ከየትም በየትም ይምጣ ይቀበላል ።

ታድያ እንዲህ ዓይነቱ ሕንጻ በዚህ ቦታ ተሠርቶ እያለ በዚሁ እየተሰበሰቡ ፈጣሪያቸውን ማመስገን ሲገባ ወደባዕድ አምልኮና እምነት መሄድ ይበጃል ? አንድ ሰው ሚሽት እያለው ከሰው ሚሽት ቢገኝ ወይም የወንድ ሚሽት ባል እያላት ከሌላ ሴት ባል ብትገኝ አያፍሩም ? አይዋረዱም ? ከኅብረተ ሰቡ ዘንድስ አይወገዱም? አይጠሉም ? አይናቁም ? አይዋረዱም ?

እነ አብርሃ ወአጽብሐ እነ ቅዱስ ላሊበላ የሠሩአቸው አብያተ ክርስቲያናት ልብ ላላቸው ሰዎች ሰባክያን ናቸው ። በነዚህ ተሰብከው ባዕድ እምነት ከመከተል ያድናቸዋል ። ስለሆነም ወላጆች ልጆቻችሁን ያዙ ምከሩ ፤ አስተምሩ ፤ የሕግ ልጆቻችሁ እኮ ናቸው ሰው እኮ የራሱን ገንዘብ ራሱ ነው የሚጠብቀው እንጂ ማንም አይጠብቅለትም በማለት ምክራቸውን ለግሰዋል ።

ከዚህም በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የሚከተለውን አባታዊ ፤ ቡራኬ ሰጥተዋል ። «ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ የእግዚአብሔር ወገኖች (ልጆች) መሆናቸውን ቀደም ብሎ በመንፈስ ቅዱስ የተነገረ ነው ። ሌሎቹ ግን በየትም ሲባክኑ ኖረው በመጨረሻ ወደ እግዚአብሔር ፍለጋ የመጡ ይኖራሉ እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ወንድ በአርባ ቀኑ ሴት በሰማንያ ቀንዋ ተጠምቀን ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ተወልደን ያደግን ስለሆን ግራ ቀኝ ነፋስ ቢነፍስ ምንም ለመናወጥ አንችልም።

እኛ ኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን ከሩቅ ስናይ እንኳ ከመሬት ወድቀን ነው እጅ የምንነሣው ሌላው ሰው ወይም የኛን እምነት ያልተከተለ እንዲህ ዓይነት የተቀደሰ ሥራ ለመሥራት አይሆንለትም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረበት ዘመን «ሰው ዓለሙን ሁሉ





www.ethiopianorthodox.org

ቢያተርፍ፣ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል ? ብሎ እንደ ተናገረው ሁላችንም ዓለምን ለማ ትረፍ ሳይሆን የዕለት እንጀራ ለማ ግኘት ነው ። ዓለምን በሙሉ ለማ ትረፍ ብንችል እንኳ ምንም እንደ ማይጠቅመን ቃሉ በሰፊው ያስ ተምረናል ብለዋል ።

እያይዘውም ቅዱስነታቸው ቅዱ ሳት መጽሐፍት እግዚአብሔርን እንድንወድ ያዘናል ። እግዚአብ ሔርን መውደድ ማለትም እግዚ አብሔር የማይወደውን አለመሥ ራት አለመከተል ማለት ነው»ካሉ በኋላ እርስ በርሳችን መልካም ሥራ ብንሠራ እግዚአብሔርን እንደ ምንወድና እርሱም እኛን እንደ ሚወደን ራሳችን ምስክሮች ነን ሌላ ሰው አይመሰክርልንም ማመን ዓለማመናችን የምናውቀው እኛው ራሳችንና እግዚአብሔር ብቻ ነን ። የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ሁሉ በምንም ዓይነት በማንም ላይ ክፉ ሥራ አይሠራምና ብለዋል ።

ስለመስቀል ደግሞ የእግዚአብ ሔር ልጆች ነን ካልን እግዚአብ ሔርንም በፍጹም ልባችን በፍጹም ነፍሳችን እንወደዋለን ካልን በእጃ ችን በአንገታችን በልብሳችን የምና ብረቀርቀውና የምናጌጠው መስቀል ከልብ እንዲሆን ይገባል ። ኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር እግዚአብሔር ከኢትዮጵያ የተለ ያዩበት ቀን እንደሌለ ተነግሮአል ። በእርግጥ እግዚአብሔር ከኢትዮ ጵያ ተለይቶ አያውቅም ሊለይም አይወድም ኢትዮጵያውያን ባልሆኑ ኢትዮጵያዊ ሥራ በማይሠሩና የኢ ትዮጵያውያንን ሥራ እምነትና ባሕል በሚነቅፉ በሚያንቋሽሹና በ ሚንቁ ሰዎችመካከልእንደማይገኝና እንደማይኖር ግን የታመነ ነው ።

በ፴ኛውና በ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተሠሩት ውቅር ሕንጻዎች እዚህ ከሠራችሁት ሕንጻ ቤተ ክር ስቲያን ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ለማ ነጻጸር የሞከሩት በክርስትና እምነ ታችሁ የሠራችሁትን መልካም ሥራ ደስብሎአችሁ እስከ መጨ ረሻ ድረስ እፍጻሜ አድርሳችሁ ለማየት እንድትችሉ ነው ።

የላሊበላና በሰሜን ክፍላተ ሀገራት የሚገኙት የሌሎች ቅዱሳን ውቅር ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት ባሳ ለፍናቸው ፲፯ ዓመታት የነበሩት ገዥዎችና የገዥዎች ተዋረድ ባለ ሥልጣናትበላዩላይ መድፍ ተክለው ሲተኩሱበት በሌላ ቦታ ሆነውም እያስኰተሱበት ፈረካክሰውታል፤ እናግተውታል ሰነጣጥቀውታል ። ባሁኑ ጊዜ ለውጭ አገር አምባሳ ሳደሮች ነግረን በመረባረብ ላይ ናቸው ።

ኢትዮጵያውያን በሃይማኖ ታቸው መከራ አይፈታቸውም በም ቾትና በጸሎት የነበሩ አምባ ገነ ኖች ገዥዎች ወገኖቻችንን እየጨ ፈጨፉ እግዚአብሔር የለም እያሉ መከራ ሲያጸኑባቸው ከእምነታቸ ውና ከዓላማቸው ፈቀቅ አላሉም ። ከረሀብ ከበሽታ ፣ ከስደት ሌላ ደግሞ የጥይት በረዶ ሲጨፈጭ ፋቸው መርዝ ሲርከፈከፍባቸው ፣ እግዚአብሔርን አማርረውና ክደ ው ከእምነታቸው ዝንፍ ለማ ለት አልፈለጉም ። በዚህ መከራ ውስጥ እያላችሁ ነው እናንተም ይህን የመሰለ ሕንጻ ቤተ ክርስ ቲያን መሥርታችሁ በሥራው ስት ረባረቡ የነበራችሁ፤ ይህም ራሱ የሃይማኖታችሁ ጽናት ይመሰክር ላችኋል ።

እዚህ ላይ አንድ የውጭ አገር ጋዜጠኛ የተናገረው ትዝ ይለኛል። «ኢትዮጵያውያን በሃይማኖታቸው የማይበሉና የሚበሉ እንስሳትና አ አራዊት በሀገራቸው በብዛት እ ያሉ በረሀብ ፣ በበሽታ በእርዛትና በችግር በመከራ እንዲሁም በጥይት በረዶ ሲጨፈጨፉ ሃይማኖታቸው እንዳይረክስባቸው በልተን እን ሙት አላሉም አልነኩአቸውም እን ደተጸየፏቸው ሃይማኖታቸውን ጠ ብቀው በረሀብ ዝም ብለው አለቁ እንጂ» ብሎአል ።


በእንደነዚህ ዓይነቱ ሰዎች ላይ እጅግ መራራና ዘግናኝ ግፍና በደል የፈጸሙ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይ ወታችን በክርስቲያናዊ ዓላማችን እንቃወማቸዋለን ። የምንቃወም ውም ክፉ ግብራቸውን ነው እንጂ እነርሱንም አይደለም ። እነርሱማ ወንድሞቻችን ናቸው ።

የተከበራችሁ የክርስቶስ በጎች ምእመናን ባሁኑ ጊዜ እኛ ሁላችን በአንድነት በኅብረት በወንድማማ ችነት በፍቅር ሁነን ለሰላም መሰ ለፍ አለብን ። ሰላምን እጥታ ስት ታመስና ስትበጠበጥ ስትናጥ የነ በረችው ሀገራችን ሰላምን ማግ ኘት አለባት ። ሰላም ለሰዎች ብቻ አይደለም የሚያስፈልገው ሰላም ለምድር እንስሳትና አራዊት ለሰ ማይ አዕዋፍና ለጥቃቅን ፍጥረ ታት ሁሉ የሚበጅ ነው ። ሰላም ከሌለ ባንድነት በፍቅር በመወያየት በሃይማኖት ጸንቶ ተረዳድቶ በልቶ ጠጥቶ አጊጦ ድሮ ኵሉ ሠርቶ አግኝቶ ለመኖር አይቻልም ።


ስለዚህ ሀገራችንን የሰላም አገር እናድርጋት እያንዳንዳችን ለሰላም ከተሠለፍን ሀገራችን ኢትዮጵያን ከዳር እስከ ዳር የሰላም የፍቅርና የአንድነት አገር ልናደርጋት እንች ላለን የሰላም ጠንቆች በጥባጮ ችና አዋኪዎች የሆኑና ሰላምን የሚነሡን ሁሉ እኛው ለሰላም የተመቸን ሁነን ስላልተገኘን ነው» ካሉ በኋላ የሰላም አምላክ ሰላሙን ለሀገራችን ይስጥልን»በማለት የተ ቀደሰ ፣ ቡራኬአቸውን ሰጥተው እንዳበቁ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።

በመጨረሻም ቅዱስነታቸው ከ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመ ሠራት ላይ ያለው ሕንጻ ቤተ ክር ስቲያኑን አንድ በአንድ እየተዘ ዋወሩ ጎብኝተዋል ። ከዚያም ጽ/ ቤቱን የስብከተ ወንጌል ትምህ ርትና መዝሙር ሲከታተሉ ነበር ። ቅዱስነታቸው ከሥፍራው ሲደርሱ የደብሩ ሰንበት ት/ቤት መዘም ራን «ባርከኒ አባ በእንተ ሰላማ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን»እያሉ ተቀብለዋቸዋል ። ከዚሁም በመ ቀጠልቅ ዱስነታቸው ቃለ በረከታ ቸውን አስተላልፈውላቸዋል ።





ቅዱስነታቸው በመሠራት ላይ ያለውን የአዋሳ ደ/ምህረት ቅ/ገብርኤልን ሕንፃ በጎበኙበት ወቅት



ቅዱስነታቸው በአዋሳ አሸኛኘት ሲደረግላቸው

«እናንት ወጣቶች ተምራችሁ እው ቃችሁ ከዚህ ደረጃ ደርሳችኋል ። ካሁን በኋላ ግን እንደገና ወዳለ ማወቅ ሥፍራ አትሂዱ ለመሆኑ ከያሬድ የበለጠ ዘማሪ አለ ? ከኢ ትዮጵያውያን የበለጡ ዘፋኞችስ ፣ አሉ ? የባዳ ሥር መሠረት የሌለው መዝሙር ያስፈለገው እምኑ ላይ ነው ? የእናንተ ኃላፊነት ነው፥ ለኃላፊነታችሁ በቂ መልስ ለመ ስጠት እንድትችሉ አሁኑኑ የተ ዘጋጃችሁ መሆን አለባችሁ በማ ለት ካበረታቱአቸው በኋላ የጉብ ኝቱ ሰዓት አብቅቶ ወደአዲስ አበባ ተመልሰዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

# እውነቱ ሲገለጥ የሚያረው ማን ነው

የግል ቤተ መጻሕፍት

ከልሳን ኦርቶዶክስ

ሐሰቱን እውነት እውነቱን ሐሰት አስመስሎ ወተቱን አጥቁሮ ፣ ማሩን አምርሮ ፤ በአስመሳይ ቃላት አኽጕርጕሮ፣ ሕዝቡን ግራ ማጋባት እንደ ሙያ ተቈጥሮ ብዙዎች ሃይማኖታውያን ነን ባዮች ሲጠቀሙበት ማየት ምንኛ ያሳፍር ? በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊ ዓለም ሐሰትን በእውነት ጠቅልሎ በማሳየት ለጊዜው ማስመሰልና ማወናበድ የሚቻል ቢመስልም ውሎ አድሮ ጨለማና ብርሃን እንደማይስማሙ ሁሉ እውነትና ሐሰት ተቃራኒ ናቸውና ጨለማው ሐሰት ተወግዶ እውነቱ ብርሃን ሲወጣ የአዋናባጅ ትርፉ ሐፍረትና ቅሌት ብቻ ሁኖ ይቀራል ።

እጅግ በጣም የሚደንቀው ሐሰት ከሚወገዝበት ፣ እውነት ከሚሰበክበትና ከሚጠበቅበት የቤተክርስቲያን ጉዳይ ላይ የሐሰት መድረክ መከፈቱ ነው ! !

በመሠረቱ እውነት ከሚጠቅም በቀር ማንንም አይጐዳም ፣ ሃይማኖት ካለ ! ! ነገር ግን እምነታቸው ያልተስተካከለ ፣ ሁሉም የሚሆነው በእምላክ ፈቃድ መሆኑን የሚጠራጠሩ ሰዎች ከእውነት ይልቅ ሐሰትን ይመርጣሉ ፣ በተንኰል ይጠቀማሉ "ተንኰል ካለ ዘንድ እግዚአብሔርን መፍራት አይኖርም ።" እስመ ኀበ ምይንት ነፍስ ኢተኃድር ጥበብ "በተንኰል ከተሞላች ነፍስ (ሕይወት) ውስጥ ጥበብ ፈሪሐ እግዚአብሔር አታድርም ተብሎአልና ። እግዚአብሔርን ከማይፈራ ማንኛውም ሰው ሃይማኖት ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም ።

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነው ሁሉን ማድረግ የሚችል ልዑል እግዚአብሔር በማይመረመር ረቂቅ ጥበቡ ይህችን ታሪካዊት፣ቀዳማዊትና ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ከሃይማኖት የለሹ ፋሺት ደርግ መንጋጋ መንጥቆ አውጥቶ ነፃነቱን ሲያጎናጽፋት በሕገ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ቀደም ሲል በደርግ ጠብመንጃ አፈ ሙዝ በእነ ዶ/ር ተፈራ ወንዴ አስገዳጅነት የተሾሙባት አባ መርቆሬዎስን ከነበራቸው ደርጋዊ ሥልጣን አውርዳ አሁን በሕገ ቤተ ክርስቲያን ከማንም ባለሥልጣን ተፅዕኖ ውጭ (ነፃ ሁና) ቅዱስ አባትዋን በምትመርጥበት ጊዜ ጎጠኛነት ዘረኛነት የ ተጠናወታቸው አንዳንድ የሐሰት ፕሮፖጋንዲስቶች በዶክትሬት ስም ለመጠቀም የሚያደርጉትን የሕልም ሩጫ (እሽቅድድም) ነው ።

እነዚህ ሰዎች የማሰብ ችሎታ ያላቸው አይመስሉም እንጂ የሕልም ሩጫ የትም የማያደርስል ከተጋደሙበት የማያንቀሳቅስ የአእምሮ ብክነት መሆኑን በተገነዘቡ ነበር ። እነዚህ በተንኰል የተካኑ በፍቅረ ንዋይና በፍቅረ ሢመት የሚባንኑ ግለ ሰዎች ቀደምሲል "የምእመናን ጩኸት (ጥያቄ)" በሚል ርእስ የበተኑት ባለቤት የሌለው ጽሑፍ

፩/ "ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከጳጳሳቱ የተለየ ምን አጠፉ ?

፪/ በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ ከተሾመ ቤተ ክርስቲያን ትከፈላለች ፣ ፓትርያርኩ ያለ ጥፋት አይሻሩም" እና ሌላም ሌላም በማለት ቀባጥረዋል ። እረ ለመሆኑ እውነቱ ሲገለጥ እርቃናቸውን የሚወጡና የሚያፍሩ መሆናቸውን ማወቅ እንዴት ተሳናቸው ?

ከዚህ አልፈው ተርፈው ደግሞ "የጎንደር ድምፅ ይሰማ" በሚል ርእስ በስድስት ገጽ ያሰፈሩት ከቤተ ክርስቲያን ሰዎች የማይጠበቅ የጠባብ ብሔር አመለካከት ጽሑፍ ማንነታቸውን አጕልቶ የሚያሳይ የሚዳ መነጽር ሆኖ ተገኝቷል ።

ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ሕግንና ፍትሕን የሚያመነጩ ፣ በሕግ በሥርዓት የሚተዳደሩ በልዩ ጥበባቸውና ዕውቀታቸው ዓለም በሙሉ የሚያውቃቸውና የሚያደንቃቸው መሆናቸው የሚታወቀው አሁን ከጎንደር መንግሥት ምሥረታ ፫፻ ዓመታት በኋላ ሳይሆን ቀደም ብሎ ከ፬ሺ (አራት ሺህ) ዓመታት በፊት እንደ ነበረ ማወቅና መረዳት ይገባቸው ነበር ። ይህን ለማወቅ ባለመታደላቸው ግን "ጐንደር የሕግና ፍትሕ ምንጭ የወግና ሥርዓት ሀገር ናት ፤ ጐንደር የዕውቀትና የጥበብ ሀገር ፤ ለነፃነት ስትታገል የኖረች» - - - እና ሌላም ብዙ ተችተዋል ። እውነት ነው አይጠረጠርም በኢትዮጵያዊነትዋ ከኢትዮጵያውያን ጋር ። ለመሆኑ ጎንደር ከኢትጵያ አካላት አንዷ አካል መሆንዋን የተጠራጠረ ሰው አለ ብለው ነው የሚደክሙት ? ጥበቡ ዕውቀቱ፣ የሕግና ፍትሕ ምንጭነቱ የአባቶቻችን ኢትዮጵያውያን መሆኑ ቀርቶ ጎንደር በእነ ዓፄ ፋሲል ከተመሠረተች ወዲህ ነው ሕግና ፍትሕ የመነጨው ብለው የሚያምኑ ከሆነ ደግሞ ተሳስተዋልና ስሕተታቸውን ከአሁኑ ያርሙ ።

ጐንደር አብዛኛው ጊዜ ከዓፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ወዲህ እስካሁንም የሊቃውንት ማስተናገጃ ሁና ያለች መሆንዋ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚያውቀው ነው ። እነዚህም ሊቃውንት ብዙዎቹ የትግራይ ፣ የሸዋ የጎጃምና የወሎ የሌሎችም ክፍለ ሀገር መሆናቸው ጸሐፊው ማስተባበል አይችሉም ። ስማቸውንና የትውልድ ቀያቸውን ጭምር መዘርዘር ይቻላልና ። እንዲህ መሆኑም ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ የሚያስደስትና የሚያኮራ እንጂ ጠባቦችን ብቻ የሚመለከት አይደለም ። ጎንደር የጋራችን ሀገር ናት እንኮራባታለን ።

በጣም የሚደንቀው ቱሪስቶች ጎንደርን እንዳይጐበኙ የተከለከሉ አስመስሎ መቅረቡ ከቶ ማን ይሆን? ጐንደር እንድትከለከል ያደረገ ስለዚህ ጉዳይ በከፍተኛ ደረጃ የምንመለስበት ሁኖወደተንሣንበትየቤተ ክህነቱ ጉዳይ እንመለስና ጽሑፉ ጐንደሬ የሆነውን ሁሉ ከመደበኛ ሥራው ማስወጣት ከደረጃውና ከክብሩ ዝቅ ማድረግ ተግባር የበለጠ ቤተክህነቱ ላይ ጎልቶ ይታያል»ካለ በኋላ«ቤተክህነታችንምየፍትሕ የእኩልነት ፣ የእውነት መገኛ ተቅዋም መሆን ሲገባት የወቅቱ ሁኔታዎችን በመከተልና የጊዜውን ኃይል በማንፀባረቅ ቅድሚያን ወስዳ ጎንደሬዎችን ስታሳድድ ትገኛለች »ወዘተ ብሎአል ።

ይህ ጽሑፍ ማንንም የጐንደር ሕዝብ የማይወክል የአባ መልከጼዴቅ እና መሰሎቻቸው የግል መሆኑ እየታወቀ አባ መልከጼዴቅ በንጹሕና ፍጹም ኢትዮጵያዊ ወኔ ባልተለየው የጐንደር ሕዝብ ስም ለመጠቀም አስበው "ለጎንደሮችም እኮ ሀገር አላቸው " በማለት ለማለያየት ሞክረዋል ። አዎን ለጐንደሮች ሆነ ለሌሎችም ኢትዮጵያውያን ሁሉ ኢትዮጵያ ሀገራቸው ናት ፣ የምታኮራ ታሪካዊትና፣ ጥንታዊት ሀገር አለቻቸው በዚህች እኩሪ ሀገራቸው ጸንተው ለዘለዓለም ለልጅ ልጆቻቸው ያወርሳሉ ።

አቡነ መልከጼዴቅ በገዛ ራሳቸው በትዕቢት ተወጥረው ከደርጉ መኰንን አቡነ መርቆሬዎስ አልለይም ብለው ሥራቸውን ትተው ለመፈርጠጥ አስበው ይህንና ሌላም ከክርስቲያን የማይጠበቅጽሑፍበኢትዮጵያን ሪቪውና በሌላም በመጻፍ ሕዝብን ግራ ለማጋባት ጣሩ እንጂ በመሠረቱ ቀደም ሲል የጻፏቸው መጻሕፍት ሕገ ቤተክርስቲያንንያል ተከተሉ ፣ የተወገዙ የመናፍቃንን ትምህርት የሚያንጸባርቁ ሁነው በመገኘታቸው የኢትዮጵያ ኦ - ተ - ቤ - ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ እንዳይታተሙ ከከለከሉ በኋላ የእምነት ልጃቸው ፣ የክብር አባታቸው አባ መርቆሬዎስ ናቸው በግል ሥልጣን ፈቅደው እንዲታተሙ ያደረጉአቸው እሳቸውንም ለሹመት ያበቋቸው ።

ይህም ነገር በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና በከፍተኛው መንፈሳዊው ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከፍተኛ ንቅናቄን ስላስነሣና ተቃውሞን ስላሰማ የአባ መርቆሬዎስ ልዩ ረዳት ጳጳስ የነበሩት አባ ዜና ማርቆስ መጻሕፍቱ እንዳይሸጡእን ዳይለወጡ ፣ ከቶ ገበያ እንዳይወጡ ሴርኩላር ማስተላለፋቸውን አባ መልከጼዴቅ ሊረሱት አይገባቸውም ነበር ። ቍስላቸውን እንዴት ይረሳሉ ?

አባ መልከጼዴቅ ይህ ሁሉ የቆጥየባጡን የሚቀባጥሩት አባ መርቆሬዎስን ወደ ደርጋዊ ሥልጣን ለመመለስ ባላቸው ቅጅታዊ ምኞት ነው ። ነገር ግን የአባ መርቆሬዎስ መመለስ ከእንግዲህ የእናታቸውን ጡት መጥባት ያህል ይመልከቱ ትና በውል የማያውቋቸው ከሆነ እስኪ አሁን ከአባ መርቆሬዎስ ጋር በውል እናስተዋውቃቸው ። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በከፍተኛ ፀፀት እንደሚያስታውሰው ከ፲፰ ዓመታት በፊት የተነሣው (የተቀጣጠለው) የሰይጥ እሳት ነኝ ባዩ ወታደራዊ መንግሥት "ሃይማኖት የአብዮት ጠንቅ ነው" በማለት ሃይማኖትን ከምድረ ኢትዮጵያ ጨርሶ ለመደምሰስ በነበረው ከፍተኛ ምሥጢራዊ ዕቅድ በመጀመሪያ ለዚሁ አረመኔያዊ ተግባሩ ተባባሪ ወይም ሥራ አስፈጻሚ የሚሆኑለት ፣ ሃይማኖታውያን ሳይሆኑ መሳዮችን ማጥናት ሞከረ ።

በዚህም በወሰደው ጥናት ለዚህ ፀረ ሃይማኖት እንቅስቃሴው ተባባሪ የሚሆኑት ያሁኑ ብፁዕ ወቅዱስ የዚያን ጊዜ አባ ዘሊባኖስ ሁነው አገኛቸው ። ምክንያቱም አባ ዘሊባኖስ የዚያን ጊዜ ከተቋቋመው ማህበረ ካህናት ውስጥ ሠርገው በመግባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እንዲያዙና እንዲገደሉ ሌሎችም ጳጳሳት እንዲታሰሩ ካደረጉት አንዱ ምክትል ሰብሳቢ እሳቸው ነበሩና

በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ኦ ተ፣ ቤተ ክርስቲያን ከእስክድርያ ቤተ ክርስቲያን የነበራትን ጥንታዊና ታሪካዊ ግንኙነት አጣች ፤ እንዲያውም ተወግዛ ተለየች ። በዚህ ደርጋዊ የሥራ ፍሬያቸው ። ለከፍተኛ መንፈሳዊ አባትነት በዚሁ ፀረ ሃይማኖት ፋሺሽታዊ መንግሥት ታጩና ብፁዕ አቡነ ማርቆሬዎስ ተብለው ተጸጸሱ ፤ የጎንደ ጳጳስ ተባሉ ።

የጎንደ ጳጳስ ተብለው አንድ ጊዜ ከተሰየሙም በኋላ በሕገ ቤተ ክርስቲያን (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ቍጥር ፪፻፱ መዛወር አይገባቸውም ነበር ። አንድ ኤጲስ ቆጶስ "ሀገር ጠበበኝ ፤ ሕዝብ አነሰኝ፣ብሎ ወደ ሌላ ሀገር መዛወር አይገባውም" ይላልና ኢ - ሕ - ዲ - ግ - በድል ሲቃረብ ኢሠፓ በፃዕረ ሞት በተገኘበት ጊዜ ከቤተ ክእርስቲያን ሀብት ብር ፲ሺ ሰጥተው አመንዝሰው ወደ ውጭ ከላኩት ፤

የጐንደርን ሕዝብ ያስፈጅና ይጨፈጭፍ ከነበረው ከሻለቃ መልእኩ ተፈራ ጋር ቀደም ሲል በነበራቸው ምሥጢራዊ ግንኙነት የብፁዕ አቡነ እንድርያስ ሀገረ ስብከት የነበረውንጐንደርን በመንጠቅ ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ከመንበረ ጵጵስናቸው እንዲባረሩ አደረጉ ።

መልእኩ ተፈራ የጐንደርን ወጣት በሚቀስፍበት ጊዜ ብፁዕ አቡነ





www.ethiopianorthodox.org

እንድርያስ የተቃወሙትን እሳቸው አሜን ብለው ተቀብለው የመቅሰፍቱ ተባባሪ ሆኑ ።

## ሀ/ በጐንደር ያደረሱት ሌላው ጥፋት

፩፣ ጎንደር እንደ ገቡ ዓዲ አርቃይ ድረስ ለጐብኝት ኺደው "በዋልድባ" ያሉት መነኮሳት ወያኔዎች ናቸው ፤ በቆባቸው ቦምብ ተሸክመው ይኼዳሉ ፤ ስለዚህ እነዚህን መነኮሳት በሙሉ ደምስሶ በሌሎች መዋቀር አለበት በማለት ከመዛታቸውም በላይ ለገዳሙ የተላከውን ርዳታ ሀ/ ፭፻ ኩንታል ስንዴ ለ/ ፭፻ የብርድ ልብስ ፣ ሐ/ ፭፻ ማጭድ ፡ መ/ ፻ ጣቃ አቡጀዴድ ፣ ሠ/ ፲ መዶሻ ረ/ ፲ ድጅኖ ፣ ሰ/ ፲ የብረት ድስት የንፍሮ መቀቀያ (ጎላ) ቀ/ ፲ ባልዲ ከገዳሙ ነጥቀው በጓላቸው የጐንደር ሕዝብ ለሚጨፈጨፍበት አብዮታዊ አገልግሎት እንዲውል አድርገዋል ።

፪/ በ፲፱፻፸፭ ዓ/ም አራት መነኮሳት ከዋልድባ ቅስና እንቀበላለን ብለው ወደ እሳቸው ቢመጡ "ወያኔዎች ናቸው" በማለት አሳስረዋል ።

፫/ "አቋቋሙን እናስመሰክራለን" ብለው ከመላዋ ኢትዮጵያ ተውጣጥተው በጎንደር ከተማ የተገኙትን ወጣት ሊቃውንትን ለብሔራዊ ውትድርና አስገድደዋል ።

፬/ አባ መርቆሬዎስ የብፁዕ አቡነ እንድርያስን መንበር በግፍ ከወረሱ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያልፈጸሙት በደል ባይኖርም አብያተ ክርስቲያናት መባዕና ዕጣን በማጣት ሲዘጉ በርዳታ የተገኘውን የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በሥልጣናቸው በመጠቀም በ፪ሺ የሚቆጠር ገንዘብ ለኳስ መጫወቻ ሜዳ አገልግሎት እንዲውል አድርገዋል ።

፭/ ፋሽሽት ደርግ በግፍ የረሸናቸው የጎንደር ክርስቲያኖች ጸሎተ ፍትሐት እንዳይደረግ ከልክለዋል ፤ (ደርግን ባለማምለካቸው ይሆን?)

፮/ አባ መርቆሬዎስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያደረሱት በደል የሚያሳዝነውና የሚያበሳጨው ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የዓለም ክርስቲያኖችን ጭምር መሆኑ ቢታወቅም አንጋፋውና የሥቃዩ ገፈት ቀማሽ የጎንደር ሕዝብ መሆኑን ማስተባበል እነአባ መልከጼዴቅ አይችሉም ። እንዲያውም የጎንደር ሕዝብ ትዕግሥት ሰፊ በመሆኑ ነው እንጂ አባ መርቆሬዎስን በጎንደር አደባባይ አቅርበን በቀላችንን እንወጣው" ማለት ይችል ነበር ።

፯/ ከብፁዕ አቡነ እንድርያስ በፊት የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ለቤተ ክርስቲያን የተዉትን ወርቅ ሸጠው በግል ተጠቅመውበታል ።

፰/ በጎንደር ከተማ የአ -ኢ- ሴ - ማ - በዓል በዓቢይ ጾም ሲከበር ፈሪዳዎች ታረዱና ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ተጠርተው ጮማ እንዲቆርጡና ውስኪ እንዲጨልጡም ታዘዙ፡ በዚህ ጊዜ ሀ/ አቶ ደምሴ ኃይሌ ፣ ለ/ ግራዝማች (አለቃ) ውበቱ ፣ ሐ/ አለቃ ታደሰ የመካነ ኢየሱስ ሊቅና መ/ ሌሎችም ብዙ ምሁራን ቀሳውቅት አድራጎቱን በመቃወማቸው እየተገረፉ አይቀጡ ቅጣት ተቀጥተው ሲያልቁ አባ መርቆሬዎስ የግፉ ተባባሪ ነበሩ ።

፱/ የኢሠፓ አባልነታቸውን ደብተር እያወጡ ምእመናንን ያስፈራሩና ያስበረግጉ እንደነበሩም ማንም የሚያውቀው እውነት ነው ።

፲/ መልአኩ ተፈራ የወላድን ማሕፀን ሲያመክንና "ለዚህ ሕዝብ ጥይት ማባከን አያስፈልግም" በማለት ፸—፹ ያህል ሕዝብ እጅ እግሩ እየታሠረ በገልባጭ መኪና ተጭኖ ወደ ሊማሊሞ ገደል ተወስዶ በሕይወት እያለ ሲገለበጥ አባ መርቆሬዎስ ተባባሪ እንደ ነበሩ ሕዝብ የሚያውቀው ነው ።

፲፩/ ፓትርያርክ ቀርቶ ሰብአዊ አመለካከት የሌላቸው አባ መርቆሬዎስ ሃይማኖትን ለማጥፋት ከደርግ ኢሠፓ ጋር ባላቸው የጠበቀ ቃል ኪዳን ለከፍተኛ ሥልጣን ታጩና በድርጊታዊ አሠራር ተመርጠው የብሔራዊ ሸንጎ አባል ተባሉና የፋሽስታዊ መንግሥት አባልነታቸውን በይፋ አስታወቁ ። ከኢትዮጵያ ፈላጭ ቆራጭ የፋሽሽት መንግሥት አባል ለመሆን በቁ ፣ በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ቍጥር ፻፺፱ የተደነገገውን ጣሉ አፈረሱ ።

## ለ/ በፓትርያርክነት ሥልጣን የፈጸሙት በደል

ዘረኛ በመሆን ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያንዋን አስተዳደር የቤተሰብ መምሪያ አድርገዋታል ። ማስተባበል የሚሞክር ይኖር ይሆን ! ማስረጃ አለና ይረጋገጥ ፣ ማስረጃው

፩/ የፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ

፪/ የፓትርያርኩ ልዩ ጸሐፊ

፫/ የቅዱስ ሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ

፬/ የቅዱስ ሲኖዶሱ ቃለ ጉባኤ ጸሐፊ

፭/ የመንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን

፮/ የውጭ ግንኙነት መምሪያ ኃላፊ

፯/ የሕግ አገልግሎት መም/ኃላፊ

፰/ የድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ

፱/ የልማት መምሪ/ም/ዋና ጸሐፊ

፲/ የሰንበት ት/ቤት መ/ዋና ጸሐፊ

፲፩/ የአ - አበባ ሀ/ስብከት የፓትርያርኩ ልዩ ሀገረ ስብከት በማድረግ ሥራ አስኪያጅ

፲፪/ ዋና ጸሐፊው

፲፫/ የትምህርትና ስብከት ኃላፊው እና ፲፬ኛው የሀገረ ስብከቱ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ክፍል ኃላፊ ፤ እነዚህ ሁሉ ቤተሰቦቻቸው ናቸው ።

፲፭/ በዚህ ልዩ ሥራ አስኪያጃቸው እየተመለመሉ በአዲስ አበባ አድባራት የሚመደቡት የአድባራት አለቆች ፣ ካህናትና ዲያቆናት ሁሉ የእሳቸው ቤተ ሰቦች ናቸው ። በየዞኑ እየተመለመሉ የሚሾሙት ሥራ አስኪያጆችም እነሱው ናቸው ።

፲፮/ የትግራይ የኤርትራና የሌሎችም ክፍላተ አህጉር ምሁራን ፣ ካህናትና ዲያቆናት «ወያኔዎች ናቸው» በማለት በከፍተኛ ተግሣጽ ሲባረሩ ኑረዋል ። በዚህ ምክንያት ከእናታቸው ጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን የተለዩ ካህናትና ዲያቆናትን በመቍጠር ጊዜ እናባክንም ጊዜ አለውና ።

፲፯/ በውጭ ሀገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኦ - ተ - አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ በመሪነትም ሆነ በተራ አገልጋይነት የሚመደቡት ሊቃነ ጳጳሳት ፣ ካህናትና ዲያቆናት ሁሉ አባ መርቆሬዎስ ከበቀሉባት ወረዳ የተገኙ ናቸው ካስፈለገ ዘርዝሮ ማቅረብ ይቻላል ።

## ሐ/ የፋሽሽት ደርግ አባል በመሆን ያደረሱት ጥፋት

፩/ በጦርነቱና በድርቅ ምክንያት ለተዘጉት አብያተ ክርስቲያናት የመጣውን የውጭና የሀገር ውስጥ ርዳታ በሥልጣናቸው በመንጠቅ በብዙ መቶ ሺሕ የሚቈጠር ገንዘብ ለጦርነት እንዲውል አድርገዋል ። እሳትን በሚተፉ ጀቶች አብያተ ክርስቲያናት እንዲቃጠሉ ተባብረዋል ። ካህናትና ምእመናን እንዲያልቁ ተስማምተዋል ።

፪/ ከአዲስ አበባ አድባራትና ከሌሎችም አድባራትና ገዳማት በሙዳየ ምጽዋትና በስእለት የተገኘውን ገንዘብ አሁንም ለፋሽሽት ደርግ ሰጥተው የካህናት ቤተሰቦችን አስርበዋል በዚህም ምእመናንን አሳዝነዋል ተስፋ አስቆርጠዋል ።

፫/ ከሁሉ የከፋ ደግሞ ስንኳን ፓትርያርክ ቀርቶ ተራ ምእመን ቢሆን የማይመደብበት «እግዚአብሔር የለም" ከሚለው ከሐዲ መንግሥት በኢሠፓ አባልነት ተመድበው የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በርሱ የሚተላለቅበትን የክተት አዋጅ አውጀዋል ፤ በዚህም የከሐዲ መንግሥት አባልነታቸውን አረጋግጠዋል ።

፬/ በጸሎተ ሃይማኖት የምትጠበቀውን ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ መሣሪያ በታጠቁና በሻለቃ የሚመሩ ወታደሮችን በማሰለፍ መነኮሳት ቆባቸውን ካህናትን ጥምጥማቸውን እያስወለቁ እንዲፈተሹ አድርገዋል ።

፭/ ከታላላቆቹ የእግዚአብሔር ትእዛዛት አንዱ "በሐሰት አትመስክር»የሚለው ሲሆን እሳቸው ግን ይህን ታላቅ የእግዛዚአብሔር ቃል በመተላለፍና የሐሰት ምስክርነታቸውን በመስጠት ፣

ሀ/ «ወያኔ ሰማንያ ሦስት አብያተ ክርስቲያናትን አቃጠለ

ለ/ ሠላሳ ካህናትን ገደለ

ሐ/ የካህናት ሚስቶችን ደፈረ

መ/ ንዋየ ቅድሳትን ዘረፈ

ሠ/ አብያተ ክርስቲያናትን የመጋጃ (የጋማ ከብት) ማጐሪያ አደረገ"

በማለት በሐሰት በመመስከር የሐሰት መሪ ሁነዋል ።

፮/ ፳ሺ ዲያቆናትን በማዝመት አብያተ ክርስቲያናትን ለማዘጋትና ዲያቆናትን በጦርነት እሳት ለመማገድ ቈርጠው ተነሥተው ነበር ፤ ነገር ግን እለቃቸው ጥሎአቸው በመፈርጠጡ ዓላማቸው ከሸፈ፣ ውሀ ውስጥ የገባች አይጥ መስለው ቀሩ

## መ/ ኢ. ሕ . አ. ዲ. ግ. ከገባ ስኋላ

ሀ/ «ምእመናን ያልመረጡአቸው የደርግ ሹም አባ መርቆሬዎስ ሥልጣኑን ይልቀቁ»ሲባሉ እንደገና ነቢያተ ሐሰትን በብሕትውና ስም አስነሥተው«ቅዱስነታቸው ስለተቀየሙ በእሳቸው እጅ ካልተጠመቃችሁ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም እሳት ከሰማይ ወርዶ ይበላችኋል»በማለት አስብከው የዋሐን ምእመናን ሁለተኛ እንዲጠመቁ አድርገዋል ።

ለ/ ያልነበራቸውን ብቃት በሰው ሠራሽ ለመጠቀም አስበው "ማርያም ተገለጠች" በማሰኘትና በማጭበርበር የንጹሐን ዜጎች ሕይወት በከንቱ እንዲጠፋ ምክንያት ሁነዋል ።

ሐ/ ልብንና ኵላሊትን የሚመረምር ረቂቅ አምላክ መኖሩን በመዘንጋት «መንበሩን ይልቀቁ»የሚለውን የሕዝበ ክርስቲያን ድምፅ ሲሰሙና ግፊቱ እያየለ ሲመጣ በለመዱት የሐሰት ኮሚኒስታዊ ሲስተም ለመጠቀም አስበው በልዩ ረዳታቸው አባ ዜና ማርቆስና በመምህራቸው አባ መልከጼዴቅ አማካሪነት «ቅዱስነታቸው ቀደም ብሎ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ከሥልጣን ወረዱ»በማሰኘት መንግሥትንና እግዚአብሔርን ማታለል ሞከሩ ።

መ/ ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ «ፓትርያርኩ ከሥልጣናቸው የወረዱት በሕመም ምክንያት ስለሆነ ሲሻላቸው ወደ ሥልጣናቸው ይመለሳሉ» የሚሉ ሰባክያንን አስነስተው ከማሰበካቸውም በላይ የዚሁ ሐሰት አስተባባሪ የሆኑት አባ መልከጼዴቅ በአሜሪካ ድምፅ በጀርመን ራዲዮ ፣ እንዲሁም በቢቢሲ በማስተባበያ እንዲሰማ አድርገዋል ።

ይህ ኮሚኒስታዊ ሲስተም ባይጠቅማቸውም መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የሥራ ጓደኞቹንና የግብር አበሮቹን ከሥልጣን ለማስወገድ በፈለገ ጊዜ «ፍቅረ ሥላሴ ወግ ደረስ ፣ ደበላ ዲንሳ ፡ ፍሥሐ ደስታና ለገሠ አስፋው»በሕመም ምክንያት ከሥራ ተሰናብተዋል በማለት አውርቶ ነበር ፡ ራሺያውያንም ሚኻኤል ጐርባቾቭን ከሥልጣን ለማውረድ የሞከሩት በዚሁ ዘዴ ነበር ፣ ታዲያ ሲያዋጣው አልታየም አፈረበት እንጂ ። አባ መርቆሬዎስና አጃቢዎቻቸው በዚሁ ዘዴ ለመጠቀም ብዙ ጣሩ ግን አልሆነም ።





www.ethiopianorthodox.org

እኮ አሁን አባ መልከጼዴቅ ለምንድነው በሐሰት ለመጠቀም የሚፍጨረጨሩት ?? እረ ለመሆኑ አቡነ መርቆሬዎስ ሕዝቡ "የደርግ ሹም ነዎት ፣ ቤተክርስቲያን ለአባትነት አትፈልገዎትም ሲላቸው እንዴት በግድ "አባት ልሁን" ይላሉ ? እንግዲህ እውነቱ ይኸው ነው እውነቱ ሲገለጥ የሚያፍረው ማነው ? ወይ አላርፍ ያለ ጣት ! !'

## « ያየነውን እንመሰክራለን »

ምስክርነት ትልቅ ኃላፊነትና ወቀሳ ከሰሳ የሚያስከትል ዕዳ ነው በመሠረቱ ምስክርነት በብዙ ዓይነት መንገድ ሊታይ ቢቻልም በጉልህ የታወቁ ሁለት ናቸው ፤ እነርሱም ፩ኛ/ የእውነት ምስክርነት ፪ኛ/ የሐሰት ምስክርነት ተብለው ይጠራሉ ። አንዳንድ ሰዎች የሐሰት መስካሪዎች ተብለው ሲዘለፉ እንዲያውም መንግሥትና እግዚአብሔር ሹሞ በፍርድ ወንበር ባስቀመጣቸው ዳኞች ፊት ቆመው በእውነት ስም መስክረው ነገሩ ሐሰት ሆኖ ሲገኝ የሚቀጡ ወይም የተቀጡ ብዙዎች ናቸው ። በእውነት ስለ እውነት የመሰከሩና የሚመሰክሩ ግን ስለእውነተኛነታቸው ይመሰገናሉ እንጂ የሚነቅፋቸው አንድም የለም ።

በዚህ ጽሑፋችን የምንሰጠው ምስክርነት ግን ከሁሉ የተለየ ነው ። ይኸውም ስለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ይሆናል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እያበረከቱ በመንፈሳዊ ኮሌጅ ዘመናዊና መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ጊዜ የቅርብ ወዳጆቻቸውና የትምህርትጓደኞቻቸውስለነበርንና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበራቸው ጠንካራ መንፈስና ጽኑ እምነት ለዚህ ከባድ ኃላፊነት እንደሚያበቃቸው የተናገሩ አበው ነበሩ ። ቅዱስነታቸው በሥራ ፣ በትምህርት ፣ የአንደኛነቱን ደረጃ ከዓመት እስከ ዓመት ከመያዛቸውም በላይ በፈሪሃ እግዚአብሔር ፣ በእፍቅሮ ቢጽና በተወከፎ ነግድ ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው ፣ ርኅሩህ ፣ አዛኝ መሆናቸውን ሁሉም የሚያውቀው ሐቅ ነው ። ስለዚህ ቅዱስነታቸው በተጠቀሱት ባሕርያት የሚገለጽ መንፈሳዊ ጸጋ እያላቸው ነው ሰዎች እውነቱ ባደፈና በጎደፈ የሐሰት ጨርቅ ሸፍነው ለከባድ ፈተና አሳልፈው የሰጡአቸው ። ይሁን እንጂ አባቶቻቸው ሐዋርያትካሳለፉት መከራ የከፋ ወይም የበለጠ አለመሆኑን ቀደም ብለው በትምህርት ገበታቸው ሳሉ የተረዱትና የተገነዘቡት ስለነበረ ፈተናውን በጸጋ ተቀብለው አልፈውታል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብም የሚፈልገው መንፈሳዊ አባት እንደቅዱስነታቸው ያለና በምድራዊ ፈተና የማይበገርና የማይበረግግ ነው ። ቅዱስነታቸው እንዳሉት ከባዱን ኃላፊነት ተረክበው የእግዚአብሔርን በጎች ማለትም ምእመናንን ተግተውና ደክመው ሰለቸኝ ሳይሉ ነጣቂዎች ፤ አታላዮችና ቀብዝብዞች በየመንደሩ እየተሰገሰጉ የመጡ የሃይማኖት አፈቀላጤዎች ከሚያስተምሩት የተሳሳተ ትምህርት እንዲጠብቁና እንዲያስጠብቁ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን አንዳንድ ሐቀኛ መንፈሳውያን አባቶች ባስተማሯቸውና በወረሱት መንፈሳዊ ቅንዓት ለየትኛውም መጤ ሃይማኖት ሳይንበረከኩ ፤ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታቸው ጸንተው ፣ በሰበካ ጉባኤና በመሳሰሉት የሃይማኖት ትሩፋት ቤተ ክርስቲያናችንን እያጠናከሩ ቅዱስነታቸውን የመሰለ መንፈሳዊ አባት እስኪያገኙ ድረስ መቆየታቸውና ባለፉት የመከራ ዓመታት ከባዱንና አስቃቂውን የሥጋዊና የመንፈሳዊ ፈተና አልፈው ፤ ለዚህ ብሩህ ሥጋዊና መንፈሳዊ አደራ የሚበቁበት ወቅት መድረሳቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያህል መንፈሳዊ ኃይል ይሰማቸው ይሆን ? ለዚህ መልሱ ከባለቤቱ ፣ ከቅዱስነታቸው ነው ።

የእግዚአብሔር መንፈስ ያልተለየው ጥቂት ተምሮ ብዙ የሚያውቅ ለእምነቱና ለአገሩ ነፃነት ቀናዒ የሆነውን ሕዝብ ጠባቂና መንፈሳዊ አባት እንዲሆኑ የፈጣሪአቸውን ጥሪ ሲቀበሉ መንፈሳዊ ኩራት ሊሰማቸው ይገባል ። ቅዱስነታቸውና ብፁዓን የሲኖዶሱ አባላት እንዲሁም የተለያዩ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መምህራን የቆሙለትን ሕዝብ አይዞህ አልንልህ በማለት በሐዲስ መንፈስ ሐዋርያዊ ድምጻቸውን ሲያሰሙት በበለጠ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነቱ እየጠነከረ ሊሄድ ይችላል ።

በብዙ ምእመናን አንደበት የወላድ መካን እየተባለች ትጠራ የነበረችው ቤተ ክርስቲያናችን በቅዱስነታቸው መንፈሳዊ ጥረት አባባሉ ተሰርዞ ፣ በአገር ውስጥም ሆነ ወደ ውጪ አገር ልካ መንፈሳዊ ትምህርት ያስተማረቻቸው አሰባሳቢ አጥተው ፣ በየድርጅቱና በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተበታተኑት ልጆቿን ለማሰባሰብ እንደምትችል ፤ ቀደም ሲል የነበሩት የቤተ ክህነት ኃላፊዎች ለገጸ በረከት አቅርበው ያስወሰዱትን ከፍተኛና መለስተኛ የመንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች ከመንግሥት ጋር በመነጋገር መፍትሔ ተፈልጎላቸው እንደሚመለሱ ተስፋ ያደርጋል ።

መንፈሳዊው ትምህርት ከቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ወጣ እያለ በየምእመናኑ አደባባይ በተሻለ ትምህርት አሰጣጥ እንደሚቀርብ ሊቃውንት (መምህራን)የኢትዮጵያ ሕዝብ ነባር ቅርስ የቆየውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እያስተማሩ ኑሮአቸው በየመቃብር ቤቱ ሆኖ፤ ከተማሪዎቻቸው ጋር የልመና እንጀራ እየተጋሩ የሚኖሩትም ጠቃሚነታቸው ታውቆ ለኑሱና ለሚሰጡት ትምህርት በቂ እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው አንዳንድ ቅን አመለካከት ያላቸው ሰዎች ከሥርዓተ ሲመቱ ማግስት መተንበይ ጀምረዋል ።

ጠቅላላውን የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ነባር ታሪክ ሠሪና ምስክር ራሷ ቤተክርስቲያን ስለሆነች ፣ መለስተኛ እንክብካቤ የሚደረግላቸውም ሆነ ፈጽመው የተረሱና እያሉ የት እንዳሉ የማይታወቁ በየአገር ቤቱ ያሉ ገዳማትና አድባራት አብያተ ክርስቲያን ከህንጻቸው ጀምሮ እስከ ንዋያተ ቅድሳቱ እንክብካቤ እየተደረገላቸው ቢያዙ ለምእመናኑ መንፈሳዊ ተስፋ ፤ ለታሪክ ጥበቃ ትልቅ አገልግሎት ሰጪ በቱሪስት አማካይነት ለቤ/ክርስቲያናችን የገቢ ምንጭ መሆናቸው ታውቆ በቅዱስነታቸው ዘመነ ፐትርክና ትልቅ ጥረት የሚጠይቅ ነውና ለተጠቀሰውም ሆነ ላልተሥቀሰው የሚያደርጉት መንፈሳዊ ጥረት ግቡን እንዲመታላቸው የቸሩ አምላክ ፈቃድ ከቅዱስነታቸው ጋር እንዲሆን በመመኘት ፤ ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመሪያው መልእክቱ ፩ ፣ ፫ ያየነውን የሰማነውን ለእናንተ ደግመን እናወራላችኋለን እንዳለው በእውነት ለእውነት እንመሰክራለን ። ከዚህ በመቀጠል ለቅዱስነታቸው ልዩ ልዩ ቅኔያት በትህትና አቀርባለሁ ።

### ጉባኤ ቃና

፩- እምርሁቅ ጳውሎስ ሰላመ ቅዱሳን እብለከ ፤
እስመ ሊቀ ምርፋቅ ከልዓኒ ብሩህ ገጽከ ።

፪- ጳውሎስ ለከ ቡራኬ ቴዎፍሎስ ጸጋ ፣
እስመ ዘመንፈስ አንተ ወርሑቅ ግዙፍ ሥጋ ።

ዘአምላኪየ

፫- ጳውሎስ ሀሊ እንተ በቅድሜከ ሀሉ ፣
ወነጽር በዓይነ ሀሊና ዘአሀለፍከ ዙሉ ፣
አምጣነ በገ ትጸውር ለእግዚአብሔር መስቀሉ ።

ዋዜማ ፣

፬- ወልደ ይስሐቅ ወባስልዮስ ወወልደ ቴዎፍሎስ አብ ዘበመንፈስ ቅዱስ ተመልአ ፣
ጳውሎስ ለቃለ አዋዲ ዮሐንስ ካልኡ ፣
ወእመ ለበስከ ጽድቅ ዘሐዋርያት አምጽኡ ፣
ትቤ በቃል ነዋ በግዑ ፣
እስመ አንተ ጥበቡ ወስምኡ ፣

### መወድስ

፭- ጳውሎስ ንዓእ በትረ ተሐድሶ ፣ ከመታስተጋብእ ቅድመ ዝርዋነ አባግዒከ ፤
ወማዕጾ ብርት ግበር አንቀጸ ቤትከ ፣
ለአቂብ እምተአዳዊ ፣ ሃይማኖተ ንዋየ ዚአሁ ለጴጥሮስ አቡከ
ወይከኑ ጥቡእነ ፣ ወእሁዛነ ሰይፍ ዘቶማስ ብፁእን ኖሎትከ ፣
ትሄውጽሂ ለለዕለቱ ለሰሚአ እሙን ቃልከ ፣
እመ ምእመናን ኢትዮጵያ እንተ በስኢል ወለደተከ ፣
ወበዕለታ ለፍትሕ ቅድመ እግዚእከ ፤
ዙነኔ ስምዓ ጽድቅ ከመ ኢንተ ሐፈር በቅድሜከ ።

ከኪሮስ ወ/ሚካኤል እንግዳ
የቀድሞ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪ

## " ንጽሕት በድንግልና "

የቤተ ክርስቲያኒቷን ጥንተ እምነት ከመሠረቱ ለማጥፋት በውስጧ ሠርገውየገቡ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ወክለው እንሰብካለን እናስተራለን የሚሉ ጸረ ቅድስት ድንግል ማርያም የሆኑ መናፍቃን እየተሽለከለኩ ወቅትና ጊዜ እየጠበቁ በቤተ ክርስቲያኒቷ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ላይ ይገኛሉ ።

የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ እምነት ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘ የቅድስት ድንግል ማርያም ፣ የጻድቃን ሰማዕታት ፣ የቅዱሳን መላእክት አማላጅነት በስፋት ተዘርግቶ በቤተ ክርስቲያኒቷ ዐውደ ምሕረት እየተሰጠ ነው ።

በዚህ መሠረት ምእመናኑ በአላቸው ፍቅረ እግዚአብሔር ዝክር በመዘከር ፣ ማኅበር በመጠጣት ከእግዚአብሔር ጋር ያለ አንድነታቸውን በማጠንከር እምልተውና እስፍተው ይገኛሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

ይሁን እንጂ ምልጃ(፪ ቆሮ ፫ ፣፩
መናፍቃን እንደሚሉት ሳይሆን ጻ
ድቃን ፣ ሰማዕታት የክብር ቃል
ኪዳንን ከፈጣሪያቸው የተቀበሉት
በገድል በትሩፋት ከዚያም ሕይወ
ታቸውን በመስዋዕትነት አሳልፈው
ለሠይፍ ፤ ለስለት በመስጠትና
"ጠባብ እንቀጽን" ካለፉ በኋላ
ነው ።

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል
ማርያም ክብር ከዚህ ሁሉ የተለየ
በሥነ ተፈጥሮዋ የርስሐት ነጠብ
ጣብ የሌለባት 'ንጽሕት በድንግልና
አልባቲ ሙስና ወልድ ተወልደ
እምኔሃ" ተብላ በቅዱስ ያሬድ
የተነገረላትና በተለይ የኢትዮጵያ
ውያን እናት ናት ። መልአኩ ወደ
እርሷ መጥቶ እንቺ በጸጋ የተመላሽ
እመቤት ሰላምታ ላንቺ ይገባሻል፣
እግዚአሔር ከአንቺ ጋር ነውና
ሉቃስ ፩ ፣ ፳፰ ብሎ ተናግሮላታል
ከእርሷ የሚወለድ ወንድ ልጅ
ሕዝብን ከኃጢአት የሚያድን መ
ሆኑን አብሥሮ በእሷ ሥነ ተፈጥሮ
የውርስ ኃጢአት የሌለባት ንጽሕት
ተስፋ አዳም በእሷም መሠረትነት
ወደ ቀደመ ቦታው የተመለሰ የብ
ዙኃን መመኪያ ናት ።

ቅዱስ ያሬድ "አንጺሐ ሥጋሐ
ቀዲሶ ኪያሃ ሃደረ ላዕሌሃ" ብሎ
"ሥጋዋን አንጽቶ ቀድሶ በእርሷ
ላይ አደረ" ያለው ሥጋዋን አንጽቶ
ብሎ አመሥጥሮ የተናገረው ቃል
እርሷ የለበሰችው አካለ ሥጋ ርስ
ሐት ኑሮበት ሳይሆን ጥንተ መሠ
ረቷ የነፃ የውርስ ኃጢአት የሌለ
ባት ንጽሕት ድንግል መሆኗን ነው ።

"መናፍቃን በምን መሠረት በመ
ነሣት ይሆን ቅድስት ድንግል የው
ርስ ኃጢአት አለባት ለማለት የቻ
ሉት ? ከመጽሐፈ ነቢያት ፣ ሐዲ
ሳት እርሷ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት
በህሊና አምላክ በክብር የነበረች
በነቢያት ላይ ትንቢት አድሮ የድኅ
ነት ተስፋ መሆኗ የተነገረላት
ንጽሕት ድንግልን የመናፍቅነት
ውርስ ኃጢአት በዘር የተላለፈባ
ቸው ጸረ ማርያሞች በንጽሐ ድንግ
ልናዋ ላይ ያላቸው ጥርጣሬ እስከ
መቼ ድረስ ይወገድ ይሆን ?

ስለ ንጽሐ ድንግልናዋ ክብር
በልሳነ አበው ፣ ነቢያት ፣ ነገሥታት
ካህናት መላእክት በስፋት የተነገረ
ላት ሲሆን ከሁሉም ሥራ እስደናቂ
በማኅፀነ ኤልሣቤጥ ውስጥ ያለ
ሕፃን ሳይቀር በእናቱ ላይ የቀረበ
ላት ሰላምታን አድምጦ ስለ ድን
ግል ክብር ፈንድቆ እንደዘለለና እን
ደሰገደላት ነው እናቱ ኤልሳ
ቤጥ ድምጿን ከፍ አድርጋ «አንቺ
ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረ
ክሽ ነሽ" በሴቶች ላይ ከተላለፈው
መርገመ ሥጋ የነጻች መሆኗን በተ
መስጦ ገልጻላታለች ።

ነቢዩ ዳዊት ካቀረበላት ምስጋና
«ወትቀውም ንግሥት በየማንከ በአ
ልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወኁብርት»
በንጉሥ ቀኝ የተቀመጠች በወ
ርቅ ልብስ የተንቆጠቆጠች ወርቅ
የተባሉ ንጽሕናዋ ድንግልናዋ ነው
"ኅሪት አምላክ" የአምላክ ምርጥ
በሰው አእምሮ ውስጥ ትርጉምና
ክብር በሚሰጣቸው ምርጥ ምሳሌ
ዎች ሁሉ ፍጡራን ቢመስሏት ምሳ
ሌዋን ሊፈጽሙት የማይችሉ ከኢ
ትዮጵያ ኦር. ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ
ያን ሊቃውንትና ካህናት ወጣት ሰን
በት ተማሪዎች ምእመናን እንደበት
እንደ ጅረት ውኃ ውዳሴዋ ሲወ
ርድ ሲዋረድ የማይደርቅ የፍጡ
ራን ምስጋና የማያልቅባት ድንግል
በቤተ ክርስቲያናችን የተለመደ የ
ክብር ውዳሴዋና እማላጅነቷ ዘለ
ዓለማዊነትን ይዞ ይኖራል ።

መ/ዳንኤል ዓለሙ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org